"ፍልስፍናዬ አገልግሎት፤ ዓላማዬም ማገልገል ነው"

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ክብርት አዳነች አቤቤ



# ዘመን

ቅፅ 22 ቁጥር 106 ነሐሴ 2015 | ልዩ ዕትም




# አዲስ አበባ
## የኢትዮጵያ ተምሳሌት !

ባድ የምሳ እቃ እና ሌሎች ተረቶች | አዲስ አበባ ማኅደረ ብዙ



ራስ መኮንን ትምህርት ቤት አካባቢ የሕዝብ እንቅስቃሴ በ1953 ዓ.ም.



# በውስጥ ገጾች


6 “ፍልስፍናዬ አገልግሎት፤ ዓላማዬም ማገልገል ነው”
ክብርት ከንቲባ አዳነች አቤቤ

18 ባዶ የምሳ እቃ እና ሌሎች ተረቶች

26 የብርሃን መንገድ

36 የአብሮነት መዲና

42 አዲስ-ጥበብ

48 አዲስ አበባን በታሪክ መነጽር

60 ዋናው ነገር ጤና

64 የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ልብ

68 ትምህርት

70 አዲስ ስፖርት

## ርእሰ አንቀጽ

# አዲስ አበባ

## የኢትዮጵያ ተምሳሌት!



የሁሉም ኢትዮጵያውያን መኖሪያ፣ የዲፕሎማሲ መናኸሪያ፣ የበርካታ ውብና ድንቅ ባህሎች መገኛ፣ የኅብረ ብሔራዊነት ማሳያና የኢትዮጵያ ተምሳሌት ናት የእኛዋ አዲስ አበባ።

የተስማሚ አየር ንብረት ባለቤትና የታታሪ ሕዝቦች መገኛ የሆነችው የኢትዮጵያዋ መዲና የዕድሜዋን ያህል ዕድገት ሳታሳይ መኖሯ በብዙ ማስረጃዎች የተረጋገጠ ሐቅ ነው። የፍትሐዊነት መጓደል፣ በፕላንና በዕቅድ አለመመራት፣ ሕዝብን አሳትፎ ልማትን በማረጋገጥ በኩል የታዩ ክፍተቶች ወዘተ አዲስ አበባን እንደ ስሟ አዲስ እንዳትሆን አድርገዋት የቆዩ ትልልቅ የዕድገት እንቅፋቶቿ ነበሩ።

በ132 ዓመት ዕድሜዋ በ32 ከንቲባዎች የመመራት ዕድል የገጠማት አዲስ አበባ መንግስታዊ አመራሮችዋና ከንቲባዎቿ የቻሉትን ያህል ሠርተው ዐሻራቸውን በዘመን ጅረት ውስጥ አሳርፈዋል።

በኢትዮጵያ የለውጥ ዘመን መከሠት ለአዲስ አበባ በርካታ ትሩፋቶችን ይዞላት መጥቷል። በዚህም አዲስ አበባን እንደገጠር ማስተዳደርና ቅድሚያ ለገጠሩ የሚሉ የተሳሳቱ ፖሊሲዎችና አካሄዶች ተቀልብሰው፤ አዲስ አበባን የኢትዮጵያ ተምሳሌትና የልማት ሞተር የማድረግ እንቅስቃሴዎች ተካሂደዋል፤ በአጭር ጊዜ ውስጥም እመርታዊ የሚባሉ ለውጦች ተመዝግበዋል።

አብርሆት ቤተመጻሕፍት፣ የቸርችል - መስቀል አደባባይ ፕሮጀክት፣ ዓድዋ መዚየም፣ አንድነት፣ ወዳጅነት፣ እንጦጦ ፓርኮች፣ የንግድ ባንክና የመከላከያ ግዙፍ ሕንጻዎች በለውጡ ዘመን ተወጥነው የተተገበሩና የአዲስ አበባን የዕድገት ግስጋሴ አፍ አውጥተው የሚመሰክሩ ታላላቅ መገለጫዎች ናቸው።

ዕድገት በሕንጻና በቁስ ሳይሆን በሰብዓዊ ልማት ነው መመዘን አለበት የሚለው  የለውጥ አመራር እሳቤም አዲስ አበባ ከሁሉ ነገር አስቀድማ ለዜጎቿ ትኩረት ሠጥታ እንድትሠራ አድርጓታል።

የወላጆችን ሸክም የአቀለለውና የነገዋን ኢትዮጵያ ተረካቢ ዜጎችን በብቃት ማፍራትን ታሳቢ ያደረገው የተማሪዎች ምገባና የደንብ ልብስ ድጋፍ፤ የአረጋውያን ምገባ፣ የዐቅመ ደካሞች ቤት እድሳት፣ ማዕድ ማጋራትን የመሳሰሉ የተቀደሱ ተግባራት በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎችን ሕይወት ቀይረዋል፡፡ የመኖር ተስፋቸውንም ያለመለሙ የአዲሲቷ አዲስ አበባ መገለጫ ባሕርያት ሆነዋል። አዲስ አበባ የዜጎቿን የኑሮ ጫና በማቃለልም በዓመት ከስምንት ቢሊዮን ብር በላይ በጀት በጅታ እየሠራች ትገኛለች።

አርሶ አደሮችን ከሚያፈናቅልና ከሚገፉ ሥርዓት የተላቀቀችው አዲስ አበባ እነዚህኑ የልማት ኃይሎች ደግፋና አቅፋ ትራክተር ጀኔሬተር፣ የውሃ መሳቢያ ፓምፕና አስፈላጊ ቴክኖሎጂዎችን አቅርባ የዕድገቷና የውበቷ አካላት አድርጋቸው እየተጓዘች ትገኛለች።

ከጄኔቭ በመቀጠል የዓለም የዲፕሎማቲክ ከተማ የሆነችው አዲስ አበባ የበርካታ ዓለም አቀፍ አህጉራዊና ቀጣናዊ ድርጅቶች መቀመጫ ናት። ይኸም ለአዲስ አበባ ተጨማሪ ውበት ድምቀትና ጥቅም ሆኗታል። በመዲናዋ የሚከናወኑ ዓለም አቀፍ ሁነቶቸም ለአዲስ አበባ ተጨማሪ ደምቀትና ገቢ ሆነውላታል።

የአዲስ አበባ ለዘመናት የተከማቹ ችግሮቿ የሥራ ሰዓትንና ቀንን ቆጥሮ በመሥራት ብቻ የማይመለሱ መሆናቸውን የተገነዘበው የከተማዋ አስተዳደርም ከችግሯ አላቆ ለዜጎቿ የተመቸች መዲናን እውን ለማድረግ ለዕድገቷና ስኬቷ ሌት ተቀን መትጋቱን ቀጥሏል።

ዊንዶው ኦፍ አፍሪካ፣ የአቪድ ግሩፕ መኖሪያ ቤቶች፣ ግዙፉ የኢኮኖሚ ዞን ወዘተ ለነገዋ አዲስ አበባ ሰርግ በዝግጅት ላይ ያሉ አጓጊ መሠረተ ልማቶች ናቸው። ሕዝቦቿን አሳትፋና አወዳጅታ በልማት ሩጫ ላይ የምትገኘው አዲስ አበባ ጅምሯ ሠምሮ ራእይዋ ተሳክቶ የሚታይበት ዘመን እውነትም መቃረቡን እርግጠኛ ሆኖ መናገር ያስችላል!


በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እየታተመ የሚወጣ

ኢፕድ

ዋና አዘጋጅ፡- ሳሙኤል ይትባረክ
ፖ.ሳ.ቁ፡- 30145
ስልክ፡- 011-1264207
Sammes.zellek@gmail.com
zemenpress@gmail.com
ከፍተኛ አዘጋጆች፡- ስሜነህ ደስታ

አዘጋጆች፡- ተስፋ ፈሩ
ዮርዳኖስ ፍቅሩ

ማስታወቂያና ደንበኞች አገልግሎት
ስልክ፡- 011 1 56 98 73
ፋክስ፡- 011 1 57 44 40

ማከፋፈያ፡-
ስልክ፡- 011 1 57 02 70

ግራፊክስ ዲዛይን
ትዕግሥት ሰይፋ

ፎቶግራፍ፡-
ሳሙኤል ተስፋዬ
ዳኜ አበራ
አሸናፊ ጉደታ
ገባቦ ገብሬ
አጋፔ ጌዮን
እዮብ ተፈሪ


TOP-UP
ADDIS ABABA
አዲስ አበባ

# “ፍልስፍናዬ አገልግሎት፤ ዓላማዬም ማገልገል ነው”

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ክብርት አዳነች አቤቤ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክብርት ከንቲባ አዳነች አቤቤ የዘመን መጽሔት ልዩ ዕትም እንግዳ ናቸው። በቆይታችን በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በተለይም ካለፉት ሦስት ዓመታት ወዲህ የተከናወኑና እየተከናወኑ ያሉ ዘርፈ ብዙ የለውጥ ሥራዎችና ተያያዥ ጉዳዮችን አንሥተናል። ስለከተማዋ የልማት ሥራዎች አተገባበር፣ በኢኮኖሚ እና በሰው ተኮር ልማት ሥራዎች ላይም ገለጻ አድርገዋል። መልካም ንባብ።

**ዘመን፡- በቅድሚያ ከዘመን መጽሔት ጋር ቆይታ ለማድረግ ስለፈቀዱ እና ስለሰጡን ጊዜ እናመሠግናለን።**

**ክብርት ከንቲባ አዳነች፡- እናንተም** ከእኔ ጋር ቆይታ ለማድረግ ስለመጣችሁ እኔም አመሠግናለሁ።

**ዘመን፡- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እየተሠሩ ያሉ ሰፋፊ የልማት ሥራዎች አሉ፤ እነዚህ ሥራዎች ከትግበራ በፊት እንዴት ታሰቡ? ምን ዓይነት የአመራር አቅጣጫስ ተከተላችሁ?**

**ክብርት ከንቲባ አዳነች፡-** “እንዴት ታሰበ?” ለሚለው ጥያቄ፣ የሥራ ሐሳብ የሚመነጨው ከሐላፊነት ነው። አንደኛው መነሻ የከተማዋን አጠቃላይ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ጥያቄዎችን መመለስና መልካም ሥራዎችንም ማስቀጠል የሚቻለው እንዴት ብንመራው ነው? ከሚል መነሻ ነው። ሌላው፤ ከተማዋን እንደሚመራ ከንቲባ፤ እንደ ሴትም፣ እንደ እናትም በአዲስ አበባ እናቶችና ሴቶች ላይ ያሉ ጫናዎችና ሁኔታ ከግምት ማስገባትና ማየት ይገባል።

የሐሳቡ መነሻ በአንድ በኩል የሕዝቡን ጥያቄ መመለስ ነው። ከተማዋን ማሳደግ፣ ከተማዋን መለወጥ፣ አዲስ አበባን ለነዋሪዎቿ ምቹ ማድረግ

> “ለማገልገል በደከመንና በተሰላቸን ሰዓት ግን ሐላፊነታችንን መልቀቅ ነው ያለብን። አገልግሎት ውስጥ ልግመኝነት፣ አገልግሎት ውስጥ ሌብነት እና ሌሎች ነገሮች ደባል ሆነው ከመጡ ትክክለኛ አገልጋይ መሆን አይቻልም”





ነው። የማኅበራዊ ጫናዎቻቸውን መቀነስ የሚቻልበትን ስልትና ዕቅድ መንደፍ አስፈላጊ ነው። "የነዋሪዎችን ጥያቄዎች የመመለስ ጉዳይ ግዴታ ነው" ብለን ከመላው አመራር ጋር ትኩረት ሰጥተን ሠርተናል። ከተማዋ የሀገራችን መዲና፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሚናዋም ሰፊ ነው። ዓለም አቀፋዊ ሚና ያላት ከተማ እንደ መሆኗ ዘመናዊና ሁሉንም ያማከለ የአመራር ስልት ስለምትጠይቅ፤ በዚህ ልክ መጀመሪያ ሐሳባችንን አደራጅተን ነው ወደ ሥራ የገባነው።

የኢትዮጵያ ምልክት የሆነች፣ አፍሪካዊ መልክ ያላት፣ በሌላ በኩል ደግሞ ዓለም አቀፋዊና አህጉራዊ ሚናዋን በሚገባ የምትወጣ፤ አስፈላጊ አገልግሎቶችን ማቅረብ የምትችል፣ ውበትና ከተሜነትን የተላበሰች ዘርፈ ብዙ ሚናዋን የምትመጥን ተወዳዳሪ ከተማ መሆን የምትችልበትን መነሻ ሐሳብ ይዘን፣ በተሠሩ መልካም ሥራዎችም ላይ ጨምረን፤ ጉድለቶቿን እየዘጋን እንድንቀጥል የሚያደርጉ መነሻዎች ይዘን ነው ወደ ሥራ የገባነው።

**ዘመን፡- እርስዎ ሥራዎችን ሲመሩ፣ ሲያቅዱ፣ ሲያስተባብሩ የሥራ ፍልስፍናዎ ምንድነው?**

**ክብርት ከንቲባ አዳነች፡** በእኔ እምነት፣ እንኳን አንድ ትልቅ የሐላፊነት ቦታ ላይ እንድትመራ ሐላፊነት የተሰጣት አመራር ቀርቶ ማንም ግለሰብ የሚኖርለት ዓላማ ሊኖረው ይገባል። በዚህ ምድር ላይ ሰው ሆኜ የመኖሬ ዓላማ ምንድነው? መኖሬ ለምን አስፈለገ? ሰው ሲኖር እንዲሁ አድጎ፣ በልቶ ጠጥቶ ሥራ ሠርቶ የግል ጉዳዩን አሟልቶ ኖሮ ለማለፍ መሆን የለበትም። ከዚህ የሚበልጥ የሚኖርለት፣ ዋጋ የሚከፍልለት፤ የሚደክምለት፤ ጊዜውን የሚሰጠው ዕውቀቱንና ፈጣሪ የሰጠውን፣ አለኝ የሚለውን ነገር መልሶ መስጠት የሚችል መሆን አለበት። ሰው የሚኖርለት አንድ ዓላማ ሊኖረው ይገባል ብዬ አምናለሁ።

እኔ ፍልስፍናዬ አገልግሎት ነው፤ ዓላማዬም ማገልገል ነው። ወደ መንግሥት ሐላፊነት የሚመጣ ሰው ለማገልገል የቆረጠ መሆን አለበት። በአንድ ጊዜ ሁለት ዓይነት ሰው፣ በአንድ በኩል አገልጋይ፣ በሌላ በኩል ነጋዴ ወይም ሐብታም መሆን አይቻልም። አገልጋይ ለመሆን ቁርጠኝነት፣ ጊዜውን እና ያለውን ዕውቀት ያለስስት መስጠት አለበት። ወደ ሐላፊነት ከመጣንም ወዲህ አመራሩን መሠረት ያስያዝነው ትልቁ ነገር 24 ሰዓት፣ ሰባቱንም ቀናት ማገልገል አለብን የሚል ነው።

እሑዳችን አገልግሎት ነው፣ ቅዳሜያችን አገልግሎት ነው፣ ማለዳችን አገልግሎት ነው፣ ምሽታችን አገልግሎት ነው፣ ቀናችን አገልግሎት ነው፤ ክብራችን አገልግሎት ነው...ማገልገል... ማገልገል... ማገልገል። ለማገልገል በደከመንና በተሰላቸን ሰዓት ግን ሐላፊነታችንን መልቀቅ ነው ያለብን። አገልግሎት ውስጥ ልግመኝነት፣ አገልግሎት ውስጥ ሌብነት እና ሌሎች ነገሮች ደባል ሆነው ከመጡ ትክክለኛ አገልጋይ መሆን አይቻልም። አገልግሎት ደግሞ ከራስ በላይ፣ ከግል ፍላጎት በላይ ነው። እኔ በዚህ አምናለሁ፤ እየኖርኩትም ነው ብዬ ራሴን በዚህ ደረጃ መግለጽ እችላለሁ።

**ዘመን፡ አዲስ አበባ ከተማ ላይ ሰው ተኮር ሥራዎች በብዛት ተሠርተዋል፣ በእነዚህ ሥራዎች የተገኙ ለውጦችን እንዴት መግለጽ ይቻላል?**

**ክብርት ከንቲባ አዳነች፡-** ይሄ "የሥራችሁ መነሻ፣ ሐሳባችሁ ምንድን ነው? ከሚለው ጥያቄህ ጋር የሚያያዝ ነው። መነሻ ሐሳባችን የሕዝቡን መሠረታዊ ጥያቄዎች እና ጫናዎች ምን እንደሆኑ ከመረዳት የሚነሣ ነው። ከዚያ ደግሞ ዓላማችን ማገልገል ነው ካልን አዲስ አበባን በጥቅሉ ስናይ ለነዋሪዎቿ የከተማ አቀፍ ሚና ያላት እና ለኑሮ ምቹ ማድረግ ይኖርብናል። ከተማን ምቹ ማድረግ ስንል ጥሩ መንገድ፣ የጤና አገልግሎቶችና ትምህርት ቤቶች እንዲኖሩን ማድረግ ብቻ አይደለም። ምቹነትን የመፍጠር ሥራ የእያንዳንዱ ማኅበረሰብ አኗኗር ምን እንደሚመስል፣ ጫናው ምን እንደሆነ፣ ምን ተመቸው? ምንስ ጎደለበት? የሚለውን ከማወቅ የሚነሣ ነው። ይህንን መነሻ አድርገን ስናይ የአዲስ አበባ ሕዝብ የተለያየ የገቢ ደረጃ ያለው ነው። በአንድ በኩል ቁጥራቸው አናሳ ቢሆንም የተሻለ ገቢ ያላቸው ትልልቅ ሀብታሞች የሚኖሩባት፤ በሌላ በኩል ደግሞ ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ያሉና ፈጽሞ ምንም ገቢ የሌላቸው፣ የመንግሥትን ድጋፍ የሚሹ የነዋሪዎችም ቁጥራቸው ቀላል ያልሆኑባት ከተማ ናት። ሁሉንም ማገልገል አለብን። አደጉ በምንላቸው ትልልቅ ሀገራት፣ የገቢ ዐቅማቸው ዝቅተኛ የሆኑ ነዋሪዎችን ዜጎቻቸው በመሆናቸው ብቻ ዐቅም ያለው ዜጋ የሚያገኘውን አገልግሎት እንዲያገኙ ያደርጋሉ። አዲስ አበባም ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ቁጥራቸው ቀላል የማይባል ነዋሪዎች ያሏት ከተማ ናት። ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ ሚናዋ ትልቅ መሆኑን ማየትም ያስፈልጋል። እነዚህን ባማከለ መንገድ ትልልቅ ሜጋ ፕሮጀክቶችን ዐቅደን መሥራት፣ በሌላ በኩል ደግሞ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውና ምንም ገቢ የሌላቸውን የከተማችን ነዋሪዎች አገልግሎት በትክክል የሚደርሳቸው፣ የሚታሰብላቸው ማድረግ መቻል አለብን።



የሰው ተኮር ሥራችን ዓላማ የተቸገሩ የከተማ ነዋሪዎች ከገቢ የሚካፈሉ፣ ከልማቱ የሚቋደሱ እና ፍትሐዊነት የነገሠባት ከተማ ማድረግ አለብን የሚል ነው። የምንሠራው ለሰው ነው። የፓርቲያችን የብልጽግናም ፍልስፍና አንዱ መርሕ "ትኩረታችንን ሰው ላይ እናድርግ" የሚል ነው። ከምንሠራቸው ሥራዎች በፊት፣ በቅድሚያ ሰው እናስቀድማለን። ስለዚህ ዝቅ ብለን የሰውን ኑሮ ማየት፣ የነዋሪውን ጫና ስሜቱን መጋራት አንዱና የመጀመሪያው ነው። ይህን መነሻ አድርገን ስንነሣ በከተማችን ላይ ትልልቅ ሰው ተኮር ሥራዎች እንዲሠሩ ውሳኔ ተወስኖ የተሄደባቸው ናቸው። ሰው ላይ ያልዋለ፤ ለሰው ሕይወት የማይደርስ የአዲስ አበባ በጀት በፍትሐዊነት ለነዋሪው ደርሷል አይባልም። እጅግ በጣም ዘመናዊ መንገዶችን ልንሠራ እንችላለን። ዘመናዊ ሕንጻዎችን ልንገነባ እንችላለን። ብዙ ታሪካዊ ነገሮችን ልንሠራ እንችላለን። ይሁንና ዛሬ ላይ ለሰው ሕይወት መድረስ የሚችል የሚቆረስ ነገር ከሌለው ግን ሙሉ ሊሆን አይችልም። ግንባታው የራሱ አስተዋፅኦና ድርሻ ቢኖረውም ሙሉ ሊሆን አይችልም። ለዚህ ነው "መጀመሪያ የአዲስ አበባ ሕፃናት፤ ነገ ይህችን ሀገርና ከተማ ተረክበው የሚያሳድጉ ልጆች እየተራቡ ትምህርት ቤት ውስጥ መዋል የለባቸውም" ብለን



የተነሣነው። ልጆች ተርበው ሲወድቁ ከማየት በላይ ሕመም የለም። እዚህ ላይ እንደ ከተማ አስተዳደር ብቻ አይደለም፣ እንደ ፓርቲም ተመክሮበት፣ የአዲስ አበባ ተማሪዎች ትኩረት ይገባቸዋል፣ በተለይ በመንግሥት ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎችን መመገብ አለብን በሚል ድምዳሜ ላይ ተደርሶ በጀቱን በይፋ ከተማ አስተዳደሩ ወስኖ ነው ተማሪዎችን መመገብ የጀመረው።

ሥራውን ስንጀምር  ምገባ ያገኙ ተማሪዎች ቁጥር ወደ መቶ ሺህ ያህል ነበሩ።  ከአንድና ከሁለት ዓመት በኋላ ሦስት መቶ ሺህ መድረስ ተቻለ። ዛሬ 2015 ዓ.ም ላይ 750ሺ ተማሪዎችን በቀን ሁለት ጊዜ እንመግባለን። ከምገባው በተጨማሪ ለትምህርት አስፈላጊ የሆኑ ዩኒፎርም፣ ደብተር፣ እስኪሪብቶና ሌሎችም መሠረታዊ ግብዓቶች

> በየዓመቱ በሚኖሩ በዓላት ከ600 ሺ በላይ ዜጎችን ማዕድ እናጋራለን።

ይቀርብላቸዋል። በዚህም ከ20ሺ በላይ እናቶች ሥራ አግኝተው ልጆቻቸውን እየመገቡ፣ በእናትነት ፍቅር እየተንከባከቡ ያገለግሏቸዋል። በሌላ በኩል ደግሞ፣ እነኚህ ተማሪዎች ሀገራቸውን የሚወዱ ነገ ላስተማረቺኝ፤ ለመገበቺኝ ለሀገሬ ነገር መሥራት አለብኝ የሚል ህልም ይዘው እንዲያድጉና በአካልም በአምሮም ብቁ የሆኑ ተማሪዎች እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል፤ እያደረጋቸውም ነው።

በተመሳሳይ ደግሞ እኩልነት ተሰምቷቸው አንዱ የበላይ አንዱ የበታች ሳይሆን፣ ማኅበረሰቡ ውስጥ ያለው የገቢ ልዩነት አእምሯቸውንና ሥነልቦናቸውን እንዳይጎዳ ትልቅ መከላከያ መሣሪያ ሆኖ እያገለገለ ነው። በእኩልነት አብረው ይጫወታሉ፤ ይቦርቃሉ ትምህርታቸው ላይ ትኩረት አድርገው ይማራሉ። የወላጆችም ጫና በዛው ልክ ቀንሷል ማለት ነው።

የአዲስ አበባ ሕዝብ የኑሮ ጫና በዚህ ብቻ የሚያበቃ አይደለም። ትናንት ሀገር አገልግለው በተለያየ ምክንያት የኑሮ እክል ገጥሟቸው ለችግር የተጋለጡ ብዙ ወገኖች አሉ። እነዚህ ወገኖች ጉልበት ባላቸው ጊዜ ሠርተው ገቢ ያገኙ የነበሩ፣ ዛሬ ግን በጤና እና በዕድሜ ጫና ምክንያት ሠርተው መብላት የማይችሉ ናቸው። ኗሪዎቻችን ስለሆኑ እኛ ካልተመለከትናቸው ማንም ሊመለከታቸው አይችልም።

እኛ በቀን ሦስት ጊዜ የምንበላባት፣ ምግብ ተርፎ የሚደፋባትና እሩት ወንድሞቻችን ከቆሻሻ ላይ ምግብ እየፈለጉ የሚበሉባት ከተማ ሌሎች ሥራዎችን ሠራሁ ብላ ብዙ ልትኮራ አይገባም፤ አያስችልምም። መንግሥት ብቻውን ሠርቶ እነዚህን ማኅበራዊ ጫናዎች ስለማይቀንስ በባለሀብቱና ነዋሪው በትብብር 19 የምገባ ማዕከላትን ገንብተናል። ዛሬ ምግብ የቸገረው የራበው የአዲስ አበባ ነዋሪ እጁን ታጥቦ ማናችንም ቤት የሚቀርብ ዓይነት ንጹሕ ምግብ ከ19ኙ የምገባ ማዕከላት በአንዱ መመገብ ይችላል። ከምገባ ማዕከላቱ ተደራሽነት አንጻር ስናየው አዲስ አበባን ሰው ተርቦ የማያድርባት ከተማ ማድረግ የተቻለበትን ትልቅ ስኬት ማግኘት ተችሏል።

በተጨማሪም ዝናብና ፀሐይ የማይከላከሉ፤ ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ ወንዝ ዳር የሚገኙ የፈራረሱ የቀበሌ ቤቶች ውስጥ ለሚኖሩ

> እኛ በቀን ሦስት ጊዜ የምንበላባት፣ ምግብ ተርፎ የሚደፋባትና እሩት ወንድሞቻችን ከቆሻሻ ላይ ምግብ እየፈለጉ የሚበሉባት ከተማ ሌሎች ሥራዎችን ሠራሁ ብላ ብዙ ልትኮራ አይገባም፤ አያስችልምም”

እናቶችና አባቶች 21 ሺ ቤቶችን ሠርተን በእርጅና ዘመናቸው ዐረፍ ብለው ሀገራቸውንና ትውልዱን እየባረኩ መኖር የሚችሉበትን ሁኔታ መፍጠር ችለናል። እነዚህን ቤቶች የሠራነው እንደ መንግሥት ማቅረብ ያለብንን ግብአቶች አቅርበን ማኅበረሰቡን በማስተባበር ነው። ቤቶቹ መታጠቢያ ቤት፣ ማብሰያ ክፍል እና መኝታ ቤት ያላቸው ናቸው።

እኛ ወደዚህ የለውጥ ሥርዓት ውስጥ በምንገባበት ሰዓት አዲስ አበባ ላይ ዳቦ በጣም ችግር ነበር። አዲስ አበባ ግን ዳቦ ብርቅ ሊሆንባት የሚገባ ከተማ አይደለችም። እዚህ ላይ መታወቅ ያለበት ነገር ከዚህ በፊት ሥራዎች አልተሠሩም ማለቴ አይደለም፤ ብዙ ሥራዎች ተሠርተዋል። ነገር ግን በዚህ ደረጃ በብዙ ጫና ውስጥ እያለፍን የሠራነው ሥራ ትልቅ እንደሆነ ደግሞ እውነቱን መናገር ያስፈልጋል። እስከ 2011 ዓ.ም. ድረስ በአዲስ አበባ ከፍተኛ ዳቦ የማምረት ዐቅም ከ300 ሺህ የማይበልጥ ነበር። ከተማዋ ዛሬ ላይ በቀን ከአምስት ሚሊዮን በላይ ዳቦ የማምረት ዐቅም ላይ ደርሳለች። 27 አዳዲስ የዳቦ ፋብሪካዎች ተገንብተዋል። ሰው ተኮር በምንለው የልማት ሥራችን ለሰው በመድረስ፤ ተመግቦ እንዲያድር፤ ደስ ብሎት እኩልነትና ፍትሐዊነት ያለው አገልግሎት እንዲያገኝ በማድረግ እንደ ዜጋ ተገቢውን ክብርና ፍቅር የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት ተችሏል፤ ውጤቶችንም ደግሞ ማየት ችለናል። ስለ ሰው ተኮር ልማትን ስናነሣ ሌሎችንም ጉዳዮች መጥቀስ ይቻላል ነገር ግን እነዚህ ትልልቅ ማሳያዎቻችን ናቸው።

**ዘመን፡- የማዕድ ማጋራት ሥራ ላይ የአገኛችሁት ውጤት እንዴት ይገለጻል?**

**ክብርት ከንቲባ** አዳነች፡- የኮሮና ቫይረስ ሀገራችን ላይ ስጋት በደቀነበት ሰዓት ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትራችን ለመላው ኢትዮጵያውያን “ማዕድ አጋሩ” የሚል ጥሪ አደረጉ። ያንን ጥሪ ተከትሎ ማዕድ ማጋራትን አዲስ አበባ ባህል አድርጋዋለች። ለዚሁ ተግባር በየዓመቱ ከሦስት



ከተማ አስተዳደሩ ለዐቅመ ደካሞች እና ለአካል ጉዳተኞች ድጋፍ አድርጓል

ቢሊዮን ብር ያላነሰ ይሰበሰባል። ባለሃብቶች ይሄ በረከት ነው እያሉ በጣም ደስ ብሏቸው ነው የሚሳተፉት። ስለዚህ በከተማችን ማኅበራዊ ሐላፊነትን የመወጣት ባህል እየዳበረ መሆኑን መናገር የምንችልበት ነው። በዚህ መንገድ በየዓመቱ በሚኖሩ በዓላት ከ600 ሺ በላይ ዜጎችን ማዕድ እናጋራለን።

ይኼን ቁጥር በድግግሞሽ ስናየው በሚሊዮን የሚቆጠር ዜጋን ማገልገል የተቻለበት ነው። ይኽ በዓል ሲሆን ወይም የኑሮ ውድነቱ ሲንር በምናካፍለው ማዕድ ማጋራት ብቻ የሚገለጽ አይደለም። ሰው ካለው ነገር ላይ በማካፈል ጎረቤቱን መርዳት እንዲችል የማድረግ ሥራ ሠርተናል። የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አብዛኛው አመራርም ወርኀዊ ወጪውን የሚሸፍንለትና ማዕድ የሚያጋራው ቤተሰብ አለው። በማዕድ ማጋራት የተካተቱት በበቂ መሥፈርት ተለይተው፣ “ይገባቸዋል” የተባሉ ቤተሰቦች ናቸው።

ከማዕድ ማጋራት ባሻገር ሕፃናት ተወልደው እዚህም እዛም የሚጣሉ አሉ። በፍጥነት ወደ ሕፃናት ማሳደጊያ ክፍላችን እንወስዳቸዋለን። ቀጥሎ የከተማዋን ነዋሪና ባለሀብቱን በማሳመን ከቻሉ ልጆቻቸው አድርገው ወስደው እንዲያሳድጓቸው፣ ያ የሚከብዳቸው ከሆነ ደግሞ በሕፃናት ማቆያዎቻችን ውስጥ የሚስፈልጋቸውን ወጪ እንዲሸፍኑ በማድረግ ለሕፃናትም የተሻለ ሁኔታ እየተፈጠረ እንዳለ በዚሁ በሰው ተኮር እንቅስቃሴዎቻችን ውስጥ ማንሳት ይቻላል።

**ዘመን፡- የአዲስ አበባን የኢኮኖሚ ዐቅም ከማሳደግ አንጻር ምን ምን ሥራዎች እየተሠሩ ነው ? ምን ዓይነት ለውጥስ መጣ ?**

**ክብርት ከንቲባ አዳነች፡-** አዲስ አበባ ለሀገራችን በአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት ዕድገት /ጂዲፒ/ የምታደርገው አስተዋፅኦ እጅግ ትልቅ ነው። ዋና የኢኮኖሚ ማዕከል ናት። ከፍተኛ የንግድ እንቅስቃሴ ያለባትና ወጪ ገቢ እቃዎችም የሚንቀሳቀሱባት ከተማ ናት። ከዚህ አንጻር አንደኛ ይኼን ሚናዋን ለማሳደግ ምቹ ሁኔታ መፍጠር አለብን በሚል መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ወደ ባለሀብትነት እንዲያድጉ የማድረግ ሥራዎችን ሠርተናል። አዲስ አበባ

> የሰው ተኮር ሥራችን ዓላማ የተቸገሩ የከተማ ነዋሪዎች ከገቢ የሚካፈሉ፣ ከልማቱ የሚቋደሱ እና ፍትሐዊነት የነገሠበት ከተማ ማድረግ አለብን የሚል ነው። የምንሠራው ለሰው ነው።

ለመጀመሪያ ጊዜ በኢንዱስትሪ ፓርክ ደረጃ የማምረቻና የመሸጫ ሥፍራዎችን መገንባት ችላለች። 90 ሄክታር መሬትና  አንድ ቢሊዮን ብር መድበን ኢኮኖሚዋን እና የማምረት አቅሟን ለማሳደግ እየሠራን ነው።

ሁለተኛ ትልልቅ ሜጋ ፕሮጀክቶችን እየገነባን ነው። እነዚህ ሜጋ ፕሮጀክቶች ሚናቸው ትልቅ ነው። በአንድ በኩል ቱሪዝምን በመሳብ የሀገር ውስጥ ጎብኚ ቁጥር ከፍ እንዲል በማድረግ ገቢን ይጨምራሉ፣ የውጪ ጎብኚዎችን ፍሰት በመጨመርም የውጭ ምንዛሬ ያስገኛሉ። በሌላ በኩል ትልልቅ የሥራ ዕድል እየፈጠሩ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴውን ያሳልጣሉ። የዓድዋ ሙዚየም ፕሮጀክትን ካየነው ነገ የሚፈጥረው ብቻ ሳይሆን ዛሬ የፈጠረውም የሥራ ዕድል በኢኮኖሚው ውስጥ ትልቅ ሚና ያለው ነው። ነገ ደግሞ ትልቁ የሀገራችን የመስሕብ ማዕከል ሆኖ እንደሚያገለግል ምንም ጥርጣሬ የለንም።

በክቡር ጠቅላይ ሚኒስትራችን ድጋፍ የተሠሩትን አንድነት፣ ወዳጅነት፣ ወንድማማችነትና እንጦጦ ትልልቅ የመስህብ ማዕከሎች ሆነዋል። አዳዲስ እየጨመርንም ነው የአለነው። ከተማዋን ከማጽዳትና ከማስዋብ ጋር አያይዘን የምንሠራው ሥራ ኢኮኖሚውን በማነቃቃት በኩል ጉልህ ሚና አለው። ወደ ከተማዋ መጥቶ መዋዕለንዋይን የማፍሰስ ፍላጎት እየጨመረ ነው ፤ የግል ግንባታዎች ብቻ ሳይሆኑ ፋብሪካዎች እና ኢንዱስትሪዎች በጣም ተነቃቅተዋል። እነዚህን ደምረን ስናይ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴውን ዕድገት በግልጽ እንመለከታልን።

የኢኮኖሚ እንቅስቃሴውን ለማሳደግና ለመደገፍ አሠራር እያዘመንን ነው። በዚህ ረገድ ቅድሚያ የሰጠናቸው ዘርፎች አሉ። ለምሳሌ፡- የገቢ አሰባሰቡ ዲጂታል እንዲሆን በኢ-ታክስ ጀምረን አሁን በቴሌ ብር እየሆነ ነው ያለው። ድካምን እየቀነስን በቀላሉ ሰው ከቤቱ ሆኖ የንግድና የግንባታ ፈቃድ ማግኘት የሚችልበትን ሥርዓት እየዘረጋን ነው። ይሄ የንግድ ሥርዓቱን በማሳለጥ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴውን ፈጣን ያደርጋል።

በቅርብ ጊዜ የጀመርናቸውና በፍጥነት እንሠራቸዋለን ብለን ለሕዝባችን ቃል የገነባናቸው ፕሮጀክቶችን የኢኮኖሚ



“

**ትልልቅ ሜጋ ፕሮጀክቶችን እየገነባን ነው። እነዚህ ሜጋ ፕሮጀክቶች ትልልቅ ሚና አላቸው። ቱሪዝምን በመሳብ የሀገር ውስጥ ጎብኚ ቁጥር ከፍ እንዲል በማድረግ ገቢን ይጨምራሉ፣ የውጪ ጎብኚዎችን ፍሰት በመጨመርም የውጭ ምንዛሬ ያስገኛሉ**

እንቅስቃሴዋን ማሳደጊያ ናቸው። የአፍሪካ መስኮት ብለን ወደ 84 ሔክታር መሬት ላይ ቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ አካባቢ የጀመርነው ፕሮጀክት አንዱ ትልቅ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴውን የሚያሳድግ፣ ቱሪዝምን የሚጨምር ነው። በቅርቡ የተፈራረምነውና ይፋ የአደረግነው «አዲስ ቱሞሮ» ፕሮጀክትም ሌላው ልዩ የኢኮኖሚ ዞን ነው። አዲስ አበባን አዲስ ገጽታ ሊያላብሳት የሚችል የአዲስ አፍሪካ ኮንቬንሽን ሴንተር ለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ላይ የመጀመሪያውን ምዕራፍ ፕሮጀክት እየጨረስን ነው። አዲስ አበባ ከተማ ለንግድና ለኢግዚቢሽን ትልቅ የስበት ማዕከል ነች። በተለይ ለአፍሪካውያን የትኩረት ማዕከል እንድትሆን፤ በከተማችን አሉን የምንላቸው ዲፕሎማቶች፣ የእንግዳና የዓለም አቀፍ ተቋማት እንቅስቃሴዎች መሸመት ሲፈልጉ ወይም መዝናናት ሲፈልጉ ከአዲስ አበባ ወጥተው ነው የሚሄዱት። ነገር ግን በዶላር ወይም በውጭ ምንዛሪ ገቢያቸውን የሚያገኙት እዚህ እየሠሩ



# “አዲስ አበባ የኢትዮጵያ መልክ ናት”

ነው። ወጪውን የሚያወጡት ግን ሌላ ሀገር ነው። አዲስ አበባ የዚያን ዓይነት አገልግሎት ስላልገነባች ነው፤ ይሄ ገብቶናል። ስለገባንም በፍጥነት እየገነባን ነው።

የአዲስ አበባን አጠቃላይ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በአደገው ገቢዋ መግለጽ ይቻላል። የአዲስ አበባ ዓመታዊ ገቢ በ2010 ዓ.ም. 30 ቢሊዮን ብር ነበር፤ ዛሬ 140 ቢሊዮን በጀተን እየሠራን ነው። በ2015 ዓ.ም. ብቻ ወደ 109 ቢሊዮን ብር መሰብሰብ ችለናል። ኢኮኖሚው ከሚያመነጨው አንጻር በጣም ገና ነን። በትክክል የንግድ እና የገቢ አሰባሰብ ሥርዓቱን ፍትሐዊ ካደረግን፣ ሥራችንን ውጤታማና ቀልጣፋ ካደረግን ከዚህ በላይ ማሳካት እንችላለን። ትልቁ ሀገራዊ ገቢ የሚሰበሰበው ከአዲስ አበባ ነው። አዲስ አበባ ግብር የምትሰበስበው ከግለሰብ ግብር ከፋዮች ነው። የገቢዎች ሚኒስቴር ደግሞ አጠቃላይ ከተቋማት አዲስ አበባ ላይ ገቢ ይሰበስባል። ሀገራዊ የገቢ ዕድገቱን ስናየው ዋናው ማዕከሉ አዲስ አበባ ላይ ነው።

**ዘመን ፡- የከተማዋ ገቢ በአስቀመጡት ልክ ከተገለፀ በጀቱስ እንዴት ይታያል?**

**ክብርት ከንቲባ አዳነች፡-** የአዲስ አበባ ገቢና የአዲስ አበባ በጀት ሁል ጊዜ የተጣጣመ ነው። ምክንያቱም አዲስ አበባ የምትተዳደረው በራሷ ገቢ ነው። የተወሰኑ ትንንሽ የውጭ ርዳታዎች በአንዳንድ ፕሮጀክት ላይ ይገኛሉ። ነገር ግን እዚህ ግባ የሚባሉ አይደሉም። ለማሳያ ያህል የ2010 ዓ.ም እንኳን ብንወስድ የከተማዋ ገቢ 30 ቢሊዮን ብር ነበር፤ ወጪዋ ደግሞ ወደ 32 ቢሊዮን ብር አካባቢ ነበር። ከዚያ በኋላ ካየነው ወጪና ገቢዋ እኩል ነው። በሚቀጥለው ዓመትም በ2016 ዓ.ም. 140 ቢሊዮን ብር ለተለያዩ ፕሮጀክቶች ዐቅደናል። ከዚያ ውስጥ ከ80 ቢሊዮን ብር በላይ የሚሆነው ለካፒታል ፕሮጀክት እንዲሆን፣ አስተዳደራዊ ወጪያችንን እየቀነስን፣ ብክነት እየቀነስን ለዘላቂ ልማት በጀታችን እንዲውል እያደረግን እየመራን ነው ።

**ዘመን፡- በአጠቃላይ የለውጥ ሥራችሁ ውስጥ ያጋጠሙ ፈተናዎች ምንድን ናቸው? ፈተናዎቹስ እንዴት ታለፉ?**

**ክብርት ከንቲባ አዳነች፡-** በዚህ የለውጥ ዘመን ውስጥ ያጋጠመን ፈተና እንደ ሀገር የሁሉም የጋራ ፈተና ነው በሚል መግለጽ ይቻላል። አዲስ አበባ ላይ ግን የተለየ ጫና ነበረው። አንዱ እና ዋናው ፈተና ነገሮችን በትክክለኛው ገጽታቸው ከመግለጽ ይልቅ ሆን ብሎ የማዛባት ስትራቴጂና ስልት በመከተል ብዥታ በመፍጠር ብዙ ጉዳቶችን ማስከተሉ ነው። እውነትን ከመግለጽ ይልቅ እውነት የሚመስሉ ሐሰተኛ መረጃዎችን በማዛባት በብዙ መንገድ በተለያዩ ሚዲያዎች፣ በሕዝብ ላይ የሚደረጉ ዘመቻዎች የተጋረጡት ተግዳሮትና ፈተና ሆነው የተከሠቱበት ሁኔታ ነው። እኛም ወደ እዚህ ሐላፊነት ስንመጣ አንዱ የጠበቀን ፈተና አመራሩ ጭምር በተለያየ ጎራ ቆሞ በተለያየ ቡድንተኝነት ውስጥ የሚታይበት ሁኔታ ነበር።

ይኼ እንዲሁ የመጣ ፈተና አይደለም። አጠቃላይ እሳቤው እውነታን የማዛባት፣ መልካም ነገሮችን የማጠልሸት፣ የሚሠራውን ሥራ በትክክለኛው ገጽታ ሳይሆን በተዛባ ገጽታ ሕዝቡ ጋር እንዲደርስ ማድረግ

ፍላጎት የፈጠረው ነው። የእኛ ኮሙኒኬሽን ስልትና ብቃት ደግሞ በዚያ ልክ ዝግጁ ሆኖ ተመጣጣኝ ያልሆነበት፣ ሕዝቡም፣ አመራሩም ይሄ ሁኔታ ጫና የሚያደርስበት መሆኑ አንዱ ተግዳሮት ሆኖ የተገለጠበትና ያለፍንበት ሁኔታ አለ። ዛሬም ተግዳሮቱ ያለ ቢሆንም በበርካታ የሕዝብ ተሳትፎ፣ ከሕዝብ ጋር ባደረግናቸው ውይይቶች፤ በአመራሩ መካከል በመነጋገርና በመወያየት የማይረባውን እና ጊዜ የሚያባክንብንን ወደ ጎን እየተውን ጊዜያችን ሳያልፍና ሳይባክን ዐሻራችንን እናስቀምጥ በሚል መግባባት ደርሰናል። ሐላፊነት ላይ እስከአለን ድረስ ምን አዲስ ነገር እንጨምራለን? ለትውልድ የምናሻግረው ምንድን ነው? የሚለው ጉዳይ ገዢ ሊሆን ይገባዋል እንጂ በማይረባና በማያዛልቀን ነገር ጊዜያችንን ማባከን ተገቢ እንዳልሆነ ተማምነን ጥሩ ጥሩ የሆኑ ሥራዎች ተሠርተዋል። ሁለተኛው ያጋጠመን ፈተና ትንሽ ሠርቶ መርካት ነው። ጉዟችን በጣም ሩቅ ነው፤ መዳረሻችን ብልጽግና ነው ብለናል። የምንሠራው ለመበልጸግ ነው። ጥቂት የሚቆጠሩ ሥራዎች ሠርተን፣ ዘንድሮ ዕቅድ ተከናወነልን፣ ጥሩ ተፈፀመልን ብለን ረክተን ዕረፍት ዓይነት ስሜት እንዲሰማን የሚያስችል ሁኔታ ውስጥ አይደለንም የአለነው። መወዳደር አለብን፤ የአፍሪካ ሕብረት መቀመጫ እና ሦስተኛዋ የዲፕሎማቲክ ማዕከል በመሆናችን፣ አጠቃላይ ተወዳዳሪነታችንን የሚፈታተኑ ነገሮች እየመጡ ነው። በደምብ ጥረን ግረን ካልያዝን በስተቀር ይኼም ነገ ሊጠፉ የሚችል መሆኑን ታሳቢ ያደረገ ሥራ መሥራት አስፈላጊ ነው።

የሕዝቡን የኑሮ ጫና ከማቃለል አንጻር ገና ብዙ መሥራት አለብን። የሕዝባችንን ብልጽግና ማረጋገጥ ነው ዓላማችን፤ ግባችንም መበልጸግ ነው። ስለዚህ እሱን ታሳቢ ካደረግን በቀላሉ መድከም አይገባንም፤ ብዙ ወደ ርካታ ሊያስኬድ የሚችልም ውጤት ላይ አይደለንም። “ድሎቻችን መሥራት እንደምንችል፣ ተግዳሮቶችን ማለፍ እንደምንችል ማሳያ ብቻ ናቸው” እያልን ነው በጥቂት ከመርካት ጋር ያሉትን ፈተናዎች ያለፍናቸው እንጂ የከተማው አመራር ቶሎ ብሎ ወደ ርካታ የመምጣት ፈተናዎችና ተግዳሮቶች ነበሩብን።

በሌላ በኩል ደግሞ ሌብነትና ብልሹ አሠራሮችም ተግዳሮቶች ነበሩ፤ አሁንም ተግዳሮት መሆናቸው ቀጥሏል ብለን ነው የምንገልጸው። አመራር ሆኜ በሌላ ቦታ ከሠራሁባቸው ይልቅ፤ አዲስ አበባ መስተዳድር ሌብነት የተለመደ ሆኖ ወደ ታች ሠርጿል። ለአገልግሎት መማለጃ መቀበል፣ ምስጋናን በቃል ሳይሆን በዓይነት ወይም በገንዘብ ለመቀበል መፈለግ ያጋጠመን ተግዳሮት ነው። “አገልግሎት በነጻ መስጠት አለብን” የሚለው ሐሳብ በዋናነት መሠረት መያዝ የሚኖርበት በሲቪል ሰርቫንቱ ቢሆንም ለዚህ አስተሳተብ ተግበራዊ መሆን የመሪዎቹ ሚናም ወሳኝ ነው። መሪዎቹ ለዚህ ቆርጠው የሚታገሉ ከሆነ እስከ ታች ድረስ እየለወጡ መሄድ ይቻላል። በዚህ በኩል ያሉትን ብልሹ አሠራሮች፣ ብልሹ አስተሳሰቦችና ተግባሮች መቀየር ላይ ብዙ ርብርብ ማድረግ እንዳለብን፤ ጫናውም ቀላል እንዳልሆነ ተረድተን እየሠራንበት እንገኛለን። ፈተናው የነበረ እና የተሻገረ ቢሆንም ዛሬ በትናንትናው ልክ አይደለም። ዛሬ አዲስ አበባ ላይ መሬት በሔክታር አይወሰድም፤ አዲስ አበባ ላይ ባለቤቱ ፈልጎ በድብቅ ካላደረገው በስተቀር የተለየ ጫና አሳድሮ ብር ካልከፈልከኝ በስተቀር ላገለግልህ አልችልም ማለት አይችልም። ባለቤቱ መጥቶ ማጋለጥ እስከቻለ ድረስ ተገቢውን አገልግሎት አግኝቶ ተጠያቂነት መስፈን የሚችልበትን አሠራር ዘርግተናል። ተግዳሮቱ ግን ዛሬም አለ። መተባበር፣ መተጋገዝ የሚፈልግ ጉዳይ ነው።

ሦስተኛው ተግዳሮት የኑሮ ውድነት ነው። የገበያው መዛባት በአንድ በኩሉ አርቴፊሻል የሆነ የዋጋ ጭማሪ በሌላ በኩል የከተማው የሕዝብ የኑሮ ጫና ሰፋ ያለ መሆኑ ነው። አራተኛ የግብይት ሰንሰለቱ ያልተስተካከለ መሆኑና ሌሎች ምክንያቶች ተጨማምረው አንድ ላይ የኑሮ ውድነቱን ትልቅ አደረጉት።

ይኼንን ተግዳሮት ለማለፍ የተለያዩ ስልቶችን ተጠቅመናል። አንደኛ ምርት ወደ አዲስ አበባ ከተማ በስፋት በማስገባት ሰው ሠራሽ ጭማሪውን ለመዋጋት ያደረግነው ጥረት ብዙ ውጤት አስገኝቷል። ወደ 179 የሚሆኑ የእሑድ ገበያዎችን በመክፈት እሑድና ቅዳሜ ታክስ የማይደረጉ ከነጋዴው ዋጋ ጋር ሲተያዩ ከ20 እስከ 30 በመቶ ልዩነት ያላቸው እንዲሆኑ በማድረግ ሕዝቡ እንዲሸምት ተደርጓል። ሕዝቡ ቅዳሜና እሑድ መሸመት እንዲችል ዕድል ፈጥረናል። አሁን ደግሞ አምስት የሚሆኑ ትልልቅ የገበያ ማዕከላት በአዲስ አበባ መግቢያ በሮች ላይ እየተገነቡ ነው። አንዱን አጠናቀናል። ሌሎቹ ሰሞኑን ተጠናቀው ወደ ሥራ ይገባሉ።

ሕዝብ በልቶ ለማደር እንዳይቸገር ማድረግ የቻሉ የከተማ ግብርና ሥራዎች ተሠርተዋል። በሌማት ትሩፋት ደግሞ ከተማዋ ራሷን እየቻለች ነው። አሁን የጀመርናቸው የእንጀራ ፋብሪካዎችም አሉ። በለሚኩራ ተጠናቆ ሥራ ጀምሯል፤ ጉለሌ ላይ ሁለተኛው የእንጀራ ፋብሪካ በቅርቡ ይጠናቀቃል። ገበያው ላይ እንጀራ የሚሸጥበትን ዋጋ አጥንተናል። በሙሉ ዐቅም እንጀራ ወደ ማቅረብ ሲገባ የእንጀራውን ዋጋ ማስተካከል፣ ገበያው ላይ ጣልቃ የምንገባበት ዕድል ነው እየፈጠርን የአለነው። እነዚህ ሥራዎች የሥራ ዕድልም ይፈጥራሉ፣ ሠርተው የሚበሉ ዜጎቻችን በስፋት እንዲመጡ እና ዕድል እንዲያገኙ ያደረገ ነው።

በአጠቃላይ በመተባበር በጋራ በመሆን ሠራተኝነትን፤ ማገልገልን፣ ተግቶ መሥራትን፣ አለመሥነፍን፣ ሃያ አራት/ሰባት የምንለውን ደጋግመን መመሪያችንና መርሐችን እያደረግን እንደዚህ ያሉ ተግዳሮቶችን የማለፍ ስልት ተከትለን ነው እየሠራን የአለነው።

**ዘመን፡- ከይዞታቸው ተፈናቅለው የነበሩ በአዲስ አበባና ዙሪያዋ ያሉ አርሶአደሮች የተሻለ ኑሮ እንዲኖራቸው ከማድረግ አንጻር የተከናወኑ ተግባራት ምንድን ናቸው?**

**ክብርት ከንቲባ አዳነች፡-** አዲስ አበባ በአሁኗ ስፋት ከመገለጧ በፊትም ዳርዳሯ ላይ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሥር የሚተዳደሩ አርሶ አደሮች አሉ። ነገር ግን ከተማዋ እየሰፋች በሄደች ቁጥር ተገቢው ትኩረት አልተሰጣቸውም። አርሶ አደሮች ምን ይሆናሉ? እንዴት ይኖራሉ? እንዴት ኑሯቸውን ይመራሉ? ከከተማዋ ጋር የሚያድጉትስ እንዴት ነው? የሚል እሳቤና ስትራቴጂ አዲስ አበባ ላይ አልነበረም። ይህ የመሪዎችና የአፈፃፀም ስሕተት ነው። በዚህ ስሕተት ምክንያት ብዙ ቁስሎች፣ ጫናዎችና ትልልቅ ጉዳቶች ደርሰዋል። አሁን



ክብርት ከንቲባ አዳነች አቤቤ

እያስተካከልን የአለነው ያንን ነው።

ይህ ችግር እንዲፈታ የለውጡ አንዱ መሠረታዊ ጥያቄ ሆኖ ሕዝቡን ያንቀሳቀሰ በመሆኑ ምክንያት በትኩረት ሠርተንበታል። አንደኛ አርሶ አደሮቹ በተገቢው ሁኔታ መሬታቸው ላይ በባለቤትነት፣ የመጠቀም መብታቸው ጭምር ተረጋግጦ ለልማት በሚፈለግበት ጊዜ ሕግና ሥርዓቱን ጠብቆ መሬታቸውን ለልማት ማዋል የሚችሉበት፣ ልማቱ በሚሠራበት ጊዜ ደግሞ አርሶ አደሮቹ ኑሯቸውን በቀጣይነት የሚመሩበት ምን መሠረታዊ ነገር እንሥራላቸው? የሚለውን ታሳቢ ያደረገ ሥራ ነው እየተሠራ ያለው። አቃቂ ላይ የተሠራው የአርሶ አደር ግብርና ልህቀት ማዕከል ይህንን ያሳየናል። ትልቅ የግብርና ልህቀት ማዕከል በኢንዱስትሪ ፓርክ ደረጃ ሊገለጽ የሚችል ሠርተናል። እዛ ውስጥ አርሶ አደሮቹ ተደራጅተው ከብት ማደለብ የሚችሉበት፣ የወተት ምርትን ለከተማዋ ጭምር ትልቅ ፀጋ ሊሆኑ የሚችሉበት፣ የዶሮ፣ የእንቁላል ተመሳሳይ ማቀነባበሪያ ጭምር መሥራት የሚችሉበት፣ ከተማዋ ላይም ንጹህ አቅርቦት በሥርዓቱ ሊቀርብ የሚችልበት ዕድልን የፈጠረ አርሶ አደሮቹም ደግሞ ሕይወታቸውን በቀጣይነት የሚመሩበት ሥራ ተሠርቷል።

እስካሁን ድረስ በመረጃ በአረጋገጥነው መሠረት ወደ አምስት ሺህ የሚደርሱ አርሶ አደሮችን በመሬታቸው ላይ ተገቢውን የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር እንዲያገኙ ማድረግ ተችሏል። ከተማው ውስጥም የመኖሪያ ቤት ጭምር ማግኘት እንዲችሉ፣ ከከተማዋ ጋር እንዲያድጉ፣ ከተማዋ ስትሰፋ መጣችልን፣ ከተሜነት መጣልን፣ ዘመናዊነት መጣልን የሚሉበት እንጂ፤ መፈናቀላችን ነው፣ መጥፋታችን ነው የሚል ስጋትና የጎሪጥ መተያየት መቅረት አለበት ብለን የሠራነው ሥራ ውጤታማ ሆኗል ማለት ይቻላል።

**ዘመን፡- የዓለም የዲፕሎማሲ ማዕከል የሆነችው አዲስ አበባ በአለፉት ዓመታት በርካታ ዕውቅናዎችን አግኝታለች። የዕውቅናዎቹ አንድምታ ምንድነው ?**

**ክብርት ከንቲባ አዳነች፡-** አዲስ አበባ ባላት ሚና ጭምር ግንኙነቷን



አርሶ አደሮች በመሬታቸው ላይ ተገቢው የባለቤትነት ማረጋገጫ እንዲያገኙ ተደርጓል

> አምስት ሺህ የሚደርሱ አርሶ አደሮችን በመሬታቸው ላይ ተገቢውን የባለቤትነት ማረጋገጫ እንዲያገኙ ማድረግ ተችሏል። ከተማው ውስጥም የመኖሪያ ቤት ጭምር ማግኘት እንዲችሉ፣ ከከተማዋ ጋር እንዲያድጉ፣ ከተማዋ ስትሰፋ መጣችልን፣ ከተሜነት መጣልን፣ ዘመናዊነት መጣልን የሚሉበት እንጂ፤ መፈናቀላችን ነው፣ መጥፋታችን ነው የሚል ስጋትና የጎሪጥ መተያየት መቅረት አለበት ብለን የሠራነው ሥራ ውጤታማ ሆኗል

በትልቁ ማጠናከር አለባት። ከተማዋ በቀደመው ጊዜም የተለያዩ ግንኙነቶች ነበሯት። ነገር ግን በአለፉት የለውጥ ዓመታት በተለይ 2014 እና 2015 ዓ.ም የነበሯትን ግንኙነቶች ከዓለም አቀፍ ከተሞች ጋር በምናይበት ጊዜ እጅግ በጣም ጎልቷል። በቅርብ ጊዜ በምገባ ከዓለም ከተሞች ጋር ተወዳድረን አንደኛ ወጥተን የተሸለምንበትን እንዲሁም የከተማዋን ቆሻሻ በምናስወግድበት ጊዜ በካይ ጋዝን እንዳያመነጭ አድርገን የምናስወግድበት ሥርዓት ላይ በጣም አደጉ ከሚባሉ ትልልቅ ከተሞች በላይ ዕውቅና ያገኘንበት ነው። ከቅርብ ጊዜዎቹ እነዚህን መጥቀስ ይቻላል። በተመሳሳይ ሌሎች በርካታ ዕውቅናዎች አግኝተናል። ሽልማቶቹ እና ስጦታዎቹ ከተለያዩ ሀገራት ጋር ትብብርን፣ አብሮ መሥራትን፣ ልምድ መቀያየርን፣ ግንኙነታችንን ማጠንከርን እናበርታ፤ እናጠናክር ያሉበት ትልልቅ ስጦታዎችን የሚያመላክቱ ናቸው። እነዚህን ስንመለከት የአዲስ አበባ ተፈላጊነት፣ የስበት ማዕከል መሆን እየጨመረ እንደሆነ በደምብ መናገር ይቻላል።

**ዘመን፡- "አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ተምሳሌት ነች" የሚሉ ወገኖች አሉ። በዚህ** አባባል ይስማማሉ?

ክብርት ከንቲባ አዳነች፡- በእርግጥም ነች። አዲስ አበባ የኢትዮጵያ መልክ ናት። ሁሉም ኢትዮጵያውያን ቤቴ ብለው የሚኖሩባት የሁላችን ከተማ ናት። የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊ እንቅስቃሴም ማዕከል ነች። የዲፕሎማሲውም ማዕከል ነች። የመገናኛ ብዙኃኑ አጠቃላይ እንቅስቃሴም ማዕከል ነች።

**ዘመን፡- ነገዎን ይንገሩን እስኪ? ስለሚመሯት ከተማ መዳረሻ ህልምዎ ምንድን ነው?**

**ክብርት ከንቲባ አዳነች** ፡- አዲስ አበባ ብዙ ሊያበለጽጓት የሚችሉ ሀብቶችና ዕቅሞች ያሏት ከተማ ናትና በልጽጋ ማየት እፈልጋለሁ። አዲስ አበባ ተወዳዳሪ ከተማ ሆና በዓለም ላይ ደምቃና ታውቃ እንድትታይ እፈልጋለሁ። ይህንን አመራሮቻችን ጭምር እንዲሰንቁትና እንዲያልሙት የሚያደርግ ሥራ እየሠራን ነው። "ለምን ህልም ነው የምንሠራው? የምንኖረው ? ዝም ብለን ደመወዝ ለማግኘት ነው የምንሠራው? አመራር ሆነን ተሽከርካሪ እና ቤት ስለሚሰጠን ነው የምንሠራው? ለምንድን ነው አመራር የሆንነው? በተቀመጥንበት ወንበር፣ የምንመራውን ተቋም ከየት ወዴት ነው የቀየርነው? ሁለት ዓመት በመኖሬ ምን ሠራሁ ? ብሎ አመራሩ ራሱን እንዲጠይቅ ይፈለጋል።

እኔ የአዲስ አበባ ከንቲባ ከሆንኩ ሦስት ዓመቴ ነው። "ምን ቀየርኩ?" የሚለውን ለኔ ለግሌ ሌጋሲ ብቻ አይደለም የምቆጥረው፤ አዲስ አበባ ላይ ነገ እኔ ብኖርም ባልኖርም በእኔ አመራርነት የመጣው ለውጥ ምንድን ነው ? የሚለውን ነው መቁጠር የሚያስፈልገው። ይኼን ያህል ብቻ ነበር መሥራት የነበረብኝ? ለምን ከዚህ በላይ አልሠራሁም? ብለን ህልም፣ ስንቅ፣ ቁጭት መያዝ ያስፈልጋል። እንደዛ ሲሆን ነው ትልቅ ሥራ መሥራት እና ትልቅ ማለም የሚቻለው። እንዲህ ዓይነት ህልም ደግሞ ሲታለም ሰውን ይዞ ነው።

ታች ያለውንም አይቶ ይዞ አብሮ መሆን አለበት። የሚሠራው ሥራ ለእኔ ነው፣ ፀጋ ነው፣ ሕይወቴን እየቀየረው ነው። ከዚህ በላይ ቢሠራ ከዚህ በላይ እቀየራለሁ የሚል በጎ አስተሳሰብ አብሮ እንዲዳብር እየተደረገ መሄድ አለበት። እነዚህ ተደማምረው አዲስ አበባ በዓለም ላይ ብቁና ተወዳዳሪ ከተማ መሆን እንድትችል ደግሞ መበልጸግ አለባት። የዜጎቿ ሕይወት መበልፀግ አለበት። አኗኗራችን፣ አስተሳሰባችን፣ አሠራራችን፣ ታታሪነታችን፣ ማደግ አለበት። እንደ ዓድዋ ሙዚየም ከተማዋ ላይ የሚታዩ ፕሮጀክቶችና ሥራዎች ዘላቂ ሆነው ለትውልድ የሚተላለፉ ዐሻራዎች እንዲሆኑ ሌት ተቀን መሥራት አለብን። ትላንት ዝም ብለን ታሪካችን ነው ብለን ዓድዋን ስንኮራበት ወይም አንዳንድ ጊዜም ስንረሳው / ዓድዋ የማይከበርበትን ጊዜ እናስታውሳለን/ እንደዛ ሆነን ሳይሆን የትላንትናው ጥሪት ወይም ደግሞ የትላንትናውን ወረት ይዘንና የዛሬውን ጥረት ጨምረንበት ነጋችንን አልመን አዲስ አበባን ማበልጸግ እንችላለን የሚል ህልም ሰንቀን ነው እየሠራን የአለነው። ይህ ለዛሬው ትውልድ ጥቅም፤ ለነገው ትውልድ ደግሞ ዐሻራ ማስተላለፍን ማዕከል ያደረገ ነው።

**ዘመን፡- ክብርት ከንቲባ ለነበረን ቆይታ እጅግ አድርገን እናመሠግናለን።**

**ክብርት ከንቲባ አዳነች አቤቤ፡-** እኔም በጣም አመሰግናለሁ።



# ባዶ የምሳ ኽቃ

## እና ሌሎች ተረቶች



# ባዶ የምሳ እቃ እና ሌሎች ተረቶች

እውነተኛ ታሪክ ነው። በብዙዎች ጓዳ፣ በሕፃናት እና አዳጊዎች፣ በደጋግ እናቶች አእምሮ ውስጥ ትዝታው ተቀርጾ የሚኖር ታሪክ። የንጋት ሰቆቃዎች፣ የኑሮ ዘባተሎ፣ የድህነት ታሪክ....የባዶ የምሳ እቃ እና የባዶ ሆድ የድብብቆሽ ሰቀቀናም "ጨዋታ"፣ የባዶ የምሳ እቃ እና ሌሎች ተረቶች እውነተኛ ታሪክ። ልብ ወለድ ያልሆነ የተኖረ የአዳጊዎች እና የወላጆች ትዝታ።

የአውራ ዶሮው ጩኸት፣ የወፎች ጫጫታ የመንጋቱ ዜና አብሳሪ ድምፆች ናቸው። አዲስ አበባ ላይ የመኪናው፣ የወያላው፣ የአዛን፣ የቅዳሴው፣ የሰው ግርግር እንደየአካባቢው መንጋቱን ያበሥራሉ። ገጠር ይሁን ከተማ የማይለወጠው ጎሕ ይቀዳል፤ ጨለማ ለብርሃን ቦታውን ይተካል። ንጋት፣ ተስፋ፣ አዲስ ቀን ይሆናል።

አዳጊዋ መክሊት [ስሟ የተቀየረ] መሽቶ በነጋ ቁጥር በትናንሽ፣ ብሩህ ዐይኖቿ ተስፋ የቆረጠ የእናቷን ፊት፣ እንጀራ አልባውን ሞሰብ ማየት የዘወትር የንጋት ተግባሯ እንደነበር ትናገራለች። በነጋ ቁጥር የእሷ እና የችግረኛ እናቷ የትምህርት ፍላጎት እየገፋት ታስሮ ያልተፈታውን የምሳ እቃ አንጠልጥላ ለብዙ ቀናት እንደጓደኞቿ አስመስላለች። ቀኑ ሲገፋ ርኃቡ ሲጠናባት በሚታይባት ድካም እና እንቅልፍ ይታወቅባታል። በዚህ ጉዞ እያለፈች እሷ የትምህርት ቤት ምገባ መጀመሩ የባዶ የምሳ እቃ ሸክሙ እና የባዶ ሆድ የትምህርት ቤት ውሎዋ ተረት ሊሆን በቅቷል። መሰሎቿ ድካሙ አሸንፏቸው ትምህርታቸውን እንዲያቋርጡ ተገድደዋል።

አዲስ አበባ በጉያዋ የደበቀችው፣ ደብቃ ያኖረችው ሰው የሚሻ የሰው ችግር ብዙ ነው። ይህንን የተረዳው ከተማ አስተዳደሩ ከተማዋ የምታመነጨውን የኢኮኖሚ ዐቅም የተቸገሩትን ለመርዳት እንዲያስችል በዕቅድ ተሠርቷል። ያ በመሆኑ የታወቁት ችግሮች ተፈትተዋል። የብዙ ወላጆችን እና አዳጊዎችን ሥነልቦና ከርኃብ በላይ የጎዱት የባዶ የምሳ እቃ ታሪኮች ተረት ሆነዋል። ከተማው ከሚያመነጨው ገቢ ውስጥ እስከ 8 ቢሊዮን ብር በመመደብ ሰው ተኮር የልማት ሥራዎች እየተሠሩ ነው። ተማሪ ተስፋ ካሳሁን (ስሙ የተቀየረ) የሐምሌ 1967 የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት የስምንተኛ ክፍል ተማሪ ነው። ስለ ምገባው ለመናገር ምገባው ሳይመጣ በተማሪዎች ላይ ምን ያስከተለው ጉዳትና ተጽዕኖ ነበረ? ምገባው ከመጣ በኋላስ የተገኘው ጥቅም ምንድን ነው? ብሎ መናገር ያስፈልጋል በሚል ይጀምራል። የሱሉልታ ተማሪ ስለሆንኩኝ የኢኮኖሚውን ትቼው ጊዜና ጉልበት ላይ ያለውን ስናገር ቤተሰብ ቁርስና ምሳ አዘጋጅቶ ምሳ ቋጥሮ ከሰጠኝ በኋላ ትራንስፖርት ይዤ እስክመጣ የነበረው መሯሯጥ አድካሚና ጊዜ የሚፈጅ ነበር። ከዚህ በተጨማሪ ምሳው ከታሰረ የቆየ በመሆኑ ስበላው ለጤና ጥሩ አልነበረም። ሐምሌ 1967 ትምህርት ቤት ያለነው ተማሪዎች አብዛኞቻችን በዝቅተኛ ኑሮ ደረጃ ላይ ከሚገኙ ቤተሰብ የመጣን ስለሆንን ጠዋት ምግብ ሳንበላ የምንመጣ፣ አንዳንዴም ምሳ ላይቋጠርልን ስለሚችል በተዳከመ

"

...በዚህ ጉዞ እያለፈች ለእሷ የትምህርት ቤት ምገባ መጀመሩ የባዶ የምሳ እቃ ሸክሙ እና የባዶ ሆድ የትምህርት ቤት ውሎዋ ተረት ሊሆን በቅቷል። መሰሎቿ ድካሙ አሸንፏቸው ትምህርታቸውን እንዲያቋርጡ ተገድደዋል።



ሁኔታ ነበር ትምህርት የምንማረው። ምግብ የምንበላ እንኳን ቢሆን የተመጣጣነ ስላልሆነ ይደክመናል። ይህም ስለሆነ ትምህርት በአግባቡ ስለማንከታተል የትምህርታችን ውጤት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ያሳድር ነበር። አሁን ግን ምገባው ከመጣ በኋላ ቀጥታ ከአልጋችን እንደተነሣን ተጣጥበን ተዘገጃጅተን ከቤት እንወጣለን። ከዚያም ወደ ትምህርት ቤት ጉዞ በማድረግ እናቶች ያዘጋጁልንን ምግብ በትምህርት ቤቱ ውስጥ በመመገብ በንቁ ተሳትፎ ወደ መማሪያ ክፍላችን በመሄድ ትምህርታችንን እንከታተላን በማለት ለውጡን ያስረዳል።

ተማሪ ተስፋ ከምገባው ስለተገኘው ጥቅም ሲያስረዳ፤ በሳምንቱ ውስጥ አምስቱንም ቀን ንጽሕናው የተጠበቀ የተለያዩ የተመጣጠኑ ምግቦች ተዘጋጅተው ስለሚቀርቡልን፤ የድካም ሁኔታ የለብንም። ይህም ስለሆነ ትምህርታችን ላይ ከፍተኛ ትኩረት በማድረግ እንማራለን። ከምገባው በኋላ ብዙ ተማሪዎች በትምህርታቸው ከፍተኛ ውጤት ማስመዝገብ ችለዋል። ምገባው የቤተሰብን የኢኮኖሚ ጫናም መቀነስ ችሏል። የምገባ መርሐ ግብሩ መጀመር ቤተሰብ ለእኔ ለምግብ የሚያወጣው ስለቀነሰለት እንዲሁም ዩኒፎርም፣ ቦርሳ፣ ደብተር እና እስኪሪብቶ የመሳሰሉት በመንግሥት በኩል ስለሚቀርቡ ቤተሰብ ለእኔ ለትምህርት አጋዥ ለሆኑ ሌሎች ነገሮች ወጪ በማውጣት የበለጠ በትምህርቴ ላይ እንድተጋ አድርጎኝ ከበፊቱ በተሻለ ውጤት ያለው ተማሪ እንድሆን አድርጎኛል ብሏል።

የዚሁ መርሐ ግብር ተጠቃሚ የሆነቸው ተማሪ ዝናሽ ቻሌ ድካም ቀርቶ ንቃት፣ የውጤት ማሽቆልቆል ቀርቶ ጉብዝና፣ መራራቅ ቀርቶ መቀራረብ፣ አብሮ መመገብ፣ የፈጠረው አንድነት በትምህርታቸው ውጤታማ መሆናቸውን



ትናገራለች። ዝናሽ የምገባ መርሐግብር ለተማሪዎች የሰጠውን ጠቀሜታ ስታስረዳ "አንደኛ ትምህርታችንን በንቃት እንድንከታተል አድርጎናል። ሁለተኛ ከግል ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች ጋር ተወዳዳሪ አድርጎናል። በግል ትምህርት ቤት የሚገኙ ተማሪዎች ዘወትር የተመጣጠነ ምግብ አግኝተው ተመግበው ይቀርባሉ። ስለዚህ ትምህርታቸውን በሥርዓት መከታተል ይችላሉ። እኛ ደግሞ የምገባ ፕሮግራሙ ከመጀመሩ በፊት ሳንመገብ የምንመጣ ተማሪዎች ነበርን። ያ ድካም እንዲሰማን ስለሚያደርግ ክፍል ውስጥ እንተኛ ነበር። በትምህርት ቤታችን ምገባ ከተጀመረ በኋላ ትምህርታችንን በንቃት መከታተል ችለኛናል። በውጤት ደረጃም የተሻለ ውጤት እያስመዘገብን ነው።" ትላለች።

በሌላ በኩል በመንግሥት ትምህርት ቤት ተማሪዎች ወላጆች መካከል ያለው የኢኮኖሚ ልዩነት ይፈጥር የነበረው የሥነልቦና ጫና መቀረፉንም ትገልጻለች። ሁኔታውን የምታስረዳው፣ የምገባ ፕሮግራሙ ከመጀመሩ በፊት የተሻለ ገቢ ያላቸው ወላጆች ለልጆቻቸው ምሳ ቋጥረው ሲልኩ ሌሎቻችን ባዶ እጃችንን መጥተን እነሱን ነበር የምናየው። አሁን ግን የምገባ ፕሮግራም መጀመሩ በመካከላችን ልዩነት እንዳይኖር አድርጓል። በአንድ መሶብ የቀረበ እንጀራ እና አንድ ድስት ውስጥ የተሠራ



ወጥ ጓደኝነት ፈጥረን በአንድነት ነው የምንበላው። ይሄ ትንሿ ኢትዮጵያ ትምህርት ቤት ውስጥ እንድትፈጠር ያደርጋል። የተቀበልነውን ለየብቻ ሳይሆን በጋራ አድርገን አንድ ላይ መመገባችን ይበልጥ ወንድምና እኅትማማችነታችን እንዲጠናከርና እንድንዋደድ እያደረገን ነው ብላለች።

ከምገባ ባለፈ የትምህርት ቁሳቁሶች እና የደምብ ልብስ ይቀርብልናል የምትለው ዝናሽ፣ የሚያስፈልገን እስክሪቢቶ ይሰጠናል። ደብተርና  በተለይ በተመሳሳይ የጨርቅ ዓይነት አንድ ዓይነት የደምብ ልብስ ተዘጋጅቶልን መምጣቱ ትለቅ ትርጉም ያለው ነገር ነው። መንግሥት ይህን የደምብ ልብስ ማቅረብ ከመጀመሩ በፊት አንዱ ተማሪ አዲስ ሌላው ደግሞ አሮጌና የተቀዳደደ የደምብ ልብስ ለብሶ መምጣቱ ሰፊ ልዩነት ያመጣ ስለነበር የሥነልቦና እና የአእምሮ ጉዳት ያደርስብን ነበር። አሁን ግን በየዓመቱ አዲስ ዩኒፎርም ተቀይሮ ስለሚሰጠን በመካከላችን ምንም ዓይነት ልዩነት የለም ትላለች።

ዝናሽ ሐሳቧን የምትቋጨው ለሴት ተማሪዎች ስለሚሰጠው ልዩ ድጋፍ "እኔ ሴት ተማሪ ነኝና በሴትነቴ የሴቶች የንጽሕና መጠበቂያ ይሰጠኛል። ከዚህ በፊት የንጽሕና መጠበቂያ የምናገኝበት ዕድል ስላልነበረን ተፈጥሯዊ የሆነው ወርኃዊ ዑደት ሲመጣ በጣም እንቸገር ነበር። አሁን ግን ከአምስተኛ ክፍል በላይ ላለን ሴት ተማሪዎች በሙሉ የንጽሕና መጠበቂያ ይቀርብልናል። በተጨማሪም ዘንድሮ ባይቀርብልንም ከዚህ በፊት በነበሩት ሁለት ዓመታት ጫማና ቦርሳ ይመጣልን ነበር።" ስትል ምስክርነቷን በመስጠት ነው።

ከሦስት ዓመት በፊት መቶ ሺዎች የነበሩት ተማሪዎች ዛሬ ቁጥራቸው ከ700ሺህ በላይ አልፏል። ቁጥሩ በአዲስ አበባ ዙሪያ ያሉትን ስለሚጨምር ዘጠኝ መቶ ሺህ ተጠግቷል። አዲስ አበባ ዛሬ ላይ ቁጥራቸው የአንዳንድ የአፍሪካ ሀገራትን ሕዝብ ቁጥር የሚያክሉ ተማሪዎችን በቀን ሁለት ጊዜ ትመግባለች።

የምግብ ዝግጅት ሂደቱም አብዛኛው የተማሪ ወላጆች እናቶች በብዛት የሚሳተፉባቸው ናቸው። ከ20 ሺህ በላይ ሰዎች በትምህርት ቤት ምገባው ብቻ የሥራ ዕድል ተፈጥሮላቸዋል።

በማምሻ ዕድሜ ያሉ አረጋውያን፣ ስለኢትዮጵያ ታላላቅ አስተዋፅኦ ያበረከቱ የአዲስ አበባ ነዋሪ የሆኑ ማኅበራዊ ጫና ለችግር ያጋለጣቸው ሰዎችም በሰው ተኮር ልማቱ የተረሱ አይደሉም። ከተማ አስተዳደሩ ባዘጋጃቸው 19 የምገባ ማዕከላት ምግብ የሻተ እጁን ታጥቦ የሚመገብባቸው ማዕከላት ተሰናድተዋል። ተስፋ ብርሃን የምገባ ማዕከላት ይባላሉ_ለብዙ ሺዎች የተስፋ ብርሃን ሆነዋልና።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኅብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ኮሚሽን ኮሚሽነር አቶ አብርሃም ታደሰ እንደሚናገሩት፤ ከሀገራዊ ለውጡ ወዲህ አዲስ አበባ ለሰው ተኮር የበጎ አገልግሎት ሥራዎች ቢሮ ከፍታ፣ አመራር መድባ፣ ሠራተኛ ቀጥራ እና በጀት መድባ ሰው ላይ ሠርታለች። ከ14 በላይ በሆኑ የተለያዩ ፕሮግራሞች ተለይተው ውጤታማ ሥራዎችም ተሠርተዋል። ይህም በማኅበረሰባችን ውስጥ እየተቀዛቀዘ የመጣውን የጋራ የመረዳዳት፣ ደስታን ብቻ ሳይሆን ችግርን የመካፈል እሴቶቻችንን በማጎልበት ረገድ ትልቅ ዐሻራ ነው።

ክረምት ይጠብቅ የነበረው የበጎ አገልግሎት ተግባር ዓመቱን ሙሉ እንዲሠራ ሆኗል። በአካባቢ ጥበቃ፣ በትምህርት፣ በደም ልገሳ፣ በአረንጓዴ ልማት እንዲሁም ዕውቀትን መሠረት ያደረጉ መጻሕፍትን በመሰብሰብ፣ በሆስፒታል የሚገኙ ድጋፍ የሚሹ የኅብረተሰብ ክፍሎችን በመደገፍ፣ የደከሙ ቤቶችን በማደስ፣ በበዓላት ማዕድ በማጋራት፣ ለአካል ጉዳተኞች አጋዥ ተሽከርካሪዎች በመስጠት፣ በተለያየ ምክንያት ጉዳት

ከሀገራዊ ለውጡ ወዲህ አዲስ አበባ ለሰው ተኮር የበጎ አገልግሎት ሥራዎች ቢሮ ከፍታ፣ አመራር መድባ፣ ሠራተኛ ቀጥራ እና በጀት መድባ ሰው ላይ ሠርታለች።



ለደረሰባቸው ሰዎች ድጋፍ በማድረግ ሂደት መላውን የኅብረተሰብ ክፍል የማንቀሳቀስ ሥራ ተሠርቷል። ተማሪዎችም ትርፍ ጊዜያቸውን ለበጎ ዓላማ እንዲያውሉ ሆኗል።

በተቋሙ አማካኝነት ትብብርን፣ ደግነትን፣ መተጋገዝን ያጎለበቱ ዐቅሞችን በማስተባበር ከ20 ሺህ 800 በላይ የሚሆኑ ቤቶች ታድሰውና ተሠርተው በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ነዋሪዎችን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል። የገንዘብ፣ የዕውቀት እና የጉልበት ትብብሩ በገንዘብ ሲገመት ወደ 11 ቢሊዮን ብር የሚደርስ ሀብት ሥራ ላይ ውሏል። በዚህ በየአመቱ እያደገ በመጣ ሰውኛ ተግባር በ2015 ዓ.ም ብቻ ከ6 ቢሊዮን ብር በላይ ሀብት ተሰባስቦ ለዚህ ሥራ ውሏል።

ደግነትን በተቋም እና በአሠራር ማስተባበር በመቻሉ የአዲስ አበባ አብነት ወደሌሎች የሀገራችን አካባቢዎችም ሰፍቷል ይላሉ አቶ አብርሃም። ይህ በማኅበረሰባችን ውስጥ የነበረውን የመረዳዳትና የመደጋገፍ ዕሴት እንዲያድግ ትልቅ አስተዋፅኦ ባደረገው የኅብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፈቃድ ለተሠሩ ሥራዎች በሙሉ የሀብት ምንጩ ሕዝብ ነው።

ባለሀብቶች እስከ አንድ ቢሊዮን ብር ድረስ ለበጎ ዓላማ ድጋፍ አድርገዋል። ድጋፉ ርኃብን የሻረ፣ ያፈሰሰ ቤት፣ የተቦደሰ ግድግዳ፣ የላስቲክ ጣራ የቀየረ ሆኗል። የአረጋውያንን ድካም፣ የእርጅና ዘመን ችግር ያስወገደ ሆኗል። ወጣቶችን ያሳተፈው የበጎ ፈቃደኝነቱ ሥራ ወጣቶች በየአካባቢያቸው ያለውን ችግር ለይተው ትናንት ላሳደጓቸው ጎረቤቶቻቸው፣ ቤተሰቦቻቸው ቤት በማደስ፣ አካባቢ በማጽዳትና በመንከባከብ፣ ብርድ ፀሐይ ሳይሉ በትራፊክ ደኅንነት ላይ በመሠማራትና ለሌሎችም በጎ ተግባራት ጊዜና ጉልበታቸውንም





ስጥተዋል፤ በዚህም የብዙዎችን ሕይወት መቀየር ተችሏል።

## “አንድ ሰው ለአንድ ቤተሰብ”

“ሃምሳ ሎሚ ለአንድ ሰው ሸክሙ፣ ለሃምሳ ሰው ጌጡ” የሚለውን አባባል ከተማዋ ለበጎነት ሥራ ተጠቅማዋለች። ኮሚሽኑ ካሉት የበጎነት ማስፈጸሚያ መርሐ ግብሮች አንዱ “አንድ ሰው ለአንድ ቤተሰብ” የሚለው ይገኝበታል። ከክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እስከ ክብርት ከንቲባዋ፣ ከከንቲባዋ እስከ ክፍለ ከተማና ወረዳ አመራሩ ድረስ ያለው አመራር ይህንን የደግነት ሥራ በተግባር ገልጧል። ይህ ከላይ የጀመረው የአመራሩ ተግባር ሌሎችን ለማነሣሣት እንደረዳቸው አቶ አብርሃም ይናገራሉ። የተቸገሩ ሕፃናትን ማሳደግ፣ ገንዘብ በቋሚነት በማዋጣት አንድ ሰው አንድ ቤተሰብ መደገፍ፣ ማዕድ ማጋራት ባህል እየሆነ መጥቷል።

> በ“አንድ ሰው ለአንድ ቤተሰብ” መርሐ ግብር ከክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እስከ ክብርት ከንቲባዋ፣ ከከንቲባዋ እስከ ክፍለ ከተማና ወረዳ ድረስ ያለው አመራር ይህንን የደግነት ሥራ በተግባር ገልጧል።

ትኩረቱን ሰው ላይ አድርጎ፣ በሰዎች ስለሰዎች አዲስ አበባ ላይ እየተሠራ ያለው ተግባር ለትውልድ የሚሻገር ነው። ከሚመለከተው በላይ ተጠቃሚዎች ይናገሩታል። የባዶ የምሳ እቃ እና ሌሎች የሰቀቀን ታሪኮችን በሚሊዮን ለሚቆጠሩ ነዋሪዎች ተረት ያደረገ ሰውኛ ተግባር ሆኗል!




የብርሃን
መንገድ






አንድነት ፓርክ

# የብርሃን መንገድ

ተስፋ ፈሩ

አዲስ አበባ አዲስ መልክ በመላበስ ላይ ትገኛለች። ለዓሥርት ዓመታት ከአሸለባት፣ በየመሐሉ እየባነነች መልሳ ከምትወሰድበት እንቅልፍ እየነቃችም ነው።

በለውጡ ዘመን አዲስን የሚመጥን ዘላቂ ልማት ታቅዶላታል። የከተማዋን ገጽታ በመቀየር ላይ የሚገኙ በርካታ የልማት ሥራዎች ተከናውነዋል፤ እየተከናወኑም ነው። በግንባታ ሂደት ላይ የሚገኙና በውጥን የተያዙ ማርሽ ቀያሪ ፕሮጀክቶችም ብዙ ናቸው። ለነዋሪዎቿ የምትመችና የአፍሪካ መዲናነቷን እንድትመጥን በሚያስችል መልኩ የሚደረገው ዘርፈ ብዙ ጥረት 'ሰርክ አዲስ' የሚለውን ስያሜ እንድትመጥንም እያገዘ ነው።

በለውጡ ዘመን በጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ግንባር ቀደም መሪነት፤ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሜጋ ፕሮጀክቶች ጽሕፈት ቤት፣ በተለያዩ የልማት ድርጅቶች፣ በመንግሥት እና በግል ባለሀብቶች ጥምረት እንዲሁም በግሉ ዘርፍ በከተማዋ ግዙፍ ፕሮጀክቶች ተገንብተዋል። የቅድመ ዝግጅት ሥራ እየተከናወነላቸው ያሉ ሜጋ ፕሮጀክቶችም አሉ። እነዚህ በቢሊዮኖች የሚቆጠር በጀት የሚፈስባቸው ግዙፍ ፕሮጀክቶች አዲሲቷን፣ አዲስ አበባን እየፈጠሩ ነው። በዚህ ጽሑፍ ለአዲስ አበባ አዲስ መልክ እየሰጧትና እንደ ስሟ ውብ እያደረጓት ያሉትን ግዙፍ ፕሮጀክቶች እንዳስሳለን።



እንጦጦ ፓርክ

> ለዓሥርት ዓመታት ከአሸለባት፣ በየመሐሉ እየባነነች መልሳ ከምትወሰድበት እንቅልፍ እየነቃችም ነው።

## የአንድነት፣ ወዳጅነት እና እንጦጦ ፓርኮች

በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ሐሳብ አመንጪነት ግንባታው የተጀመረው የአንድነት ፓርክ በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ ተጠናቆ ጥቅምት 10 ቀን 2011 ዓ.ም በይፋ ተመርቆ ለሕዝብ ክፍት ሆኗል። የአንድነት ፓርክ በታላቁ ቤተ መንግሥት ቅጥር ግቢ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን፤ የተለያዩ ታሪካዊ፣ ተፈጥሯዊ እና ባህላዊ ቅርሶችን ያቀፈ ነው። ፓርኩ የሚገኝበት ታላቁ ቤተ መንግሥት በ1887 ዓ.ም. የተመሠረተ ነው። ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ አሕመድን ጨምሮ ቤተ መንግሥቱ የስምንት ኢትዮጵያውያን መሪዎች የመኖሪያና የሥራ ቦታ ሆኖ ዘልቋል። በ40 ሄክታር መሬት ላይ ከዐረፈው ቤተ መንግሥት 13 ሄክታር ያህሉ ላይ የዐረፈው አንድነት ፓርክ የሀገር በቀል ዕፅዋትና እንስሳት መገኛ፣ የነገሥታቱ እልፍኞች፣ ሙዚየምና ታሪክ ነጋሪ ክፍሎችን ይዟል።

የወዳጅነት ፓርክ የባህል ማዕከላትን፣ የሥነ ጥበብ ጋለሪ እና የሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ቦታዎችን የአካተተ 58 ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለው የእንጦጦ-አቃቂ የወንዝ ዳር (ሪቨር ሳይድ) ውበት ፕሮጀክት አካል ነው። የእግር ኳስ እና የቅርጫት ኳስ መጫወቻ ሜዳዎችን ጨምሮ የተለያዩ ደረጃቸውን የጠበቁ የመዝናኛ መገልገያዎችን እና የመጫወቻ ሜዳዎችን የአካተተ ነው።

በጠ/ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ አሕመድ ሐሳብ አመንጪነት የተጀመረው ሸገርን የማስዋብ ፕሮጀክት አካል የሆነው የእንጦጦ ፓርክ ግንባታ አንድ ዓመት ተኩል ገደማ የወሰደ ነው። የእንጦጦ ፓርክ በአምስት የግንባታ ሳይቶች ላይ በርካታ መዝናኛዎችን ይዟል። ከእንጦጦ እስከ አቃቂ የሚዘልቀው ሸገርን የማስዋብ ፕሮጀክት አካል የሆነው የእንጦጦ ፓርክ ከ2 መቶ ዓመታት በላይ የቆዩ ታሪካዊ ቅርሶችና የኢትዮጵያ ትልቁ የአርት ጋለሪ የሚገኝበት ነው። በአምስት ሳይቶች ተከፋፍሎ የተገነባው የእንጦጦ ፓርክ፣ በውስጡ የፈረስ መጋለቢያ ሜዳ እስከነ ፈረሶቹ ጋጣ፤ ባህላዊ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎችና በቀድሞ ነገሥታት የግብር አዳራሽ አምሳል የተሠሩ ባህላዊ ምግብ ቤቶችን፤ ዘመናዊ ካፍቴሪያዎችን፤ ለጥንዶችና በቡድን ለሚዝናኑ የተዘጋጁ መናፈሻዎችን፤ የህዋ መመልከቻ ማማ፤ የብስክሌት መጓጓዣና ሌሎችንም ይዟል።

## የመስቀል አደባባይ ፕሮጀክት

ግንባታው በሰኔ 2012 ዓ.ም የተጀመረው የመስቀል አደባባይ ፕሮጀክት ለግንባታ ሥራው 2 ቢሊዮን 589 ሚሊዮን 800 ብር በጀት ወጪ ተደርጎበታል። ከቸርችል ጎዳና እስከ መስቀል አደባባይ ልዩ ገጽታን ያላበሰው ይህ ፕሮጀክት መስቀል አደባባይ  የቀድሞ ይዘቱን ሳይቀይር ከመሬት ሥር ሁለት ወለል ወደ ውስጥ በመግባት የመኪና ማቆሚያ እንዲሁም አደባባዩንና ጎዳናዎችን የማስዋብ ሥራ ተሠርቷል። አደባባዩ ከዚህ ቀደም ሲሰጥ የነበረውን ሃይማኖታዊ፣ ሕዝባዊ እና ሌሎች ማኅበራዊ ዝግጅቶች በተለይ በከተማዋ ብዙኃኑን ታሳቢ ያደረጉ ኹነቶችን በተሻለ እና ምቹ በሆነ መልኩ ለማዘጋጀት በሚያስችል መልኩ የተገነባ ነው።

የመስቀል አደባባይ ፕሮጀክት በአካባቢው የሚስተዋለውን የተሽከርካሪ ማቆሚያ ሥፍራ ጥበትን ከመቅረፍ አንጻር እስከ 1ሺህ 400 የሚደርሱ ተሽከርካሪዎችን የሚያስቆሙ ባለሁለት ወለል የመሬት ውስጥ ስማርት ፓርኪንግ የያዘ ነው። በተጨማሪም 35 ሱቆች፣ 140 መጸዳጃና 20 መታጠቢያ ቤቶች፣ እንዲሁም ሌሎች የቢሮ መገልገያ ክፍሎች አሉት። ሱቆቹ የኢትዮጵያን ባህል እና ቅርሶች የሚያሳዩ እና ለጎብኚዎች እንዲሸጡ በሚያመች ሁኔታ የተገነቡ ናቸው። ስድስት ዘመናዊ ሊፍቶች፣ ለ24 ሰዓት አገልግሎት የሚሰጡ የደኅንነት ካሜራዎች፣ ዘመናዊ ዲጂታል ስክሪኖች እና የእሳት መከላከያ ተገጥሞለታል። በመስቀል አደባባይ እና አካባቢው ነጻ የWiFI ኢንተርኔት አገልግሎትም እንዲሰጥ ተደርጎ የተሠራ ነው።

## አብርሆት ቤተመጻሕፍት

የነገዋን ሀገር ተረካቢዎች ለማፍራት ትምህርት ተኪ እንደሌለው ጸሐይ የሞቀው ሐቅ ነው። ትምህርት ደግሞ ያ ለንባብ የሚታሰብ አይደለም። ከዚህ መሠረታዊ እውነት የተነሣውና ከ1 ነጥብ 1 ቢሊዮን ብር በላይ በሆነ ወጪ በአዲስ አበባ 4 ኪሎ በዘመናዊ መልኩ

የተገነባው አብርሆት ሁለገብ ቤተመጻሕፍት ታኅሣሥ 23 ቀን 2014 ዓ.ም በጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ አሕመድ በይፋ ተመርቆ ተከፍቷል። በ19 ሺህ ካሬ ሜትር ቦታ ላይ የዐረፈው ቤተመጻሕፍቱ በአፍሪካ ቀዳሚ ከሆኑ 10 ቤተመጻሕፍት መካከል አንዱ መሆኑ ተነግሮለታል። ቤተመጻሕፍቱ በ4 ወለሎቹ 1 ነጥብ 4 ሚሊዮን መጻሕፍትን መያዝ የሚችል 1 ነጥብ 5 ኪ.ሜ መደርደሪያ ይዟል። ተመርቆ በተከፈተበት ወቅት ከ240 ሺህ በላይ መጻሕፍትና 300 ሺህ ጥናታዊ ጽሑፎችን መያዙ ተገልጿል። የሕፃናት ማንበቢያ እንዲሁም ለዐይነ ስውራን አንባቢዎች በቂ የብሬይል መጻሕፍት አቅርቦት ያለው መሆኑም ልዩ ያደርገዋል። ዘመናዊ ካፍቴሪያ፣ የመሰብሰቢያ አዳራሾች፣ ስምንት የመጻሕፍት መሸጫ ሱቆች፣ አምፊ ቴአትር እና መጫወቻ ቦታዎችንም የአካተተ ነው። በተጨማሪም ደኅንነቱ የተጠበቀ በአንድ ጊዜ 115 መኪኖችን ማስተናገድ የሚችል የመኪና ማቆሚያ የያዘው ይህ ቤተመጻሕፍት ግንባታው የተጠናቀቀው በ18 ወራት ነው።



ሳይንስ ሙዚየም

## የሳይንስ ሙዚየም

በኢትዮጵያ በዓይነቱ የተለየ ነው የተባለ የሳይንስና ሥነ ጥበብ ሙዚየም በታላቁ ቤተ መንግሥት አቅራቢያ ተገንብቶ መስከረም 24 ቀን 2015 ዓ.ም. ተመርቆ ተከፍቷል። ሕንጻው በቀለበት ቅርጽ እና በጉልላት መልክ የተሠራ መሆኑ ምሉዕነትን፣ የማያቋርጥ የከፍታ ጥረትንና ምኞትን ማሳያ፣ ረቂቅ የሆነውን የኢትዮጵያዊ ጥበብ እንዲሁም ኢትዮጵያ የወደፊቱን ቴክኖሎጂ ለመጨበጥ ያላትን ፍላጎት የሚያሳይ ነው ተብሏል። የሙዚየሙ ውስጣዊ ክፍል ወደ 1400 ሜትር ስኩየር ስፋት ያለው ድምፅ የማያስተላልፍ ቋሚ እና ጊዜያዊ የዐውደ ርእይ ቦታዎችን የያዘ ነው። ሙዚየሙ ከዐረፈበት ቦታ 80 በመቶ የሚሆነው መሬትም ከአራት ሺህ በላይ በሆኑ ሀገር በቀል ዕፅዋትና ውብ አበቦች የተሸፈነ ነው፤ በቂ የመኪና ማቆሚያ ሥፍራም አለው። ሙዚየሙ ከተፈጥሮ ጋር በማይቃረን መልኩ የታነጸ ሲሆን የኤሌክትሪክ ኃይልም ከፀሐይ ብርሃን ያገኛል።


የአዲስ አበባ ከተማ ማዘጋጃ ቤት የውስጥ ገጽታ

## የአዲስ አበባ ከተማ ማዘጋጃ ቤት እድሳት

የአዲስ አበባ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ሕንጻው ከ57 ዓመታት በኋላ ነባር ገጽታውን ሳይለቅ እድሳት ተደርጎለት ጥር 15 ቀን 2014 ዓ.ም. ተመርቋል። የከተማ አስተዳደሩ ለመጀመሪያ ጊዜ የማዘጋጃ ቤቱን ዋና መሥሪያ ቤት ለማደስ በአጠቃላይ 2.2 ቢሊዮን ብር ፈሰስ አድርጓል። የእድሳት ሥራው የመሬት አቀማመጥ፣ ቢሮዎችን እና ባለ 850 መቀመጫዎች ያሉት የቴአትር አዳራሽ ማደስ እንዲሁም በማዘጋጃ ቤቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ አዳዲስ መገልገያዎችን የአካተተ ነው። እድሳቱ የተጠናቀቀው የማዘጋጃ ቤት ሕንጻ የሕፃናት መዋያ፣ ቤተመጻሕፍት፣ የሥልጠናና የምርምር ክፍሎች፣ ክሊኒክ፣ የቴአትር አዳራሽ፣ ስብሰባ አዳራሾች፣ የሠራተኞች እና የባለጉዳዮች መመገቢያ አዳራሽና የተለያዩ ቢሮዎችን ያቀፈ ሲሆን፤ በቂ የመኪና ማቆሚያ፣ አረንጓዴ ሥፍራዎችንና የከተማ ግብርናን አካቶ የያዘ ነው።

## ቤተ መንግሥት-ስማርት የመኪና ማቆሚያ

ዓለም አቀፍ የግንባታ ጥራቱን ጠብቆ የተገነባው ግራንድ የመኪና ማቆሚያ በቀን 1000 የሚሆኑ ተሽከርካሪዎችን የመያዝ ዐቅም አለው። ወደ ታች አራት የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች የያዘውና 9000 ካሬ ሜትር ላይ የዐረፈው ይህ ሜጋ ፕሮጀክት ግንባታው ሦስት ዓመታት ያህል ወስዷል። ከግል ተሽከርካሪዎች በተጨማሪ የአንበሳና የሸገር ባስ ማቆሚያ ቦታ ያለው ሲሆን፤ በውስጡም የተለያዩ ሱቆች፣ አምፊ ቴአትር ቤትና ቢሮዎችን አካቶ ይዟል። ዘመናዊነትን የተላበሰና ከታች ግራውንድ እስከ ላይ ድረስ የሚያወጣ የራሱ የሆነ የመኪና ማጓጓዣ አሳንሰር አለው። ጎብኚዎችን ከአንድነት ፓርክ ጋር ቀጥታ የሚያገናኝ ድንቅ ዋሻም በማዕከሉ ይገኛል።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከ1.7 ቢሊዮን ብር በላይ በሆነ ወጪ የተገነባው ግራንድ የመኪና ማቆሚያ አምፊ ቴአያትር፣ ባህላዊ ሬስቶራንቶች፣ ሱቆች እና ሌሎች መስኅቦችን የአካተተ ነው። የፓርኪንግ ሕንጻው ለብሔራዊ ቤተ መንግሥት፣ ለሳይንስ ሙዚየም፣ ለወዳጅነት አደባባይ ምዕራፍ ሁለት እና ለሌሎችም የፓርክ መዳረሻዎች ከመስቀል አደባባይ እስከ አብርሆት ቤተመጻሕፍት የጎብኚዎች ማዕከል ሆኖም ያገለግላል።

## የገርጂ ዘመናዊ መኖሪያ መንደር

በ18 ወራት ውስጥ በሦስት ቢሊዮን ብር በፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን የተገነባው የገርጂ ዘመናዊ መኖሪያ መንደር ቴክኖሎጂ፣ ጊዜና ወጪ ቆጣቢ ፕሮጀክት መሆኑ የተመሰከረለት ነው። የገርጂ ዘመናዊ መኖሪያ መንደር ፕሮጀክት በዓይነቱ ልዩ የሆነና እንደ ሀገር በመኖሪያ ቤት ግንባታ ዘመኑን የዋጀ አዳዲስ የግንባታ ቴክኖሎጂዎችን ይዞ የመጣ ነው። የመኖሪያ መንደሩ ዘመናዊ የደኅንነት ጥበቃ ሥርዓት የተገጠመለት፣ ከ800 በላይ መኪና ማቆም የሚያስችል ሥፍራ፣ የጋራ መጠቀሚያ አዳራሽ፣ የተለያዩ ስፖርት መሥሪያ ቦታዎች፣ ካፌና ሬስቶራንት፣ መናፈሻ፣ አምፊ ቴአትር፣ የልጆች መጫወቻና መዋኛ ገንዳን የአካተተ ነው።

## የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ዋና መሥሪያ ቤት

ለአዲስ አበባ ተጨማሪ ሞገስ የሆነውና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የአስገነባው አዲስ የዋና መሥሪያ ቤት ሕንጻ 209 ነጥብ 15 ሜትር ከፍታ ያለው ሲሆን ምድር ውስጥ ያለውን ጨምሮ ባለ 53 ወለል ነው። 5 ዓመታት ከ11 ወራት የወሰደው ግንባታው 303 ሚሊዮን 500 ሺህ የአሜሪካ ዶላር ወጪ ተደርጎበት የካቲት 6 ቀን 2014 ዓ.ም ተመርቋል። ሕንጻው በውስጡ የቢሮ አገልግሎት ከሚሰጡ ክፍሎች በተጨማሪ እጅግ ግዙፍ የመሰብሰቢያ አዳራሾች፣ ሙዚየም፣ ሱፐርማርኬት እና ሲኒማ ቤትን አካቷል። እስከ 1 ሺህ 500 መኪናዎችን መያዝ የሚችል ማቆሚያም አለው። የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የአስገነባው የዋና መሥሪያ ቤት ሕንጻ በቁመቱ ከምሥራቅ አፍሪካ ቀዳሚ እንዲሁም በአፍሪካ 7ኛው ግዙፍ ሕንጻ እንደሆነ ተነግሮለታል። ሌሎች ባንኮችና የፋይናንስ ተቋማትም ለአዲስ አበባ አዲስ ገጽታን ያላበሱ ረጃጅም ሕንጻዎችን ገንብተዋል። አሁንም እየተገነቡ ያሉ በርካቶች ናቸው።

## የመንገድ ፕሮጀክቶች

የከተማ ዘመናዊነት አንዱ መገለጫ የመንገድ መሠረተ ልማት ነው። ዘመናዊቷ አዲስም በተለይም በለውጡ ዘመን እጅግ ውብና ዘመናዊ መንገዶች ባለቤት በመሆን ላይ ትገኛለች። በዓይነቱ ልዩ የሆነው የሳር ቤት ጎፋ ማዞርያ የፑሽኪን ጎተራ ማሳለጫ ዘመናዊ የመንገድ ፕሮጀክት ግንባታ ተጠናቆ ለአገልግሎት ክፍት ሆኗል። የማሳለጫ መንገዱ የአዲስ አበባን ስምና ዓለም አቀፍ ደረጃዋን በሚመጥን መልኩ ዘምኖ የተገነባ ነው። የፑሽኪን አደባባይ ጎፋ ማዞሪያ- ጎተራ ማሳለጫ የመንገድ ፕሮጀክት 3 ነጥብ 8 ኪሎ ሜትር ርዝመትና ከ30 እስከ 45 ሜትር ስፋት ያለው ሲሆን፤ የግንባታ ወጪው 1 ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር ደርሷል። በሁለት በኩል 320 ሜትር ርዝመት ያለው ዋሻ፣ የፈጣን አውቶቡስ መተላለፊያ መሥመርና ተሽከርካሪዎችን ከሥርና ከላይ የሚያሳልፍ ዘመናዊ መንገድ ያቀፈ ነው።

## የመከላከያ ዋና መሥሪያ ቤት

የመከላከያ ሚኒስቴር ዋና መሥሪያ ቤት ሕንጻ ግንባታው ተጠናቆ ጥር 1 ቀን 2014 ዓ.ም ተመርቋል። የሚኒስቴሩ ዋና መሥሪያ ቤት ጦር ኃይሎች በሚገኘው የቀድሞ የአውሮፕላን ማረፊያ ሥፍራ ላይ የተገነባ ነው። ሕንጻው በ13 ሺህ ካሬ ስፋት ላይ ያረፈ ሲሆን፣ ባለ 5 ወለል እና ከ700 በላይ ቢሮዎች ያሉት ነው። በውስጡም የተለያየ ደረጃ ያላቸው የስብሰባ አዳራሾች፣ ቤተመጻሕፍት፣ የምርምር ማዕከላትና የተደራጀ የመረጃ ማዕከልን አካቷል። የሕንጻው ኪነ ሕንጻ ከኢትዮጵያውያን ሥነ ልቦና እና ፍልስፍና ተቀድቶ የተዘጋጀ ሲሆን፤ ከላይ ጦር እና ጋሻ ሆኖ ይታያል፤ ይህም የመከላከያ ሠራዊት ሀገር የመጠበቅ ሚናውን የሚያንጸባርቅ ነው። በአረንጓዴ ልማት የታጀበው ይህ ዘመናዊና ኢትዮጵያን የሚመጥነው ሕንጻ ሰው ሠራሽ ፏፏቴም አለው።

## ዓድዋ ሙዚየም

የዓድዋ ሙዚየም ፕሮጀክት በአዲስ አበባ መሐል ፒያሳ ላይ እየተገነባ ያለ ግዙፍ ግንባታ ነው። የዓድዋ ሙዚየም ፕሮጀክት ኢትዮጵያውያን አባቶቻቸውን ዘክረውና አንድነታቸውን አጽንተው ለትውልድ የሚያስተላልፉበት የጥንካሬ፣ የጀግንነት እና የነጻነት ማሳያ ነው። 4.6 ቢሊዮን ብር በጀት የተያዘለትና በ12 ሔክታር መሬት ላይ የዐረፈው ይህ ፕሮጀክት ግንባታው በመገባደድ ላይ



የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ዋና መሥሪያ ቤት





የሳር ቤት ጎፋ ማዞርያ የቱሽኪን ጎተራ ማሳለጫ ዘመናዊ መንገድ

ይገኛል። የመዋቅር ግንባታ ሥራው መጠናቀቅን ተከትሎ የማጠቃለያ ሥራዎች እየተከናወኑ ነው። በዚህም የኤሌክትሪክና የውሃ መሥመር ዝርጋታ፣ የወለል ንጣፍ፣ የጅብሰም እና ሌሎች መሰል የማጠቃለያ ተግባራት በሕንጻው ውስጣዊ ክፍሎች በመሠራት ላይ ይገኛሉ። ሙዚየሙን ለአገልግሎት ለማብቃት ሥራዎች እየተፋጠኑ ሲሆን የፕሮጀክት ግንባታ አፈፃፀም 80 ከመቶ በላይ ደርሷል።

የዓድዋ ሙዚየም ፕሮጀክት ከ2,000 እስከ 4,000 ሰዎችን ማስተናገድ የሚችል የመሰብሰቢያ አዳራሽ፣ የሕዝብ ቤተመጻሕፍት፣ የተለያዩ ቢሮዎች፣ ካፍቴሪያና የመሳሰሉትን አገልግሎቶችን የሚሰጡ ክፍሎች፣ የቤት ውስጥ ስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎች፣ የአውቶቡስና የታክሲ ተርሚናል፣ እንዲሁም ከሕንጻው ውጪ የቴአትርና የኤግዚቢሽን ማሳያ ቦታዎች የሚይዝ ነው።

## የላጋር የተቀናጀ መንደር

በአዲስ አበባ የድሮው ባቡር ጣቢያ ለገሐር አካባቢ በ360 ሺህ ካሬ ሜትር ስኩዌር ቦታ ላይ የሚያርፈው የለገሐር የተቀናጀ የልማት ፕሮጀክት በአዲስ አበባ ማዕከል እየተገነባ ያለና በውስጡ ከ4000 በላይ መኖሪያ ቤቶች፣ የመዝናኛ ሥፍራዎች፣ ግዙፍ የንግድ ማእከላት፣ መጋቢና ዋና መንገዶች እና ሌሎች ዘመናዊ አገልግሎት መስጫ ሥፍራዎችን የያዘ ግዙፍ መንደር ነው።

ከቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ በቅርብ ርቀት የሚሠራው

ዘመናዊቷ አዲስም በተለይም በለውጡ ዘመን እጅግ ውብና ዘመናዊ መንገዶች ባለቤት በመሆን ላይ ትገኛለች። በዓይነቱ ልዩ የሆነው የሳር ቤት ጎፋ ማዞርያ የቱሽኪን ጎተራ ማሳለጫ ዘመናዊ የመንገድ ፕሮጀክት ግንባታ ተጠናቆ ለአገልግሎት ክፍት ሆኗል።

ይህ ሁለገብ መንደር ባለ አምስት ኮከብ ሆቴሎች፣ አረንጓዴ መዝናኛ ሥፍራዎች፣ ምቹና ሰፋፊ የእግረኛ መንገዶች እና የመኪና ማቆሚያ ሥፍራዎች በበቂ ሁኔታ በውስጡ እንዲካተተ ማስተር ፕላኑ ያመለክታል። ከለገሐር በስተሰሜን ምሥራቅ አቅጣጫ እየተገነባ ያለው ይህ መንደር በኢትዮጵያ መንግሥት እና በዱባዩ ኤግል ሒልስ ትብብር እየተሠራ የሚገኝ ነው።

## የካ - 2 መኪና ማቆሚያ

ከአንድ ነጥብ አንድ ቢሊዮን ብር በላይ በጀት ተመድቦለት ግንባታው እየተከናወነ የሚገኘው የካ-2 መኪና ማቆሚያ ግንባታ ፕሮጀክት ከመሬት ውስጥ እና ከመሬት በላይ እየተሠሩ ባሉ ወለሎች 900 ተሽከርካሪዎችን ማስተናገድ የሚያስችል ዐቅም ያለው ነው። የከተማው አስተዳደር የግዙፍ ፕሮጀክቶች ግንባታ አካል የሆነው የካ-2 መኪና ማቆሚያ (ሾላ ፓርኪንግ) ግንባታ የተወሰኑ ሱቆችና መኪና ማጠቢያን የአካተተ የመኪና ማቆሚያ ሕንጻ ነው። የግንባታ ፕሮጀክቱ ሲጠናቀቅ ከዘጠኝ መቶ በላይ መኪናዎችን ማቆም የሚያስችል ምቹና አስተማማኝ ጥበቃ ያለው ቦታን በማቅረብ በሾላ ገበያ አካባቢ ያለውን የመኪና ማቆሚያ ቦታ እጥረት በመቅረፍ የአካባቢውን የትራፊክ ፍሰት ያሳልጣል ተብሎ ይጠበቃል። በአሁኑ ወቅት ግንባታው 42 በመቶ ደረጃ ደርሷል።

## የግብርና ምርቶች ማከማቻና መሸጫ ማዕከላት

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሕዝቡን የኑሮ ጫና ለማቃለል አምራችን ከሸማች በቀጥታ ማገናኘት የሚያስችል የግብርና ምርቶች ማከማቻና መሸጫ ማዕከላት ግንባታ በማከናወን ላይ ነው። በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ ሰባት፣ በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ወረዳ ሁለት አያት እና ወረዳ አምስት ሰሚት አካባቢ እየተገነቡ የሚገኙት እነዚህ ግዙፍ ፕሮጀክቶች በድምሩ ከስድስት ቢሊዮን ብር በላይ በጀት ተመድቦላቸዋል። ማዕከላቱ ግንባታቸው ሲጠናቀቅ አሁን ላይ ያለውን ሕገወጥ የገበያ ትስሥር ሰንሰለትን በማስቀረት እና የነዋሪውን ኅብረተሰብ የኑሮ ጫና በማቅለል ረገድ ከፍተኛ ሚና ይኖራቸዋል። የሦስቱ የገበያ ማዕከላት ግንባታ በአራትና አምስት ወራት ጊዜ ውስጥ ከ45 እስከ 65 በመቶ መድረስ ችሏል።

### ትራፊክ ማኔጅመንት ማዕከል

የአዲስ አበባ ከተማ ትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 08 አካባቢ በመገንባት ላይ ያለ ፕሮጀክት ሲሆን፤ ሕንጻው በ7,507,175 ካሬ ሜትር ላይ ዐርፏል። ግንባታው ከተጀመረ ጊዜ አንሥቶ 831,842,924.43 ብር ፈሰስ ተደርጎበታል። ሕንጻው በመጀመሪያ ወለሉ ላይ የደኅንነት መጠበቂያ ክፍል፣ ፓርኪንግ፣ የመሰብሰቢያ አዳራሽ፣ የፋይናንስ ክፍል፣ የእንግዳ መቀበያ ክፍል፣ የአደጋ መውጫና ሌሎች ክፍሎችን አካቶ ይዟል። በሁለተኛ፣ በሦስተኛና በአራተኛ ወለል ላይ ደግሞ የተለያዩ አገልግሎቶችን ይሰጣል። ፕሮጀክቱ ሙሉ ለሙሉ ተጠናቆ እውን ሲሆን ለአዲስ አበባ ከተማ ዘመናዊና ቴክኖሎጂን የተላበሰ የትራፊክ አገልግሎትን ለመስጠት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። በአሁኑ ወቅት ግንባታው 54 በመቶ ተጠናቋል።

## የልማት ተነሽ አርሶ አደሮች መልሶ ማቋቋሚያ ፕሮጀክት

የልማት ተነሽ አርሶ አደሮች መልሶ ማቋቋሚያ ፕሮጀክት ለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ኮዬ ፈቼ ኮንዶሚኒየም አካባቢ የሚገኝና 14 ሔክታር መሬት ላይ የዐረፈ ፕሮጀክት ነው። ፕሮጀክቱ እስካሁን 811,683,914,94 ብር ወጪ የተደረገበት ሲሆን፤ ከ91 በመቶ በላይ ተጠናቋል። በልማት ምክንያት ከቀዬአቸው የተፈናቀሉ አርሶ አደሮች የኢኮኖሚ ተጠቃሚ እንዲሆኑበት ታስቦ እየተገነባ ያለው ይህ ፕሮጀክት በውስጡ 300 ሜትር ኪዩብ ውሃ የመያዝ ዐቅም ያለው ማጠራቀሚያ፤ ለወተት ላሞች እርባታ ዓሥር ብሎኮች፣ ለሥጋ ከብቶች ማደለቢያ ዓሥር ብሎኮች፣ ለምርት መሸጫና ማሳያ 32 ሼዶች እንዲሁም አንድ የከብቶች መኖ ማከማቻና ሌላ የዶሮ መኖ ማከማቻና መጋዘኖችን ከተጨማሪ ሌሎች አገልግሎት መስጫ ክፍሎች ጋር አጣምሮ የያዘ ነው።

## ለሚ አደባባይ

በ1.3 ቢሊዮን ብር በጀት በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ እየተገነባ ያለው ለሚ አደባባይ ለአዲስ አበባ ከመስቀል አደባባይ ቀጥሎ ሁለተኛው ግዙፍ አደባባይ ነው። ግንባታው በይፋ ጥር 9 ቀን 2015 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከንቲባ ወ/ሮ አዳነች አቤቤ የተጀመረው አደባባይ 14,400 ካሬ ሜትር ላይ ያርፋል። የሕዝብ ሥፍራ አደባባይ (ፐብሊክ ስፔስ)፣ የመኪና ማቆምያ፣ የመዝናኛ ሥፍራዎች፣ ጂምናዝየሞች፣ የስብሰባ አዳራሽ፣ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራ፣ የሰርግና ሌሎች አገልግሎቶች የሚውል መናፈሻ፣ ሱፐርማርኬት፣ የቢሮ አገልግሎት የሚሰጡ ቦታዎች፣ መጻሕፍት የማንበቢያ ሥፍራና ሌሎች አገልግሎት መስጫ ቦታዎች ይኖሩታል። አካባቢውንም በማስዋብ ከመንገድ አካፋዮች፤ አደባባዮችንና የእግረኛ መንገዶች ጋር ተናቦ የሚሠራ ሁለንተናዊ ፕሮጀክትም ነው። ፕሮጀክቶች በመሐል ከተማ ብቻ ሳይሆኑ በዳር አካባቢዎችም ማዳረስን ታሳቢ ያደረገ መሆኑ የተነገረለት የለሚ አደባባይ አዲስ አፍሪካ ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽን ማዕከል በሚገኝበት አካባቢ እየተገነባ ያለ ነው።

## አዲስ አፍሪካ ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽን ማዕከል

አዲስ አፍሪካ ኤግዚቢሽንና ኮንቬንሽን ማዕከል ከአራት ቢሊዮን ብር በላይ በሆነ ወጪ ሴኤምሲ አካባቢ እየተገነባ ያለ ትልቅ ፕሮጀክት ነው። የኮንቬንሽንና ኤግዚቢሽን ማዕከሉ ዓለም አቀፍ መስፈርቶችን አሟልቶ እየተገነባ የሚገኝ ዓለም አቀፍና አህጉራዊ ስብሰባዎች፣ ኮንቬንሽኖችና ዐውደ ርእዮች ማስተናገድ የሚችል ግዙፍ ፕሮጀክት ነው። የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የአዲስ አፍሪካ ኤግዚቢሽንና ኮንቬንሽን ማዕከል ከፍተኛ ባለአክስዮን ነው።

## የአነስተኛ እና መካከለኛ ኢንዱስትሪ ክላስተር ግንባታ

የአዲስ አበባ ከተማ አነስተኛ እና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ክላስተር ግንባታ 4 ነጥብ 7 ቢሊዮን ብር ተበጅቶለት ጥቅምት 2015 ዓ.ም ተጀምሯል። ፕሮጀክቱ ለአዳዲስ ኢንዱስትሪያሊስቶች የሥራ ዕድል መፍጠር፣ ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ በሚመረቱ ምርቶች መተካት፣ የውጭ ምንዛሪ ችግርን መቅረፍ ታሳቢ አድርጎ እየተካሄደ ያለ ነው።

## አደይ አበባ ስታዲየም

በአዲስ አበባ ቦሌ አካባቢ በቻይናው ስቴት ኮንስትራክሽን ኢንጂነሪንግ ኩባንያ እየተገነባ ያለው አደይ አበባ ብሔራዊ ስታዲየም 62 ሺህ ሰዎችን የመያዝ ዐቅም ያለው ነው። የመጀመሪያው ምዕራፍ ሥራው የተጠናቀቀ ሲሆን፤ ይህም አጠቃላይ የሕንጻውን መዋቅር ጨምሮ የስፖርተኞች ማረፊያ፣ ቢሮዎች፣ የጋዜጠኞች ማስተናገጃ ወዘተ ያካትታል። ለመጀመሪያው ምዕራፍ ግንባታ ከ2.47 ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ ተደርጓል። በሁለተኛው ምዕራፍ የስታዲየሙ ፕሮጀክት ከሚካተቱት ሥራዎች መካከል የመጫወቻ ሜዳውን ሳር ማልበስ፣ የመሮጫ ትራክ ማንጠፍ፣ የስታዲየሙን ጣሪያ ማልበስና ወንበር መግጠም ይገኙበታል። በተጨማሪም ሰው ሠራሽ ሐይቅ፣ የሄሊኮፕተር ማረፊያ፣ ዘመናዊ የደኅንነት ካሜራ መግጠምና ሌሎች በርካታ ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ።



አደይ አበባ ስታዲየም በግንባታ ላይ የዘውዲቱ መታሰቢያ ሆስፒታል የማስፋፊያ ግንባታ

## የዘውዲቱ መታሰቢያ ሆስፒታል የማስፋፊያ ግንባታ


በ1 ሺ 800 ካሬ ሜትር መሬት ቦታ ላይ የማስፋፊያ ግንባታው እየተከናወነ የሚገኘው የዘውዲቱ መታሰቢያ ሆስፒታል ሰፋፊ መታከሚያ ክፍሎች አሉት። ተኝቶ መታከሚያ 200 አልጋ፣ ለተመላላሽ ታካሚ 26 ክፍሎች፣ ለሕፃናትና ፅኑ ሕሙማን የሚሆን 50 አልጋ እንዲሁም የኦፕራሲዮን ማድረጊያ 6 አልጋ መያዝ የሚያስችል ዐቅም አለው። በተጨማሪም ራሱን የቻለ የኤክስ ሬይ (X ray)፣ ሲቲ ስካን (city scan ) ክፍል፣ የተለያዩ ሥልጠናዎች ማካሄጃ ክፍሎች፣ 300 ሰዎችን ማስተናገድ የሚያስችል መሰብሰቢያ አዳራሽ እና ደረጃውን የጠበቀ መድኃኒት ማከማቻ ክፍል ያለው ግዙፍ የልማት ሥራ ነው። በአዲስ አበባ ከሚገኙት ሆስፒታሎች መካከል ተጠቃሽ የሆነውና ለዘጠና ዓመታት አገልግሎት የሰጠው ይህ አንጋፋ ሆስፒታል የማስፋፊያ ግንባታው ሲጠናቀቅ በሆስፒታሉ ያለውን የሕሙማን አገልግሎት አሰጣጥ ክፍተት በከፍተኛ ደረጃ ይቀርፋል ተብሎ ታምኖበታል።

## "አዲስ ቱሞሮ"

ጥቅምት 11 ቀን 2012 ዓ.ም ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ አሕመድ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተገኝተው ከምክር ቤቱ አባላት ለቀረበላቸው ጥያቄ ምላሽ በሰጡበት ወቅት፤ ጎተራ አካባቢ ለባለሀብቶችና ዲፕሎማቶች የቤት ፍላጎት የሚሆን "አዲስ ቱሞሮ" የተሰኘ አዲስ ፕሮጀክት ከቻይና መንግሥት ኩባንያ ጋር ሊፈራረሙ መሆኑን ገልጸው ነበር። ይሄው ዕቅድ ጎልምሶና ፍሬ አፍርቶ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ክብርት አዳነች አቤቤ እና በቻይናው አምባሳደር ዚንሃዎ አማካኝነት የትግበራ ስምምነት ተፈርሟል።

ከላይ የተዘረዘሩት ግዙፍ ፕሮጀክቶች እውን መሆን የአዲስ አበባ ብሩህ ዘመን እውነትም መቃረቡን አመላካች ናቸው። በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በደምብ ቁጥር 110/2012 ዓ.ም. ተቋቁሞ ከአንድ ቢሊዮን ብር በላይ በጀት ያላቸውን ትላልቅ ፕሮጀክቶች ከውሃ፣ መብራትና መንገድ መሠረተ ልማቶች ውጪ ግንባታዎችን እንዲያሠራ ሥልጣን የተሰጠው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሜጋ ፕሮጀክቶች ጽሕፈት ቤት ምክትል ሥራ አስኪያጅ ኢንጂነር ምሬሳ ልኬሳ አስተያየት ይህንኑ የሚያረጋግጥ ነው። ጽሕፈት ቤታቸው በሚያሠራቸው ትላልቅ ፕሮጀክቶች ለ24 ሰዓታት ያለመቋረጥ የግንባታ ሥራዎች ይከናወናሉ። ከታች እስከ ላይኛው አመራር ድረስ በተዘረጋ የክትትልና ድጋፍ መስጫ ሥርዓት በመታገዝ ለግንባታ ሥራዎቹ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶ ችግሮች ከሥር ከሥር እየተቀረፉ ግዙፍ ግንባታዎቹ በተያዘላቸው ጊዜ እንዲጠናቀቁ እየተደረገ ነው። በቀጣይ መሰል ግንባታዎችን በራስ ዐቅም ማካሄድ የሚያስችል የቴክኖሎጂ ሽግግርና የሰው ኃይል የማብቃት ሥራም እየተሠራ ነው። ውብ-አዲስ አበባ በአስገራሚ ፍጥነትና ዘመን ተሻጋሪ በሆነ የጥራት ደረጃ እየተገነባችና እያበበች በብርሃን ፍኖት የትንሳኤ ጉዞዋን ቀጥላለች።

# የኅብሮነት



# ሙዚቃ



# የኅብሮነት መዲና

**ሳሙኤል ይትባረክ**

> **አዲስ አበባ**
> የሀገራችን ዋና መዲና፤ የተለያዩ አህጉር አቀፍና ዓለም አቀፍ ተቋማት መቀመጫ፤ የአፍሪካ ሕብረት ጽሕፈት ቤት መቀመጫ፤ ከዓለም ሦስተኛዋ የዲፕሎማቲክ ከተማ፤

ጽጌረዳ ቢጫ ሮዝ ቀይ.. ቀለማት አሉት። እነዚህ የቀለማቱ መለያየት ጽጌረዳ የሚለውን ስያሜ አሳጥተው ሌላ ስያሜ እንዲኖረው አለአደረጉትም፤ ይልቁኑ ተጨማሪ ውበትና ድምቀት ሆነውለት መወደዱንና መፈለጉን ጨመሩለት እንጂ! ኢትዮጵያም እንዲሁ ናት አንዲት ግን ብዙ ቀለም፣ ባህል፣ ሃይማኖትንና ቋንቋን የአቀፈች። የሥነ ልቦና ሳይንቲስቶች ልዩነት የውበት መገለጫና ስልቹነትን ማስወገጃ ፍቱን መድኃኒት ነው ይሉታል።

ብዝኃነት ጌጥ ከሆነላቸው ጥቂት ሀገራት መካከል ኢትዮጵያ ተጠቃሽ ነች። ብዙ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የሚኖሩባት፣ የቋንቋ፣ የባህል፣ የሃይማኖት፣ የመልክአ ምድራዊ አሠፋፈርና መሰል ልዩነቶች የታደለች ናት። በልዩነት ውስጥ የዳበረው አንድነት በዓለም ላይ ካሉ ውስን ሀገራት ቀዳሚ ያደርጋታል። የበርካታ ብሔሮችና ብሔረሰቦች መኖሪያ በመሆኗ የአያሌና ማራኪ ባህላዊ ዕሴቶች፤ እደ ጥበብ ሀብቶች፤ ሀገር በቀል ዕውቀቶችና አስደማሚ ቅርሶች ባለቤት በመሆኗ በርካቶቹን የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ ቅርሶቿን በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፤ የሳይንስና የባህል ድርጅት/ UNESCO/ በዓለም ቅርሥነት አስመዝግባለች።

በኅብረ-ብሔራዊነቷ ምክንያት «ትንሿ ኢትዮጵያ» በመባል የምትጠራው አዲስ አበባም የሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ ነጸብራቅ በመሆኗ በውስጧ አቅፋ ያልያዘችው የሀገራችን ብሔር ብሔረሰብ አለ ለማለት ያዳግታል። የእነዚህ ብሔሮችና ብሔረሰቦች በከተማዋ መኖር ለከተማዋ ልዩ ውበትና ድምቀት ከመሆን ባለፈ ከተማዋ የራሷ መለያ ጠባይ እንዲኖራት አስችሏል። አዲስ አበባ የሁሉም ኢትዮጵያውያን መልክ ያላት እና ከብሔረሰቦች ባህል መዋሐድ ባለፈ እጅግ በረቀቀ መልኩ በፍቅር፣ በጋብቻ እና በመሳሰሉት ሁኔታዎች የተዋሐዱ ሰዎች መኖሪያ ከተማ እንድትሆን አድርጓታል።

አዲስ አበባ ስትመሠረት ጀምሮ የነበራትን የኅብረ ብሔራዊነት ረጅም ታሪክ በ19ኛው እና በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በሀገርኛና በኅብኚዎች የተፃፉ ሥራዎች ዘግበውታል። በስቶኒ ብሩክ ዩኒቨርሲቲ የአፍሪካ ታሪክና የፖለቲካ መምህር ዶክተር ሺመልስ ቦንሳ፤ አዲስ አበባ ከብዙ የአፍሪካ ከተሞች በተለየ ድሃና ሀብታም ተሰባጥረው የሚኖሩባት፤ ነዋሪዎቿን ከነብዝኃነታቸው አቅፋ የኖረች፣ ያኖረች፣ የምታኖር የኢትዮጵያ የልብ ትርታና የነርቭ ማዕከል የሆነች ከተማችን ማረፊያችን፣ ችግሯም ችግራችን፣ ፍቅራችን እንደገናም ተስፋችን ሆናለች። ይህች ድንቅ ስብጥር የሆነች ከተማ ንብርብር ታሪክ የተሸከመች ምድር ከመሪዎቿ በላይ የብዙኃን ነዋሪዎቿ ድምር ውጤትና የእጅ ሥራ ነጸብራቅ ናት ሲሉ ይገልፃሉ።

ዶክተር ሺመልስ በጽሑፋቸው፤ በብዙኃነት ጥልፍልፍ ተፀንሳ የተወለደች አድጋም የጎለመሰች አዲስ አበባ ምንነቷና የማንነቷ ምስጢር በአንድነት ተጋምዶ፣ በልዩነት ውበት አሸብርቆ ደምቆ የተፈጠረ የውህደት ቋጠሮ ነው። አዲስ አበባ ልክ እንደ ኢትዮጵያ የነዋሪዎቿ ስብስብ ውጤት ብቻ ሳትሆን ከድምርነቷም በላይ እጅግ የጠበቀ፣ የጠለቀ የውሕደት ስብጥር ናት። አዲስ አበባን ለመፍጠር ያልተጋ የኢትዮጵያዊ እጅ የለም። ኦሮሞው ከአማራው፣ ጉራጌው ከትግሬው፣ ዶርዜው ከሐረሪው፣ ሶማሌው ከወላይታው፣ ምሥራቁ ከደቡብ፣ ሰሜኑ ከምዕራቡ፣ ወንዱ ሴቱ፣ ልጅ ዐዋቂው፣ ነጋዴው ምሁሩ፣ ሀገሬው ከሌላው ተዋዶ፣ ተዋልዶ፣ ተናግዶ የፈጠራት ከተማ ከሚባል ነገር በላይ የሆነች ምስጢርም ናት።

አዲስ አበባ ኢትዮጵያውያን ለጋራ ታሪካቸው የተዋደቁባቸውና ጠንካራ አንድነታቸውን ያስመሰከሩባቸው




ታሪኮች ሐውልት ተቀርጾላቸው በየቀናቸው ክብረ በዓል ተበጅቶላቸው እምነት፣ ባህል፣ ቋንቋ፣ ፆታ ሳይለይ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በራሱ አለባበስ ተጊጦና ኀብር ሠርቶ በድምቀት የሚያከብርባት ከተማ ናት። ሀውልቶቹም የከተማዋ ውበት ብቻ ሳይሆኑ ከሰሜን እስከ ደቡብ፣ ከምዕራብ እስከ ምሥራቅ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን የታሪክ ዐሻራን በደማቅ የሚያሳዩ ናቸው። ለአብነት ያህል 30 ሺህ የሚደርሱ በአዲስ አበባ የነበሩ ኢትዮጵያውያን ስለመጨፍጨፋቸው የሚያወሳው የየካቲት 12 የሰማዕታት መታሰቢያ ሐውልትን፣ የዐፄ ምኒልክንና የድል ሐውልትን እንዲሁም የኢትዮ ኩባ የወዳጅነት ሐውልትን ብቻ ብንመለከት ትግሬው፣ ኦሮሞው፣ አማራው፣ ሐረሪው፣ ሱማሌው፣ አፋሩ፣ ሲዳማው፣ አጠቃላይ ሁሉም ብሔር ብሔረሰብ ለእናት ሀገሩ ኢትዮጵያ መሥዋዕትነት የከፈለበት የታሪክ ዐሻራዎቹ የሚገኙባት ከተማ አዲስ አበባ የማንነት ደብር መሆኗን ያስረዳሉ።

መዲናችን አዲስ አበባ የሁሉም ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መኖሪያ መሆኗ የተለያዩ አልባሳት፣ ምግቦች፣ ጭፈራ እምነት ወዘተ መናኸሪያ እንድትሆን አድርጓታል።

በከተማዋ የተለያዩ ክፍሎች ስንዘዋወር የምናገኛቸው እና የተለያየ ስያሜ ያላቸው ክትፎ፣ ቁርጥ፣ ዶሮ ወጥ፣ ተጋቢኖ፣ ቦርሰሜ ጭኮን የመሳሰሉ ምግቦች የአዲስ አበባ የብዙኃን ከተማ መሆኗ የወለዳቸው ምርጥ ስጦታዎቻችን ናቸው።

እግር ጥሎን ወይም ደግሞ ለመሸመት ፈልገን ሽሮ ሜዳ ከሄድንም ትንሿን ኢትዮጵያን በተለያዩ አልባሳት ተወክላ እናገኛታለን። የጋሞ፣ አማራ፣ ኦሮሞ ትግሬ፣ ሲዳማ፣ ስልጤ......ወዘተ አልባሳትን የቀለምና የውበት ስብጥር ሽሮ ሜዳ ላይ ስንመለከት ኅብረ ብሔራዊነት ለአዲስ አበባ ጌጥና በረከት መሆኑ ፍንትው ብሎ ይታየናል።

የአዲስ አበባ የባህል ቤቶች ኢትዮጵያን በአንዲት ጠባብ ክፍል ውስጥ ሥጋ ለብሳና አካል ተጎናጽፋ የምንመለከትባቸው ድንቅ የትዕይንት ማዕከላት ናቸው። በእያንዳንዱ የባህል ማዕከል የኢትዮጵያውያን ብሔሮችና ብሔረሰቦችን ሙዚቃና ጭፈራ ለማዳመጥ የታደልነው ከአዲስ ኅብረ-ብሔራዊነት በመነጨ ነው።

ከአራቱም የኢትዮጵያ ማዕዘናት የመጡ ዜጎች እና የውጭ ሀገር ሰዎች በከተማዋ የተለያዩ ቦታዎች ታሪክን በሚያወሱ ሠፈሮች ኑሯቸውን

**መርካቶ በንግድ የተሠማሩት የከተማ ነዋሪዎች ከመላው ኢትዮጵያ ከሚመጡ ሰዎች ጋር የፈጠሩት የራሱ ውብ የሆነ ቀለም አለው። ፒያሳ አካባቢ የጥንቱ የአዲስ አበባ መልክ ይስተዋላል**

መሥርተው ይገኛሉ። በዚህም ባህል፣ ጥበብ እና ታሪክ ተዋሕደው መላው ኢትዮጵያውያንን የሚገልፁ በርካታ ሠፈሮች በመዲናይቱ ይገኛሉ። የአዲስ ሠፈሮቿ የማይዳሰሱ ቅርሶች ናቸው። ስያሜያቸውም ከውጭ ሀገር ዜጎች ጋር፣ ከብሔረሰቦችና ክፍላተ ሀገራት እንዲሁም ከመኳንንቶች እና በዋነኝነት ከአርበኞች ጋር የበለጠ ቁርኝት አላቸው።

በሌላ በኩል የአንድ አካባቢ ማኅበረሰብ ሰዎች አንዱ አንዱን እየሳበ በብዛት የኖሩባቸው ሠፈሮች በብሔሩ ስም ተሰይሞ በአዲስ አበባ ውስጥ እናገኘዋለን፡ ቦሌ አካባቢ የሚገኘው ወሎ ሠፈር፣ መርካቶ የሚገኘው ጎጃም ሠፈር፣ በማዘጋጃ ጀርባ ፖስታ ቤት አካባቢ የሚገኘው ወለጋ ሠፈር፤ እሪ በከንቱ አካባቢ የሚገኘው ጅሩ ሠፈር፣ ሽሮሜዳ አካባቢ ጋሞ ሠፈር፣ አዲስ ከተማ ትምህርት ቤት ጀርባ ቸሃ ሠፈር፣ አራት ኪሎ ባሻ ወልዴ ችሎት አካባቢ ደግሞ ሶዶ ሠፈር፣ እንዲሁም ኮልፌ አካባቢ ምሁር ጉራጌ ሠፈር ተብለው ይጠራሉ። ቀድሞ ዘመድ እና ዘር እየፈለጉ የኖሩ ሰዎች ከተማዋን እየተላመዱ ሲመጡ ከሠፈሮቻቸው ወጥተው ወልደው፣ ተዋልደው፣ ትስሥራቸውን ጠብቀው፤ ባህል፣ እምነት፣ ወግ፣ እሴታቸውን በጋራ እያከበሩ የአብሮ መኖር ተምሳሌትነታቸውን እያንጸባረቁ በአራቱም አቅጣጫ ላይ ሠፍረው እናገኛቸዋለን።

በዚህም አዲስ አበባ ለኢትዮጵያ ትልቅ ምሳሌ ናት። የአንድ አካባቢ ነዋሪዎችን፣ የተቋም ሠራተኞች፣ የንግድ ሥፍራዎች፣ ትምህርት ቤቶች፣ የእድር እና እቁብ አባላትን… በመመልከት አዲስ አበባ የብሔር ብሔረሰቦች መኖሪያ መሆኗን መመስከር ይቻላል። ለዘመናት ተቻችሎና ተከባብሮ እንደየዐቅሙ ሁሉም የሚኖርባት ከተማ መሆኗንም መግለጽ ቀላል ነው። ይህንን ሐቅ የተለያዩ ሰዎች በተለያዩ አጋጣሚዎች ሲናገሩ ተደምጠዋል፤ ነዋሪዎችም አጣጥመዋል። ይኼ በጣም አስፈላጊና በመላው ኢትዮጵያ ሊሰፋና ልናባዛው የሚያስፈልግ መልካም ተሞክሮ ነው።

# አዲስ አበባ

የሀገራችን ዋና መዲና፤ የተለያዩ አህጉር አቀፍና ዓለም አቀፍ ተቋማት መቀመጫ፤ የአፍሪካ ሕብረት ጽሕፈት ቤት መቀመጫ፤ ከዓለም ሦስተኛዋ የዲፕሎማቲክ ከተማ፤ የበርካታ ኤምባሲዎች መቀመጫ፤ ለኮንፈረንስ ቱሪዝም ተመራጭ ከተማ፤ በርካታ ታሪካዊና ተፈጥሯዊ የቱሪስት መስሕብ የታደለች፤ የሁሉም ኢትዮጵያውያን መናኸሪያ ከመሆን ባለፈ የአፍሪካውያን መዲና



በዚህ ጉዳይ ላይ በአንድ ወቅት ረዳት ፕሮፌሰር ነብዩ ባዬ ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ፤ አዲስ አበባ የመንግሥት መናገሻና የሀገሪቷ የፖለቲካ ማዕከል በመሆኗ ኢትዮጵያውያን ለዘመናት ተሰባስበው የኖሩባት ከተማ መሆኗን ተናግረዋል። የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እና ፖሊሲ የሚመሩ ማዕከላት የሚገኙባት ከተማ በመሆኗ በሀገሪቱ ደረጃ ትልልቅ ፖለቲካዊ ውሳኔዎች የሚወሰነውም በአዲስ አበባ ነው።

ዓለም አቀፍ የፖለቲካ ማዕከል ከመሆኗ ባሻገር የመንግሥት መቀመጫነቷ እና መናገሻነቷ እንዲሁም በዘመናት በሄደችባቸው የዕድገት ጎዳናዎች ከሁሉም የኢትዮጵያ ክፍል የመጡ ኢትዮጵያውያን ሰፍረዋል። ተድረዋል፣ ወልደው አሳድገዋል። ልጆቹ ደግሞ የኢትዮጵያን መልክ በአዲስ አበባ የበለጠ እያደመቁ እና እያጎሉ ለዘመናት ተጉዘው አሁን ላይ ከተማዋ ልዩ ባሕርይ ያለው የአብሮነት ኅብረት እንዲኖራት ማስቻላቸውን አመላክተዋል።

ረዳት ፕሮፌሰር ነብዩ እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ ምን ትመስላለች ብሎ መጠየቅ ለሚፈልግ ሰው ምላሹ ‹‹አዲስ አበባን›› የሚል ከሆነ ትክክል ነው። አዲስ አበባ ውስጥ የሌለ ሃይማኖት፣ የማይነገር ቋንቋ፣ የማይታይ ባህልና ብሔረሰብ የለም። ይሄ ሁሉ መስተጋብር አዲስ አበባን የባህሎች፣ የማንነቶችና የሃይማኖቶች መናኸሪያና መገለጫ ከተማ እንድትሆን አድርጓታል። ይኼ መስተጋብር እየተሻሻለ ለዘመናት ተጉዞ አሁን ላይ በጣም በብዙና በዝርዝር ሊጠና የሚችል የፍቅር እና የአንድነት ግንኙነት ፈጥሯል።

መርካቶ በንግድ የተሠማሩት የከተማ ነዋሪዎች ከመላው ኢትዮጵያ ከሚመጡ ሰዎች ጋር የፈጠሩት የራሱ ውብ የሆነ ቀለም አለው። ፒያሳ አካባቢ የጥንቱ የአዲስ አበባ መልክ እንደሚስተዋል ይናገራሉ። እንጦጦ አካባቢ ብዛት ያላቸው የሃይማኖት ተቋማት ያሉበት አሁን ደግሞ የለማው የእንጦጦ ፓርክ የሚገኝባት ናት። ቦሌ ደግሞ ዘመናዊነት እና ዓለም አቀፋዊነትን የተላበሰ አካባቢ መሆኑን አንሥተዋል። እነኚህ ሁሉ በየጊዜው የሚከናወኑ የከተማዋ ዕድገቶች አዲስ አበባ ኢትዮጵያውያንን እያቀፈች፣ እየጨመረች፣ ከሁሉም አቅጣጫዎች ሁሉንም እየአካተተች የባህሎች ኅብር መገለጫ መሆን ችላለች።

አዲስ አበባ የሀገራችን ዋና መዲና፤ የተለያዩ አህጉር አቀፍና ዓለም አቀፍ ተቋማት መቀመጫ፤ የአፍሪካ ሕብረት ጽሕፈት ቤት መቀመጫ፤ ከዓለም ሦስተኛዋ የዲፕሎማቲክ ከተማ፤ የበርካታ ኤምባሲዎች መቀመጫ፤ ለኮንፈረንስ ቱሪዝም ተመራጭ ከተማ፤ በርካታ ታሪካዊና ተፈጥሯዊ የቱሪስት መስሕብ የታደለች፤ የሁሉም ኢትዮጵያውያን መናኸሪያ ከመሆን ባለፈ የአፍሪካውያን መዲና መሆኗ ይታወቃል።

‹‹ኅብረ-ብሔራዊነት ልክ እንደ አትክልት ቁርጥ ነው!›› እንደሚባለው የተለያዩ አትክልቶች ሙዝ፣ አቦካዶ፣ ቲማቲም፣ ቃሪያ፣ ቆስጣ፣ ሰላጣ ወዘተ ተቀላቅለው ስንመገባቸው የሚፈጥሩት ጣዕም እጅግ ይለያል፤ የሚያስገኙት ንጥረ ነገርም ጤናማ ያደርገናል። በተመሳሳይም አዲስ አበባ የኅብረ ብሔራዊነትና የመቻቻል ከተማ ሆና ትንሿን ኢትዮጵያ መስላ ልጆቿን በፍቅርና በአንድነት ማኖሯን ቀጥላለች!





የብሔራዊ ቴአትር ቤት ተጫዋቾች በ1969 ዓ.ም.

# አዲስ - ጥበብ





ከቸርችል ወደ ማዘጋጃ ቤት በ1950ዎቹ

# አዲስ - ጥበብ

**ስሜነህ ደስታ**

የሁሉም ኢትዮጵያውያን ኅብረብሔራዊ ከተማ የሆነችው መዲናችን አዲስ አበባ ከኪነ ጥበብ ጋር ያላት ቁርኝት እጅግ ጥልቅና ትልቅ ነው። በዚህ ጽሑፍ አዲስ አበባን በኪነ-ጥበብ መነጽር እንቃኛታለን።

ቀደም ሲል ዋና ከተማ ከነበረችው እንጦጦ ከተማ ላይ ሆነው የአዲስ አበባን ዕድገት የተመለከቱ ነዋሪዎቿ በከተማዋ ፈጣን ዕድገት ይገረሙ ነበር። በእምነት ገብረአምላክ የተባሉ ገጣሚም በ1950ዎቹ የአዲስ አበባን ውበት በገለጹበት ግጥማቸው የሚከተለውን ብለዋል።

**‹‹እንጦጦ ላይ ሆኜ አዲስን ሳያት፣**
**ባለፈርጥ ኮከብ መስላ አገኘኋት።››**

የሥነ ግጥም መምህርና ተመራማሪው ረዳት ፕሮፌሰር ብርሃኑ ገበየሁ " አዲስ አበባ በአማርኛ ሥነ ግጥም " በሚለው መጣጥፋቸው ይህን መንቶ ግጥም እንደሚከተለው ገልጸውታል። ‹‹የዚህ መንቶ ደራሲ፣ የአዲስ አበባ ውበት በድንገት ያነቃው ያነሆለለው ባለቅኔ ነው። ከግጥሙ ዓውደ ንባብ ተነሥተን ስናሰላስል፤ የገጣሚው አድናቆት የመነጨው ከምሽት ትዕይንት ነው ማለት ይቻላል። ለምን ቢሉ ለአድናቆቱ ማንጸሪያ፣ ለአድናቆቱ መያዣ የመረጠው ምስል ባለፈርጥ ኮከብ ነውና፤ አንድም ኮከብ በምናባችን የሚከሠተው የብርሃን ምስል ነውና። አገላለጹ ውብ ነው፤ ምስሉም የተባና የደመቀ። እናም በእነዚህ ስንኞች አዲስ [አዲስ አበባ] ለገጣሚው ብቻ ሳይሆን ለተደራሲውም አዲስ ውበት ትሆናለች።›› ("አዲስ አበባ ባለፈውና በአዲሱ ሚሊኒየም" በተሰኘው መድብል)

ከአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት በቸርችል ጎዳና ወደ መስቀል አደባባይ የሚዘልቀው አውራ ጎዳና ‹‹እይታን እንደ ቅርስ›› በሚል መርሕ በከተማ አስተዳደሩ የማስፋፋትና የማስዋብ ተግባር ተከናውኖ ሰኔ 6 ቀን 2013 ዓ.ም ተመርቋል። በአውራ መንገዱ ግራና ቀኝ ለእግረኛ መተላለፊያና ለብስክሌት ጋላቢዎች በሚያመች መልኩ እንዲሰፋ ተደርጓል። ከዚህ በተጨማሪ

በዕፅዋት፣ በአበባ እና በተለያዩ የዛፍ ዘሮች አካባቢው ተውቧል። እግረኞች፣ ከመስቀል አደባባይ እስከ ፒያሳ ሲጓዙ ዐረፍ የሚሉበት፣ ከፈለጉም ቁጭ ብለው የሚያወጉበት መቀመጫዎችም ተበጅተዋል።

በተለይ የቸርችል ጎዳናን የምሽት ገጽታ በኤሌክትሪክ ብርሃን ሕብረ ቀለማት አሸብርቆ ለተመለከተ ሰው የገጣሚ በእምነት ገብረ አምላክ ግጥምን የሚያውቅ ከሆነ ያስታውሳል። የእሳቸውን ግጥም በመዋስም

**‹‹ማዘጋጃ ቤት ሆኜ ቸርችልን ሳያት፣**
**ባለፈርጥ ኮከብ መስላ አገኘኋት።››** ሲል ይችላል። ጎዳናው በጣም በሚያምር ሁኔታ ዐይነ ግቡ በመሆን ለመንፈስ ርካታን በሚሰጥ መልኩ ተውቦ ተሠርቷልና ቢባል ይገባዋል።

አዲስ አበባ በግጥም ስትወሳ አብዛኛውን ጊዜ የሚነገር መንቶ ግጥም አለ። ይኸውም

**‹‹ወይ አዲስ አበባ ወይ አራዳ ሆይ**
**ሀገርም እንደሰው ይናፍቃል ወይ››**

የሚለው የናፍቆት ግጥም ነው። በዚህ ግጥም ላይ ሐሳባቸውን የሰጡት ረዳት ፕሮፌሰር ብርሃኑ ገበየሁ ከላይ በተገለጸው መጣጥፋቸው ላይ የሚከተለውን ብለዋል። ‹‹ በአማርኛ ሥነ ግጥም የአዲስ አበባ ምስል ተደጋግሞና ተዘውትሮ የሚገኘው በትዝታና ናፍቆት ግጥሞች ውስጥ ነው፤ ወይም በስደት ግጥሞች ውስጥ ነው። የሰው ልጅ ገነትም ሆኖ የትውልድ ቀየውን፣ በተራዛሚውም አገሩንና ወንዙን አይረሳም እንዲል ሐዲስ። የአማርኛ ገጣምያን ባሕር ማዶ ለትምህርት ወይ ለሥራ በስደት ሲኖሩ፤ ቃሉ ይለያይ እንጂ የዝማሬያቸው ቃና የቅኔያቸው መንፈስ፤ ‹‹ወይ አዲስ አበባ ወይ አራዳ ሆይ ሀገርም እንደሰው ይናፍቃል ወይ›› የሚል ነው። ይህ ዓይነቱ የልብና የቀልብ መሸፈት ከአያሌ ስሜቶች ሊቀሰቀስ ይችላል። ከናፍቆትና ከትዝታ፣ ከመከፋትና ከመገፋት፣ ከባይተዋርነትና ከብቸኝነት፣ ከማንሜነትና ከራስ ጥል። በዚህ ረገድ የመንግሥቱ ለማና የገብረ ክርስቶስ ደስታ ግጥሞች ሁነኛ የዘመናቸው ወኪሎች ናቸው።››

ስለ አራዳ ከተነሣ በቃል ግጥም የተባሉትን አንሥተን እንለፍ።

**የአራዳ ዘበኛ ክብሬ ነው ሞገሴ፣**
**በቸገረኝ ጊዜ የሚደርስ ለነፍሴ።**

ይህ መንቶ ግጥም በወቅቱ ከተማዋን እንደ ፖሊስ ሆነው ጥበቃ ያደርጉ ለነበሩ አገልጋዮች የተገጠመ ነው። የአራዳ ዘበኞች ምን ያህል ተግባራቸውን በትጋት እንደሚፈጽሙም የሚያመላክት ነው። በተለይ በምሽት ጊዜ ለሚፈጸም ችግር ለነፍስ የሚደርሱ መሆናቸውን ያሳይል።

**ምነው ባደረገኝ ከአራዳ ልጅ መሳ፣**



የሙዚቃ ዝግጅት በ1952 ዓ.ም.

**እንኳን ለገንዘቡ ለነፍሱ የማይሳሳ።**

አራዳ ሲኒማ አምፔር፣ ሲኒማ ኢትዮጵያ እና ሲኒማ ዓድዋ (ፈርሷል፤ አራዳ ሕንጻ ተሠርቶበታል) የሚገኙበት ቦታ ነው። የአራዳ ልጆች ሲኒማ በመመልከት ለሌሎች አዲስ የሆኑ ድርጊቶችን ማሳየት የተለመደ ነበር። አርቲስት ዓለማየሁ እሸቴ በፊልም የሚያያቸውን ቴክሳሶች በመምሰል በፈረስ አራዳን ይዘዋወር እንደነበረ በመገናኛ ብዙኀን ተናግሯል።

ስለ አራዳ ካነሣን አይቀር አጠገቡ ስላለው ደጃች ውቤ ሠፈር የተባለውን ቃል ግጥም እንመልከት።

**ደጃች ውቤ ሠፈር ምን ሠፈር ሆነች፣**
**ያችም ልጅ አገባች ያችም ልጅ ታጨች።**

ደጃች ውቤ ሠፈር ከአራዳ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ወደ አፍንጮ በር መሄጃው ላይ ይገኛል። ሠፈሩ በስማቸው የተሰየመላቸው ደጃች ውቤ መኳንንት እና ባለሃብት የነበሩ እንዲሁም ዘውዲቱ ምኒልክን አግብተው የኖሩ ታዋቂ ሰው ናቸው። አዲስ አበባ ሬስቶራንት መኖሪያቸው ነበር። በዚያ አካባቢ ቡና ቤቶችና የጭፈራ ቤቶች ይበዙ ነበር። በእነዚህ ቤቶች ደግሞ የሚሠሩ ሴቶች ደንበኞቻቸውን እንደፍላጎታቸው ያስተናግዳሉ። ከላይ የቀረበው ግጥም ሲታይ ከዚህ በፊት እንደፍላጎቱ ሲስተናገድ የቆየ ደንበኛ፣ አሁን የለመዳቸው አግብተውና ታጭተው በሥፍራው ሲያጣቸው እነሱ የሌሉበት ደጃች ውቤ ሠፈርን እንደሠፈር አለማየቱን የሚያመላክት ነው። የዘመኑ ወጣቶች ሠፈሩን በተለየ ሁኔታ ለጭፈራ ያዘወትሩት ነበር።

ስለአዲስ አበባ ከአነሣን መርካቶን አለማንሣት ከባድ ነው። ባለቅኔው ሎሬት ጸጋዬ ገብረ መድኅን በ1966 ዓ.ም. በአሳተሙት ‹‹እሳት ወይ አበባ›› በሚለው የግጥም መድብላቸው ላይ “አይ መርካቶ” የሚል ርእስ ያለው ግጥም መጻፋቸውን ብናነሣ ጥሩ ነው። ከዚህ ግጥም የመጀመሪያውን አንጓ ወስደን እንመልከት

**አገር ከየጎራው ወጥቶ**
**አንቺን ብሎ ነቅሎ ወጥቶ**
**ግሣንግሡን ጓዙን ሞልቶ**
**ኍልቆ መሣፍርትሽ ፈልቶ**
**ባንቺ ባዝኖ ተንከራትቶ**
**እንደባዘቶ ተባዝቶ**

አዲስ አበባ ከተማን በተመለከተ የተዘፈኑ ዘፈኖች ይዘት ስንመለከት ከተማዋ በጠዋት ተኳኩላ ለአሸናፊነት ብቅ እንዳለች ወጣት እንስት ተመስላ ታይታለች።

**ተንጠራውዞ ዋትቶ ዋትቶ**
**አይ መርካቶ……**

በአንዳንድ አካባቢዎች ቀንን መሠረት በማድረግ የሰኞ፣ የማክሰኞ፣ የረቡዕ፣ ወዘተ. ተብሎ ስያሜ ወጥቶላቸው በዕለቱ ገበያ ቆሞ ከፍተኛ ግብይት ይከናወናል። መርካቶ ግን ሁሌም ገበያ አለ። ግብይቱ ቀዝቀዝ ብሎ የሚታይበት ቀን ቢኖር እሑድ ብቻ ነው። መርካቶ ለመገበያየት የሚመጣው ሕዝብ ከሁሉም የኢትዮጵያ አቅጣጫ ነው ማለት ይቻላል። ለዚህም ነው ገጣሚው በ1965 ዓ.ም. ያዩትን ሲጽፉ “አገር ከየጎራው ወጥቶ፣ አንቺን ብሎ ነቅሎ ወጥቶ” ያሉት። ለመሸጥ ወይም ለመግዛት የሚመጣውን ሰውና ጓዝ በመመልከት ደግሞ ኍልቆ መሣፍርትሽ ፈልቶ” በማለት ገልጸውታል። መርካቶ በውስጧ ምናለሽ፣ ቆርቆሮ፣ ጋዝ፣ ዶሮ፣ ቦንብ፣ አውቶቢስ፣ ጭድ፣ ጫት፣ ቆጮ፣ ብረት፣ ቡና፣ ሶማሌ፣ ሳጥን፣ ጠረጴዛ፣ ሸክላ፣ ፎጼ፣ ሚሊቴሪ፣ ድር፣ ሚስማር፣ ሸማ፣ ሸራ፣ ወዘተ. ተራ በሚል የተሰየሙ መገበያያ ሥፍራዎች አሏት። ሎሬትም በዚህ ሥፍራ የተመለከቱትን ነው በግጥም የገለጹት።

ሎሬት ስለ መርካቶ ይህን ሲሉ ጌታቸው ካሳ ደግሞ ስለመርካቶ የሚከተለውን አዚሟል።

**ውብ አዲስ አበባ የትውልድ ሀገሬ**
**ያደኩብሽ መንደር መርካቶ ሰፈሬ**
**ከልጅነት እስከዕውቀት ያየሁት ኑሮዬ**
**ከልቤ ተጽፎ ተሥሎ ከላዬ…**

ከግጥም መምህሩና ተመራማሪው እይታ በመቀጠል ስለ አዲስ አበባ ከተማ የተዘፈኑ የተወሰኑ ዘፈኖችን እንመልከት።

**አዲስ አበባ ቤቴ አዲስ አበባ ቤቴ**
**ሸጋ ልጅ ቆንጆ ልጅ አለች ጎረቤቴ**
**ኧረ እንዲያው ይመኙሻል ኧረ እንዲያው ይመኙሻል**
**ኧረ እንዲያው ይመኙሻል ኧረ እንዲያው ይመኙሻል**
**በምኞት ቢጓጉ ወዴት ያገኙሻል። …**

(ዓለማየሁ እሸቴ)

ይህን የዓለማየሁ እሸቴ ዘፈን ትዝታ ቀስቃሽ ነው።

**ኤሌ ኤሌ አባ - አዲስ አበባ**
**ኤሌ ኤሌ አባ - አዲስ አበባ**
**መዓዛዋ ጠራኝ - አዲስ አበባ**

**ስሟ ሲነሣ - አዲስ አበባ**
**በንጋት ተኩላ- አዲስ አበባ**
**በአበባው ሞይሳ - አዲስ አበባ**
**ዐይኗም ይናጋራል - አዲስ አበባ**
**ፍቅሯ እያደራ - አዲስ አበባ**
**ውበት አልብሷታል - አዲስ አበባ**
**አቤት የእሱ ሥራ - አዲስ አበባ ...**

ብርሃኑ ተዘራ እና ዮሐንስ በቀለ (ቶኪቻው)

ይህ የብርሃኑ ተዘራ ዘፈን አዲስ አበባ ከተማ ስሟ ሲነሣ መዓዛዋ ያውደኛል ይለናል፤ መልካም ገጽታዋን ለማድነቅ የተባለ ነው። ከተማዋ በንጋት ተጣጥባ ተኳኩላ በለጋነቷ (በአበባነቷ) ለአሸናፊነት በተዘጋጀች እንስት ተመስላ ቀርባለች (ሞይሳ በኦሮሚኛ አሸናፊ ማለት ነው)። በተጨማሪም ከተማዋ ውበቷ (መልካምነቷ) አማሎት አምላኩን ያደንቃል፤ ያሞግሳል።

ታምራት ደስታም ስለ አዲስ አበባ ሲዘፍን ተመሳሳይ ይዘት ያለው ከተማዋ የፍቅርና የጥቁር ሕዝብ መሰብሰቢያ እንደሆነች፣ በክፉ ቀን ሳትነፍግና ሳትሰስት አምኗት ለመጣ ለአዳም ዘር ሁሉ መጠለያ ሆና ያላትን የቸረች መሆኗን እንደሚከተለው አቅርቧል።

**አንቺ የፍቅር አንባ የአፍሪካ መዲና**
**አንቺ የፍቅር አንባ ሀገሬ አዲስ አበባ**
**የጥቁር ሕዝብ መናኸሪያ**
**የፍቅር መጀመሪያ**
**ተወልጄ ያደኩብሽ**
**ብዙ ብዙ ያዩብሽ ...**
**አንቺን አምኖ ተጠግቶ...**

አዲስ አበባ ከተማን በተመለከተ የተዘፈኑ ዘፈኖች ይዘት ስንመለከት ከተማዋ በጠዋት ተኳኩላ ለአሸናፊነት ብቅ እንዳለች ወጣት እንስት ተመስላ ታይታለች። ከዚህ በተጨማሪ እንደስሟ የፈካች አዲስ አበባ መሆኗ እና ኅብረ ብሔራዊነት ያላት የኢትዮጵያ ተምሳሌትነቷ ተጠቅሷል። ውበቷ በውስጧ ካላት ሰላምና ከኢትዮጵያ ስመ ገናናነት የመነጨ መሆኑም ተወስቷል። ከተማዋ የጥቁር ሕዝቦች መዲና እና መመኪያ ከመሆኗ በተጨማሪ በተለይ ክፉ ቀን ላጋጠማቸው የአዳም ዘር ለሆኑ በሙሉ ሳትነፍግና ሳትሰስት መጠለያ ሆና ያላትን የቸረች መሆኗ በሚያምር ድምፅና ጆሮ ገብ በሆነ ሙዚቃ ቀርቧል።


ይህ ጽሑፍ አዲስ አበባ ከተማ በኪነጥበብ በምን መልኩ ቀርባለች ለሚለው ዳሰሳ ለማድረግ የተሞከረበት ነው።






አዲስ አበባ በ1956 ዓ.ም

# አዲስ አበባን በታሪክ መነጽር





ቤተ መንግስት በ1953 ዓ.ም.



ቤተ መንግስት በ2015 ዓ.ም.

# አዲስ አበባ በታሪክ መነጽር

**ተስፋ ፈሩ**

አዲስ አበባ ከተማ ከባህር ጠለል በላይ በሦስት ሺሕ ሜትር ከፍታ ላይ ትገኛለች። የአየር ጠባይዋ ለነዋሪዎቿም ሆነ ለእንግዳ ጎቢኝዎች ተስማሚና ተመራጭ ነው። አዲስ አበባ ከሌሎች የአፍሪካ ከተሞች አመሠራረት በተለየ ሁኔታ ሙሉ በሙሉ በኢትዮጵያውያን የተቆረቆረችና የለማች ከተማ መሆኗን መረጃዎች ያመለክታሉ። ይህች የአፍሪካ መዲና በየዘመኑ የተከሠቱትን አዳዲስ የሥልጣኔ ውጤቶችን በመቀበልና በመላ ሀገሪቱ በማሠራጨት የተጫወተችው ሚና ከፍተኛ ነው።

ከአዲስ አበባ ከተማ መመሥረት ጥቂት ጊዜ በፊት እ.ኤ.አ በ1884 ዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ እንጦጦን የኢትዮጵያ ዋና ከተማ አድርገው ነበር። ከጊዜያት በኋላ ግን እንጦጦ የማያረካ ሆኖ ተገኘ። የዚህም ዋናው ምክንያቱ ቀዝቃዛ አየር፣ የውሃ እጥረትን የመሳሰሉ ነገሮች ነበሩ።

እ.ኤ.አ በ1886 አዲስ አበባ የሸዋ ግዛት ዋና ከተማ ሆነ። እ.ኤ.አ በ1887 ምኒልክ የባለቤታቸውን ቤት ቤተ መንግሥት ይሆን ዘንድ ሰፊ አድርገው አሠሩት። ይህም ቦታ እስከዛሬ ድረስ የመንግሥት መቀመጫ ነው። እ.ኤ.አ በ1889 ምኒልክ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ሲሆኑ አዲስ አበባም የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ሆነች። ከተማይቱም በፍጥነት ማደግ ጀመረች። አካባቢው ይማርክ የነበረው መኳንንትን ብቻ አልነበረም። ነገር ግን ባለሙያዎችን፣ ነጋዴዎችንና የውጭ ጎብኚዎችንም ይማርክ ነበር።

አዲስ ማለዳ እ.አ.አ. ታኅሣሥ 12 ቀን 2018 አዲስ አበባን በተመለከተ ባሥነበበው ጽሑፍ ፒትር ጋረስተን የተባሉ የታሪክ አጥኚ ስለከተማዋ ያስቀመጡትን ምልከታ ይዞ ወጥቷል። የታሪክ አጥኚው ለሦስተኛ ዲግሪ (PhD) ማሟያቸው ‹የአዲስ አበባ ታሪክ ከጽሕፈትዋ 1879 እስከ 1902› በሚል ርእስ ያቀረቡት የጥናት ጽሑፍ አዲስ አበባ አገር በቀል (indigenous) ከተማ እንደሆነች ያትታል። ይሄው ጥናታዊ ጽሑፍ በመደምደሚያ ክፍሉ አዲስ አበባ እንዴት በጊዜ ሒደት ለንጉሣዊው ግዛት የምጣኔ ሀብት እምብርት እየሆነች እንደመጣች ዘርዝሮ አስቀምጧል።


ዕውቁ የታሪክ ተመራማሪ ፕሮፌሰር ሪቻርድ ፓንክረስ ‹ሚኒልክ እና የአዲስ አበባ መቆርቆር› በሚል ርእስ እ.ኤ.አ. በ1961



አቡነ ጴጥሮስ አደባባይ በ1952 ዓ.ም



አዲስ አበባ በተመሠረተችበት ወቅት የነበሩ ቤቶች



በጻፉት ጥናታቸው እንደሚነግሩን፥ ዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ በማገዶ እጥረት የተጠቃችውን አዲስ አበባን በአዲስ ዓለም ሊተኳት አስበው ነበር። ዐፄው ቤተ መንግሥታቸውን በአዲስ ዓለም ማሳነጽ ሲጀምሩ፣ የጣሊያን መልእክተኞች ለጋሲዮናቸውን "አይቀሬ" ወደምትመስለው ዋና ከተማ አዲስ ዓለም ቸኩለው አዛውረው ነበር። የሆነ ሆኖ ለማገዶ ፍጆታ የሚውል ቶሎ፣ ቶሎ የሚበቅል የባሕር ዛፍ ወደ ኢትዮጵያ በመግባቱ የማገዶ ችግሩ በመቀረፉ እንዲሁም ውኃ ከጉድጓድ ማውጣት እና በቧንቧ ማጓጓዝ በመቻሉ፣ እና ሌሎችም የመገናኛ ዘዴዎች ወደ አገር ውስጥ በፍጥነት በመግባታቸው አዲስ አበባ ዘለቄታን አግኝታለች።

በ1900ዎቹ ገደማ የአዲስ አበባ ሕዝብ 65,000 ገደማ እንደነበር ሪቻርድ ፓንክረስት ዶክተር መረብ ‹ኢምፕሬሽን ደ ኢትዮፒ› በሚል የጻፈውን መጽሐፍ ጠቅሰው ዘግበዋል።

በአዲስ አበባ የመጀመሪያዎቹ ነዋሪዎች ቤታቸውን ክብ ቅርፅ ባለው ጎጆ መልክ ይሠሩ ነበር። ግድግዳውን ከሳር ጋር በተቀላቀለ ጭቃ እንጨት ላይ ተጣብቆ፣ ጣራውም የሳር ክዳን ነበር። የአዲስ አበባ ሕዝብ ቁጥር መጨመር የጀመረው ብዙ ሰው ከገጠር ወደ ከተማ ባደረገው ፍልሰት ነበር። ይህም የታቀደበት አልነበረም። በዚህ ጊዜ ነበር መኳንንቱ አንድ ቦታ ላይ ለመስፈር ያተኮሩት።

ከጣሊያን ወረራ በፊትም ከተማው ጠንካራ መዋቅር የያዘ ነበር። በታሪክ አጥኚው በሪቻርድ ፓንክረስትም እይታ የአዲስ አበባ ሕዝብ ቁጥር የጨመረው በክፍለ ሀገር መሪዎችና በወታደሮቻቸው እ.ኤ.አ በ1892 በነበረው ድርቅ ምክንያትና በመጨረሻም በዓድዋ ጦርነት ምክንያት ነበር። ሌላው ምክንያት ደግሞ እ.ኤ.አ በ1902 የወጣው የመሬት ሕግና በ20ኛው ክፍለ ዘመን የተጀመረው ባቡር፣ የታየው የትራንስፖርት ዕድገትና በ1909 ዓ.ም. የተቋቋመው ማዘጋጃ ቤት እንዲሁም ሌሎችም ዕድገቶች ናቸው። ከእነዚህ የከተማዋን ይዘት ከቀየሩ ተጠቃሽ ምክንያቶች መካከል የማዘጋጃ ቤት መቋቋምን በዝርዝር መመልከት ተገቢ ይሆናል።

የአዲስ አበባ ከተማ የሕዝብ ቁጥር መጨመር፣ የኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ እና የቆዳ ስፋት እያደገ በመምጣቱ እንዲሁም ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ወደ ከተማዋ የሚመጡ ባለጉዳዮችን በአግባቡ ለማስተናገድ በማስፈለጉ በ1909 ዓ.ም የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ተቋቋመ። የማዘጋጃ ቤት አስተዳደር ከተቋቋመም በኋላ ሊሎ ሽፋኑ በተባለ ፈንረሳዊ እና አድለቢ በተባለ ሶሪያዊ ግሪት ማዘጋጃ ቤቱ ዓድዋ ሲኒማ ተብሎ የሚጠራው አካባቢ እንዲመሠረት ተደረገ። ማዘጋጃ ቤቱም የከተማው "የማኅበር ቤት" ተብሎ ይጠራ ነበር። ስያሜው

የተሰጠውም ማዘጋጃ ቤቱ እንዲመሠረት ግፊት ሲያደርጉ በነበሩት በሶሪያው አድሊቢ ነው። በኋላም "የከተማ ማኅበር ቤት" የሚለው ስያሜ "municipality" የሚለውን የእንግሊዘኛ ቃል አይወክልም በሚል በኅሩይ ወልደ ሥላሴ አማካኝነት በ1920 ዓ.ም ማዘጋጃ ቤት የሚል ስያሜ እንደተሰጠው በታሪክ ሰፍሯል።

በወቅቱ የከተማዋ ማዘጋጃ ቤት ለአዲስ አበባ ከተማ ዕድገትና ለከተማዋ ሕዝብ ደኅንነት ሲባል የሚያከናውናቸውን ተግባራት በ16 ዋና ዋና ክፍሎች ከ250 ባልበለጡ ሠራተኞች ይፈጽም ነበር። የሥራ ክፍሎቹም የከንቲባ ጽሕፈት ቤት፣ የርስት ክፍል፣ የካርታ ማንሣትና የግምት ክፍል፣ የዳኝነት ክፍል፣ የአራዳ ዘበኛ የተሽከርካሪና የመንጃ ፈቃድ ክፍል/የቁማር ጨዋታ ቁጥጥር ክፍልን ጨምሮ/፣ የጽዳት ክፍል፣ የገንዘብና የሥራ መቆጣጠሪያ ክፍል፣ የምስጢር ክፍል/የሕክምና ክፍል ወይም ልዩ ጓዳ/፣ የውል ክፍል፣ የእሳትና አደጋ መከላከል ክፍልና የጋራዥ ክፍል የተባሉት ነበሩ። እነዚህ የሥራ ክፍሎች ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ እያንዳንዱ ክፍል ንኡስ ቅርንጫፎች ነበሩት። ማዘጋጃ ቤቱ ከላይ የተዘረዘሩት ዋና ዋና ክፍሎች ይኑሩት እንጅ ለከተማዋ ዕድገት የነበረው አስተዋፅኦ አመርቂ እንዳልነበር የተለያዩ ጽሑፎች ያስረዳሉ። የአዲስ አበባ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ከከተማዋ ዕድገት ጋር ተያይዞ የመጣውን የነዋሪዎች ችግር ለማሻሻል እና የተሻለ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል አደረጃጀት እና ሕንጻ በማስፈለጉ ዛሬ በማገልገል ላይ የሚገኘው ማዘጋጃ ቤት ሕንጻ ተገንብቷል።

አዲስ አበባ ከተቆረቆረች ጊዜ ጀምሮ ሌሎች ጉልህ የሥልጣኔ ተግባራት ተከሥተዋል። በአክሱም ነገሥታት ከታተሙት የመገበያያ ሳንቲሞች በኋላ ብሔራዊ ገንዘብ ታትሞ ለዝውውር የበቃውና የቴሌፎን አገልግሎት የተጀመረው ከአዲስ አበባ መመሥረት በኋላ በ1986 ዓ.ም ነው። በ1890 የሩስያ ቀይ መስቀል ሆስፒታል፣ በ1894 ዓ.ም. የኢትዮ ጅቡቲ የምድር ባቡር ኩባንያ፣ በ1897 ዓ.ም. የአቢሲንያ ባንክ፣ 1898 ዓ.ም. ዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት፣ በ1900 ዓ.ም. የእቴጌ ጣይቱ ሆቴልና የመጀመሪያው ሲኒማ ቤት እንዲሁም በ1902 ዓ.ም. የዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል ሥራቸውን እንደጀመሩ በታሪክ ተመዝግቧል። የዘመናዊ መንገድ ግንባታና የመኪና መምጣት፣ የቧንቧ ውሃ መዘርጋት፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ መመሥረት፣ የትላልቅ ሕንጻዎች መገንባት፣ የዘመናዊ ትምህርት መስፋፋት፣ ዩኒቨርስቲዎች መከፈት፣ የጤና ተቋማት መበራከት፣ የመንግሥት አስተዳደር ቅርጽ እየያዘ መምጣት አዲስ አበባን ወደ ሥልጣኔ ማዕከልነት ያሸጋገሯት የዘመኑ ክሥተቶች ናቸው።

እ.ኤ.አ በ1917 ራስ ተፈሪ መኮንን እንደራሴ ተደርገው ሲሾሙ የከተማው መዘመንና መስፋፋትም የሚያመጣውን



ፒያሳ ደጎል አደባባይ በ1953




ጥቅምም ስለተረዱ ራሳቸውን እያሳደጉ ላሉ ሰዎች ሀብት ማከፋፈል ጀመሩ። እ.ኤ.አ በ1918 ግልፅ በሆነ ሁኔታ የእንደራሴነት ሥልጣንን አገኙ። እ.ኤ.አ በ1926 እና በ1927ም ከፍተኛ የሆነ የኢኮኖሚ አብዮት ተካሄደ። ከካፒታል መጨመርም ጋር ተያይዞ የቡና ምርት በከፍተኛ ምርት ተመረተ። በዚህም የተጠቀሙት መሪዎች አዲስ እና በድንጋይ የተገጠሙ ቤቶችን ገነቡ። ከአውሮፓ በአስመጧቸው የቤት ዕቃዎች ቤታቸውን አስዋቡ። አውቶሞቢሎች አስገቡ። እንዲሁም ባንኮችንም አስፋፉ።

እ.ኤ.አ በ1930 ዓ.ጼ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ሲሆኑ በአዲስ አባባ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ማስገባትና ግንባታዎችን ማከናወናቸውን ቀጥለዋል። ከእነዚህም መካከል የኤሌክትሪክና የስልክ መስመሮች ዝርጋታ እንዲሁም የተለያዩ ተቋማት ግንባታዎች ይጠቀሳሉ። ዶክተር ሺመልስ ቦንሣ "አዲስ አበባ፣ ከየት ወደየት?" በሚል ርእስ ባዘጋጁት ጽሑፍ እንደሚገልጹት፤ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ከተማዋ ዘመናዊ ብቻ ሳይሆን ብሔራዊ ሆና እንድትፈጠር ወይንም እንድታድግ አቅደው ይሠሩ ስለነበር አዲስ አበባ ከተማም፣ የሀገርም ምልክት ሆና በእሷ ውስጥ ኢትዮጵያን በኢትዮጵያ ውስጥም እሷ እንድትታይ ሆና ነበር የተቀረጸችው።

ጣሊያኖች ኢትዮጵያ ላይ ዳግም ወረራ ሲፈጽሙ እ.ኤ.አ. በ1936 ወታደሮቻቸው ቀኝ ይገዟት ከነበረችው ኤርትራ ተነሥተው አዲስ አበባ ገቡ። ከጅቡቲ ጋር የተሳሰረው የባቡር መንገድም ሳይሰበር ቆየ። ጣሊያኖች ኢትዮጵያን ከያዙ በኋላ እ.ኤ.አ እስከ 1941 ድረስ አዲስ አበባን የጣሊያን ምሥራቅ አፍሪካ ዋና ከተማ አድርገው ቆይተዋል።

እ.ኤ.አ በ1941 ሜጀር ኦርዴዊንጌት በኃይለ ሥላሴ የጌዲዮን ጦርና የኢትዮጵያ ነጻነት ተዋጊዎች አማካኝነት ኢትዮጵያ ከጣሊያን አገዛዝ ነጻ ወጣች። ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ከኢትዮጵያ ከወጡ በአምስት ዓመታቸው ተመለሱ። በከተማዋ እምብርት አራት ኪሎ ላይ የሚገኘውን ሚያዚያ 27 (የድል ሐውልት) እንዲሠራም አደረጉ። ኢትዮጵያ ነጻ ከወጣች በኋላ አዲስ አበባ ከፍተኛ የሆነ የሕዝብ ቁጥር መጨመርና የኢኮኖሚ መቀዛቀዝ ገጠማት።

እ.ኤ.አ በ1946 ኃይለ ሥላሴ አዲስ አበባ የአፍሪካ ዋና ከተማ ትሆን ዘንድ ሞዴል ለማስያዝና ለማሳመር ታዋቂውን ማስተር ፕላነር ሰር ፓትሪክ አቤርክሮምቢን ጠሩት። አቤርክሮምቢ በተቀናጀ ሁኔታ ማስተር ፕላኑን ጀመረ። እ.ኤ.አ በ1943 ከነበረው የለንደን ትራፊክ ችግርም በመነሣት ማስተር ፕላኑን በዋናው የትራፊክ መንገዶች ሠፈሮችን በመከፋፈል ሠራው።

በኋላም የዐፄ ኃይለ ሥላሴ ህልም እውን ሆኖ እ.ኤ.አ በ1963 የአፍሪካ አንድነት ድርጅት መመሥረት እውን ሆነ። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ አዲስ አበባ የአፍሪካ የዲፕሎማሲ ማዕከልነቷ አንድ ብሎ ጀምሯል።

እ.ኤ.አ በ1974 ወታደራዊው ኃይል ደርግ ወደ ሥልጣን ከመጣ በኋላ በአዲስ አባባ ለሽያጭ ከተዘጋጁ ቤቶች ውስጥ ሁለት ሦስተኛው ወደ ኪራይ ቤት ተቀየረ። በ6 ነጥብ 7 በመቶ እያደገ የነበረው የሕዝብ ቁጥር ወደ 3 ነጥብ 7 በመቶ ቀነሰ። ሲኬ ፖሎኒ የተባለ ሀንጋሪያዊ አርክቴክትም የከተማይቱን ማስተር ፕላን እንዲሠራ በደርግ መንግሥት ተጠራ። ፖሎኒም መስቀል አደባባይን እንደአዲስ አስገነባው። የደርግ መንግሥትም መስቀል አደባባይን አብዮት አደባባይ በማለት ስሙን ቀየረው።






ከመስቀል አደባባይ እስከ ከንቲባ ጽሕፈት ቤት ድረስ የተሠራ ፕሮጀክትህ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እና ክብርት ከንቲባ አዳነች አቤቤ ሲመረቅ

14ቱ ክፍለ ሀገራት በነበሩበት የደርግ ዘመን ደግሞ አዲስ አበባ እንደ 15ኛ ክፍለ ሀገር ትቆጠር ነበር። በ1980 ዓ.ም የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (ኢሕዲሪ) ሲመሠረት ኢትዮጵያ የተካለለችው በ25 አስተዳደር አካባቢና በአምስት ራስ ገዞች ነበር። አዲስ አበባም ራሷን የቻለች የአስተዳደር አካባቢ እንድትሆን ተደርጎ ነበር። ደርግ በዘመኑ አዲስ አባባ ላይ (በተለይም አቃቂ አካባቢ) በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ሠራተኞችን የሚያቅፉ በርካታ ፋብሪዎችን በማቋቋም በከተማዋ ኢንዱስትሪ እንዲስፋፋ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክቷል።

በ1983 ዓ.ም. ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ አዲስ አበባን ከተቆጣጠረ በኋላ በ1984ዓ.ም. የሽግግር መንግሥት ሲመሠረት አዲስ አበባ ክልል 14 ተብላ የራሷ አስተዳደር እንዲኖራት ተደረገ። የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (ኢፌዴሪ) መንግሥት በ1987 ዓ.ም. እውን ሲሆን ክልልነቷ ቀርቶ በሕገ መንግሥቱ የፌዴራል መንግሥቱ መቀመጫ ዋና ከተማ መሆኗ ተደነገገ። በ1989 ዓ.ም በሕገ መንግሥቱ መሠረት ራስን በራስ ማስተዳደር የምትችልበት ሕግ ወጥቶላት በአዲስ አበባ ቻርተር እየተዳደረች ትገኛለች።

በዘመነ ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ. አዲስ አበባ ብዙ መሻሻሎችን አሳይታለች። የከተማዋን ኗሪዎች የቤት ችግር ለመቅረፍ የኮንዶሚኒየም የቁጠባ ቤቶች በስፋት ተገንብተዋል። ከቀለበት መንገዶች ጀምሮ የተለያየ ደረጃ ያላቸው የአስፋልትና የውስጥ ለውስጥ የኮብልስቶን መንገዶች ግንባታ ተካሂዷል። ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ጤና ጣቢያዎችና ትምህርት ቤቶች ተሠርተዋል። በሁሉም ክፍለ ከተሞችና ወረዳዎች በአንጻራዊነት ለነዋሪዎች የተቀላጠፈ አገልግሎት መስጠት የሚያስችሉ የአገልግሎት መስጫ ሕንጻዎች ግንባታ ተከናውኗል። ቤተ መጻሕፍትን ጨምሮ ሁለገብ አገልግሎት የሚሰጡ የወጣት ማዕከላት በእያንዳንዱ ወረዳ ተከፍተዋል። ይሁንና ኢፍትሃዊነት አድልዎና በተለየም አርሶ አደሩን ማፈናቀል የሥርዓቱ ደከመት ሆኖ ለለውጥ ሕዝብን አነሣስቷል።

ሀገራዊ ለውጡን ተከትሎ መጋቢት 24 ቀን 2010 ዓ.ም. ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ወደ ሥልጣን ከመጡ በኋላ አዲስ አበባ በተለየ የዕድገት ጎዳና ላይ መጓዝ ጀምራለች። ሸገርን እናስውብ በሚል መሪ መልእክት ብዙ ፕሮጀክቶች በአዲስ አበባ ተሠርተዋል። በአምስት ዓመታት ውስጥ እንጦጦ የተፈጥሮ ፓርክ፣ አንድነት፣ ወዳጅነት ፓርክንና የሳይንስ ሙዚየምን የመሳሰሉ ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ የፈሰሰባቸው፤ ዘመኑን የዋጀ መሠረተ ልማት የተሟላላቸው እና እጅግ የተዋቡ የኗሪዎቿን እና ጎብኚዎቿን መንፈስ እያደሱ በደስታ የሚሞሉ መስሕቦች ባለቤት ሆናለች። የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ታሪካዊ ይዘቱን ሳይለቅ በቅጥር ግቢው ውስጥ አዳዲስ መገልገያዎችን በሚያካትት መልኩ ሙሉ ሕንጻው እድሳት ተደርጎለት የከተማዋ ምልክትነቱ ይበልጥ መጉላት ችሏል።

መስቀል አደባባይ የቀድሞ ይዘቱን ሳይቀይር ከመሬት ሥር ሁለት ወለል ወደ ውስጥ በመግባት፣ የመኪና ማቆሚያ እንዲሁም አደባባዩንና ጎዳናዎችን የማስዋብ ሥራ ተሠርቶለት ይበልጥ ግዝፈትን ነስቶ የከተማዋ ግርማ ሞገስ ሆኗል። በአፍሪካ ቀዳሚ ከሆኑ 10 ቤተ-መጻሕፍት መካከል አንዱ የሆነ፣ በ4 ወለሎቹ 1 ነጥብ 4 ሚሊዮን መጻሕፍትን መያዝ የሚችልና 1 ነጥብ 5 ኪ.ሜ መደርደሪያ የያዘ፣ በ19 ሺህ ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ያረፈ ሁለገብ የሆነው አብርሆት ቤተ መጻሕፍት ተገንብቶላታል። 1400 ሜትር ስኩየር ስፋት የሚሸፍን ውስጣዊ ክፍል ያለው ድምፅ የማያስተላልፍ ቋሚ እና ጊዜያዊ የዐውደ ርእይ ቦታዎችን የያዘ የሳይንስ ሙዚየምም ባለቤት ሆናለች። በዓይነቱ ልዩ ከሆነው የሳር ቤት ጎፋ ማዞርያ የፑሽኪን ጎተራ ማሳለጫ ዘመናዊ የመንገድ ፕሮጀክት ግንባታ በአጭር ጊዜ ውስጥ

ተጠናቆ አገልግሎት እንዲሰጥ ተደርጓል።

ከላይ በወፍ በርር በተመለከትነው የታሪክ መንገድ ተጉዛ ዛሬ ላይ የደረሰችው አዲስ አበባ የዓለም የዲፕሎማሲ ማዕከልነቷን አጠናክራ ቀጥላለች። በዓለማችን ከሚገኙ በርካታ ቁጥር ካላቸው ከተሞች በዲፕሎማቶች መቀመጫነት እንዲሁም በኤምባሲና በዓለም አቀፍ ድርጅቶች መናኸሪያነት በአንደኛነት የምትጠቀሰው የአሜሪካዋ ኒውዮርክ ከተማ ስትሆን ጄኔቭ በሁለተኛነት ትከተላለች። ሦስተኛዋ ደግሞ የእኛዋ አዲስ አበባ ከተማ ናት። አዲስ አበባ የአፍሪካ ኅብረትና የአውሮፓ ኅብረትን ጨምሮ የበርካታ ሚሲዮኖችና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች መቀመጫ ናት። አዲስ አበባ የዲፕሎማቶች መኖሪያ ብቻ ሳትሆን የበርካታ ዓለም አቀፍ ስብሰባዎች፣ ኮንፈረንሶች፣ ወርክሾፖችና ኤግዚቢሽኖች የሚሰናዱባት እና የንግድ፣ የጤና፣ የልማት፣ የኢንቨስትመንት፣ የሰላምና የጸጥታ ጉዳዮች ላይ የሚመከርባትም መድረክ ናት።

"አዲስ አበባ ባለፈውና በአዲሱ ሚሌኒየም" በሚል ርእስ በ2000 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ሚሌኒየም ጽሕፈት ቤት የታተመ ጽሑፍ የአዲስ አበባ ሠፈሮችን አሰያየም በሚገባ ያስረዳል። በርካታዎቹ የከተማዋ ቀደምት ሠፈሮች ስያሜያቸውን ያገኙት በቤተ መንግሥቱ ዙሪያ መሬት በጉልት መልክ በተሠጣቸው መሳፍንትና መኳንንት ስም ነው። በዚህ መልክ ስያሜያቸውን ከአገኙት ሠፈሮች መካከል ራስ መኰንን ሠፈር፣ ራስ ተሰማ ሠፈር፣ ራስ ብሩ ሠፈር፣ ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ሠፈር፣ ራስ ሥዩም ሠፈር፣ ራስ ሙሉጌታ ሠፈር፣ ደጃዝማች ውቤ ሠፈር፣ ጌጃ ሠፈር ነጋድራስ ኃይለ ጊዮርጊስ ሠፈር፣ ደጃዝማች ዘውዱ አባኮራን ሠፈር እና ሸንኬ (የአሶሳ ገዢ በነበሩት በሼክ ሆጀሌ አል ሐሰን የተሰየመው) ሠፈር ይጠቀሳሉ።

ከመላው የሀገሪቱ ማዕዘናት መጥተው አዲስ አበባ በሠፈሩ ብሔረሰቦች የተመሠረቱ ሠፈሮች ደግሞ በሁለተኛ ደረጃ ይቀመጣሉ። በዚህ መልክ ከተመሠረቱት ሠፈሮች መካከል ለአብነት አደሬ ሠፈር፣ ጎፋ ሠፈር፣ ወሎ ሠፈር፣ ወርጂ ሠፈር፣ መንዜ ሠፈርና ሱማሌ ተራ ይገኙበታል።

በሦስተኛ ደረጃ በተለያዩ ሙያዎች ተሠማርተው በተለይም በቤተ መንግሥቱ የተለያዩ የሥራ ድርሻዎች በነበራቸው ባለሙያዎች የተቆረቆሩ ሠፈሮችን እናገኛለን። እነዚህም ሠራተኛ ሠፈር፣ ዘበኛ ሠፈር፣ ሥጋ ቤት ሠፈር፣ ኩባንያ ሠፈር፣ ጠመንጃ ያዥ ሠፈር፣ ካህን ሠፈር (በኋላ ገዳም ሠፈር)፣ ገባር ሠፈር፣ ሠረገላ ሳቢ ሠፈርና ውሃ ስንቁ ሠፈርን ያካትታሉ። ሠራተኛ ሠፈር በዐፄ ምኒልክ ቤተ መንግሥት በዕደ ጥበባት ሙያ በተሠማሩ ነዋሪዎች የተመሠረተ ሠፈር ነው። የሠፈሩ መሥራቾች ዋነኛ ሙያ የብረታ ብረት ሥራ እንደነበረ ይነገራል። ይኼም የተለያዩ የብረታ ብረት ውጤቶችን ለምሳሌ ማረሻ፣ የፈረስ እርካብን፣ የቤት እቃዎችን፣ የጋሻና ጦር እና የጠመንጃ እድሳትን ይጨምራል። በቤተ መንግሥቱ በአናጢነት የተሠማሩ ባለሙያዎችም የሚኖሩት በሠራተኛ ሠፈር እንደነበር ይነገራል።

በሌላ በኩል ጥቂት የማይባሉ የአዲስ አበባ ሠፈሮች ስያሜያቸውን ያገኙት በተለያዩ አጋጣሚዎች፣ ክሥተቶችና ታሪካዊ ክንዋኔዎች ነው። ሰባራ ባቡር፣ እሪ በከንቱ፣ ዶሮ ማነቂያ፣ አፍንጮ በር፣ አራት ኪሎ፣ አምስት ኪሎ፣ ስድስት ኪሎ፣ ጣሊያን ሠፈር፣ ሃያ ሁለት ማዞሪያ፣ ሾሮ ሜዳና ነፋስ ስልክ ተብለው የሚጠሩትን ሠፈሮች በዚሁ ዘርፍ መፈረጅ ይቻላል። ሰባራ ባቡር ሠፈር ስያሜውን ያገኘው ሙሴ ሰርኪስ ተርዚያን በሚባሉ አርመናዊ ነጋዴ አማካይነት ከውጭ አገር መጥቶ አሁን ስያሜውን ባገኝበት ቦታ ተበላሽቶ በቀረው የመንገድ መሥሪያ ተሽከርካሪ (ሮለር) ምክንያት ሠፈሩ ሰባራ ባቡር በመባሉ ነው።

በተጨማሪም በከተማው ከሚገኙ ዋና ዋና ሠፈሮች መካከል በኦሮሞ ተወላጆችና የቦታ ስሞች የተሰየሙ ሠፈሮችን እናገኛለን። ከነዚህም መካከል ጉለሌ፣ ጎርዶሜ፣ ቀበና፣ ኮተቤ፣ የካ፣ እንዲሁም ገርጂ እና ላፍቶ የተባሉት ሠፈሮች ለአብነት ይጠቀሳሉ።

እንዲሁም ሠፈሮችን በከተማዋ በሚገኙ አብያተ ክርስቲያን እና አጥቢያዎች መሰየም ሌላ መንገድ ነው። በዚህ ዘርፍ ከሚገኙ ሠፈሮች መካከል ተቀዳሚውን ሥፍራ የሚይዘው አራዳ ጊዮርጊስ ሠፈር ነው። አራዳ በተለይም ከጣሊያን ወረራ ቀደም ባለው ጊዜ የአዲስ አበባ የኢኮኖሚ ማዕከል ከመሆኑ አኳያና በርካታ ማኅበራዊ ክንዋኔዎችን ያስተናግድ የነበረ ሠፈር እንደመሆኑ በሥነቃል ብዙ ተብሎለታል። በተመሳሳይ መንገድ ከተሰየሙ ሌሎች ሠፈሮች ደግሞ አማኑኤል፣ ዮሴፍ፣ ኪዳነ ምሕረት፣ ቀራኒዮ መድኃኔ ዓለም፣ እና ቀጨኔ መድኃኔ ዓለም ይገኙበታል።

ከ1888 ዓ.ም. የዐድዋ ጦርነት ድል እና ከአዲስ አበባው ስምምነት በኋላ ጣሊያን፣ ሌሎች የአውሮፓ መንግሥታትና አሜሪካ የአገራችንን ሉዓላዊነት በመቀበል ከኢትዮጵያ ጋር ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት መሥርተዋል። በዚህ ሂደት በርካታ አገሮች የእነዚህን አገሮች ፈለግ በመከተል ኤምባሲዎቻቸውን በአዲስ አበባ ከፍተዋል። ከአዲስ አበባ በርካታ ሠፈሮች መካከል አንዳንዶቹ ስያሜያቸውን ያገኙት ከእነዚህ ኤምባሲዎችና ቀደም ሲል ደግሞ ከሌጋሲዮኖች ነው። ፈረንሣይ ሌጋሲዮንና ሩዋንዳ ሠፈሮች ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ናቸው።

ከአዲስ አበባ ሠፈሮች መካከል አንዳንዶቹ በታዋቂ የውጭ አገር ዜጎች ስም የተሠየሙ ናቸው። ከእነዚህም መካከል ቤኒን ሠፈርና ተረት ሠፈር ይገኙበታል። ቤኒን ሠፈር ስያሜውን ያገኘው ከጣሊያን ወረራ በፊት ታዋቂ ነጋዴ በነበሩት የአይሁድ ተወላጅ ቤኑን ሲሆን፣ ተረት ሠፈር





አዲስ አበባ ማገናኛ 2015 ዓ.ም

ደግሞ ስያሜውን ያገኘው በአዲስ አበባ ከተከፈቱት ከመጀመሪያዎቹ ሆቴሎች አንዱ በነበረው በሆቴል ዳፍራንስ ባለቤት ፈረንሣዊው ሙሴ ቴረስ ስም ነው።

የታሪክ መምህሩ ዶክተር ሺመልስ ቦንሣ ከላይ በተጠቀሰው ጽሑፋቸው “የአዲስ አበባ ማንነት” በሚል ንኡስ ርእሥር በአፈሯቸው አንቀጾች የአዲስ አበባን መልክ እንደሚከተለው ይገልጹታል። “ስብጥር የሆነች ከተማ፣ ንብርብር ታሪክ የተሸከመች ምድር፣ የብዙኃን ነዋሪዎቿ ድምር ውጤት፣ የእጅ ሥራ ነጸብራቅ ሆና የኖረች ግማደ-ኢትዮጵያ ... በብዝኃነት ጥልፍልፍ ተፀንሳ የተወለደች፣ አድጋም የጎለመሰች። አዲስ አበባ ምንነቷና የማንነቷ ምስጢር በአንድነት ተጋምዶ፣ በልዩነት ውበት አሸብርቆ ደምቆ የተፈጠረ የሃገርነት ቋጠሮ ነው።

የአዲስ አበባ ከንቲባ ጽሕፈት ቤት ድረ ገጽ ላይ የሠፈረ መረጃ እንደሚያመለክተው፣ አዲስ አበባ ከምስረታዋ አንሥቶ እስከአለንበት ጊዜ ድረስ በ32 ከንቲባዎች ተዳድራለች። ከተማዋን በከንቲባነት የአገለገሉት ባለታሪኮች በቅደም ተከተል ወልደ ጻዲቅ ጎሹ-1882 ዓ.ም.፣ ኃይለ ጊዮርጊስ- 1909 ዓ.ም.፣ ወሰኔ ዛማኔል- 1910 ዓ.ም.፣ ይገዙ በሀብቴ- 1910፣ ማተቤ -1910 ዓ.ም.፣ ጎሩይ ወልደሥላሴ ከ1910-1914 ዓ.ም፣ ነሲቡ ዛማኔል ከ1914-1923 ዓ.ም.፣ መኮንን እንዳልካቸው ከ1924-1926 ዓ.ም.፣ ጠና ጋሻው ከ1926- 1928 ዓ.ም.፣ አበበ አረጋይ ከ1926- 1933 ዓ.ም.፣ ታከለ ወ/ሐዋርያት ከ1933-1934 ዓ.ም.፣ ከበደ ተሰማ 1934 ዓ.ም.፣ መስፍን ስለሺ ከ1934- 1938፣ ደምሴ ወ/አማኑኤል 1938 ዓ.ም.፣ ዘውዴ በላይነህ ከ1947-1948 ዓ.ም.፣ ትርፌ ሹምዬ ከ1948-1950 ዓ.ም.፣ ዘውዴ ገ/ሥላሴ ከ1950-1952 ዓ.ም.፣ ዘውዴ ገ/ሕይወት ከ1952-1961 ዓ.ም.፣ ኃ/ጊዎርጊስ ወርቅነህ ከ1961-1966 ዓ.ም.፣ መኮንን ሙላት ከ1966-1970 ዓ.ም.፣ ዓለሙ አበበ ከ1970-1973 ዓ.ም.፣ ዘውዴ ተክሉ ከ1974-1981 ዓ.ም.፣ ግዛው ንጉሴ ከ1981-1983 ዓ.ም.፣ ሙሉዓለም አበበ ከ1983-1985 ዓ.ም.፣ ተፈራ ዋልዋ ከ1985-1989 ዓ.ም.፣ አሊ አብዶ ከ1990-1995 ዓ.ም.፣ አርከበ ዕቁባይ ከ1995-1998 ዓ.ም.፣ ብርሃነ ደሬሳ ከ1998-2000 ዓ.ም.፣ ኩማ ደመቅሳ ከ2000-2005 ዓ.ም.፣ ድሪባ ኩማ ከ2005-2010 ዓ.ም.፣ ታከለ ኡማ 2010-2012 እንዲሆም ከ2012 ዓ.ም. ጀምሮ ከተማዋን እያስተዳደሩ የሚገኙት ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ናቸው።

አዲስ አበባ ዛሬ ላይ ከተከናወኑላት እጅግ አበረታችና ተስፋ ሰጪ ልማቶቿ በተጨማሪ ለነገ የታሰቡና እየተገነቡ ያሉ እንደ አዲስ ቱሞሮው፣ ዊንዶው ኦፍ አፍሪካ፣ የግብርና ምርት ሽያጭ ማዕከላት፣ ሆስፒታሎችና መንገዶች የከፍታዋና የብልጽግናዋ መዳረሻ እጹብ ድንቅ መሆኑን አፍ አውጥተው ይመሰክራሉ!


የዳግማዊ ምኒልክ ሪፈራል ሆስፒታል የኩላሊት እጥበት ማዕከልን

# ዋናው ነገር ጤና !

አሜሪካዊው ፈላስፋ ራልፍ ዋልዶ ኤመርሰን «ቀዳሚው ሀብት ጤና ነው» የሚለውን ጥልቅ ሐሳብ እንደተናገረ ይገለፃል። በተለይ በዚህ ጉዳይ ላይ እ.ኤ.አ. በ1860 በቀረበው ትንተና በእርግጥም የዓለም ሕዝቦች የድህነትና ሀብት፣ የኋላ ቀርነትና ሥልጣኔ፣ የመታደልና ያለመታደል ዋነኛ ማነጻጸሪያ ጤናና የጤና ዋስትና ቀዳሚው መሠረታዊ ጉዳይ መሆኑ ይታወቃል። በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ መሠረታዊ የሚባሉት ፍላጎቶች ምግብ፣ መጠለያና አልባሳትም ቢሆኑም እነዚህ ሁሉ ግን ያለጤና ከንቱ ናቸው።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርም የጤና ጉዳይ የመኖር፣ የልማትና የብልጽግና መሠረት መሆኑን አጽንዖት ሰጥቶ ለከተማዋ ነዋሪ የሚመጥን የጤና አገልግሎት ተደራሽ ለማድረግ በአለፉት ጥቂት ዓመታት በትኩረት እየሠራ ይገኛል።

«የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያዉ ሦስት ዓመት (2013-2015 ዓ.ም.) የልማት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት» ላይ እንደተገለጸው፤ የከተማ አስተዳደሩ ጤና ቢሮ የአገልግሎት አሰጣጥ ተደራሽነትን ለማስፋፋት የተመላላሽ ሕክምና ተጠቃሚ ኅብረተሰብ ቁጥርን በ2010 ዓ.ም. በጀት ዓመት እኩሌታ ከነበረው 2 ነጥብ 3 ሚሊዮን ዓመታዊ አሐዝ በ2015 ዓ.ም. ወደ 9 ነጥብ 5 ሚሊዮን በማሳደግ ከፍተኛ የተደራሽነት መሻሻልን ማምጣት ችሏል።

የአስተኝቶ ሕክምና ታካሚዎች ቁጥርንም በ2010 ዓ.ም. ከነበረው 149 ሺህ 596 በአሁኑ ጊዜ ወደ 197 ሺህ 386 ማሳደግ ተችሏል። በጤና ተቋማት የታዘዙላቸውን መድኃኒቶች በዚያው የመንግሥት ጤና ተቋም ውስጥ 100% ያገኙ ተገልጋዮች በመቶኛ በ2010 ዓ.ም. ከነበረው 60 በመቶ አፈጻጸም በ2015 ዓ.ም. ወደ 84 በመቶ አድጓል። አጠቃላይ ኦፕሬሽን ያገኙ ተገልጋዮች ብዛት በ2010 ዓ.ም. በጀት ዓመት እኩሌታ ከነበረው 38 ሺህ 429 በ2015 ዓ.ም. ግማሽ ዓመት ብቻ ወደ 54 ሺህ 638 በማሳደግ የኦፕሬሽን አገልግሎት የሚፈልጉ ታካሚዎች ይበልጥ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ሆነዋል።

የከተማ አስተዳደሩ በሰፋት ተንቀሳቅሶበት ውጤት ከተመዘገበበት ዘርፍ አንዱ በሆነው በማኅበረሰብ አቀፍ ጤና መድኅን ፕሮግራም ይበል የሚያሰኙ ተግባራት ተፈጽመዋል። በ2010 ዓ.ም. በጀት ዓመት እኩሌታ ከነበረው 10 ወረዳዎች ሽፋን፤ 15 ሺህ



የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርም የጤና ጉዳይ የመኖር፣ የልማትና የብልጽግና መሠረት መሆኑን አጽንዖት ሰጥቶ ለከተማዋ ነዋሪ የሚመጥን የጤና አገልግሎት ተደራሽ ለማድረግ በአለፉት ጥቂት ዓመታት በትኩረት እየሠራ ይገኛል።




አበበች ጎበና የእናቶችና ሕጻናት ሆስፒታል

886 አባወራዎችና 71 ሺህ 487 አጠቃላይ የአባልነት ሽፋን፣ በ2015 ዓ.ም. ሁሉንም ወረዳዎች በማጠቃለል የአባዎራዎችን ቁጥር ወደ 271 ሺህ 038 እንዲሁም የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ኅብረተሰብን ወደ 2,002,130 አባላት ማድረስ ተችሏል። በ2015 ዓ.ም. በጀት ዓመት የከተማ አስተዳደሩ የድሃ ድሃ ተናጠል ድጎማ እና 50 በመቶ ለእያንዳንዱ ከፋይ አባል በድምሩ ከ500 ሚሊዮን ብር በላይ ድጎማ በማድረግ ለፕሮግራሙ መሳካትና ለኅብረተሰቡ ተጠቃሚነት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርጓል።

የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራትን ከማሻሻል አንጻር በተመለከተም የአስተኝቶ ሕክምና ታካሚዎች ሞት መጠን በ2010 ዓ.ም. በጀት ዓመት እኩሌታ ከነበረበት 3 ነጥብ 9 በመቶ፣ በ2015 ዓ.ም. ወደ 2 በመቶ መቀነስ ተችሏል። እንዲሁም የድንገተኛ ታካሚዎች ሞት መጠንን ከነበረው 0 ነጥብ 8 በመቶ ወደ 0 ነጥብ 5 በመቶ በመቀነስ የሚሰጠው አገልግሎት ጥራት

ከጊዜ ወደ ጊዜ ከመሻሻሉ በተጨማሪ የሞት ምጣኔ አመላካቾቹ የዓለም ጤና ድርጅት የአስቀመጣቸውን ስታንዳርዶች በአግባቡ አሳክቷል።

በጤናው ዘርፍ ሌላው ተጠቃሽ ስኬት የአበበች ጎበና እናቶችና ሕፃናት ሕክምና መስጫ ማዕከል ነው። ማዕከሉ፣ የእናቶችና ሕፃናት ጤናን ከማሻሻል፣ አገልግሎቱንም ይበልጥ ተደራሽ ከማድረግ በተጨማሪ የወሊድ አገልግሎት ለማግኘት ረጅም ርቀት ይጓዙ ለነበሩ እናቶች የተቀላጠፈ አገልግሎት በመስጠት የእናቶችና ጨቅላ ሕፃናትን ሞት ለመቀነስ ሥራዎችን በስፋትና በጥራት ለማድረስ ትልቅ ሚና እየተጫወተ ይገኛል። ከተማ አስተዳደሩ ባደረገው ቁርጠኛ ውሳኔ ለሌላ ዓላማ ይውል የነበረውን ይህን ግዙፍ ማዕከል ለሕክምና አገልግሎት እንዲሆን በመወሰን በ400 አልጋዎች ለእናቶችና ለሕፃናት ዘርፈ ብዙ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል። ማዕከሉ ከተመሠረተ ከ2013 ዓ.ም. ጀምሮ ለ35 ሺህ 996 እናቶች የወሊድ አገልግሎት መስጠት ችሏል።

ጤና ጣቢያዎች የቀዶ ሕክምና የማወለድ አገልግሎት መስጠት ጀምረዋል። በቀዶ ሕክምና የማዋለድ አገልግሎት ፍላጎትን ለማሟላት የማዋለድ ምጣኔያቸው ብዙ በሆኑ፣ በተመረጡና ከሆስፒታሎች ርቀት ላይ ባሉ ጤና ጣቢያዎች ተጀምሯል። ሥራው እየተከናወነ ያለው ከተለያዩ ሆስፒታሎች ጋር ትስሥር በመፍጠርና የባለሙያ ዝውውሮችን በማካሄድ ከዚህ ቀደም አገልግሎቱ ከሚሰጥባቸው አካባቢዎች ተሞክሮ በመቅሰም ነው። አገልግሎቱ የእናቶችና የሕፃናት ሞት ለመቀነስ ከሚያበረክተው አስተዋፅኦ ባሻገር የጤና ዘርፍ ትራንስፎርሜሽን ዕቅድን ለማሳካት ይረዳል።

የእናቶችን ጤና አገልግሎት ለማሻሻልና ሞትን ለመቀነስ በ19 ጤና ጣቢያዎች የኦፕሬሽን ማዋለድ አገልግሎት(C/S Delivery) እየሰጡ ይገኛሉ። የሕፃናት ጤናን ከማሻሻል አንጻር በአለፉት ሦስት ዓመታት ለ235 ሺህ 893 (100%) ሕፃናት ሁሉንም ክትባት ለመስጠት ታቅዶ ለ345 ሺህ 142 (146.3%) ሕፃናት መስጠት ተችሏል። ለአፈጻጸሙ ከፍተኛነት በዘመቻ ወቅት ክትባት ያላገኙ ሕፃናትን የማፈላልግ ሥራ መሠራቱና የክትባት አቅርቦት ማሻሻል መቻሉ ይጠቀሳሉ።

ቤት ለቤት የወላጆች የምክር እና የዐቅም ግንባታ 5 ሺህ ሴት ወጣቶችን እና 67 የክትትል እና ድጋፍ ባለሙያዎችን (Supervisors) በሌቭል ደረጃ 2 በማሠልጠን ወደ ሥራ ተገብቷል። በዚህም ከፅንስ እስከ 6 ዓመት ባለው የሕፃናት ዕድገት ጊዜ ውስጥ ሕፃናት ጤናማ አካላዊ እና አእምሯዊ ዕድገት እንዲኖራቸው፣ የሥርዓተ ምግብ ልየታ፣ ክትባትና ሌሎች የቤት ለቤት ክብካቤዎችን በሁሉም ጤና ጣቢያዎች እየተተገበረ ይገኛል። በዚህም ካለፉት ሁለት ዓመታት ጀምሮ እስከ ዘንድሮ 2015 ዓ.ም. ከአንድ ሚሊዮን በላይ ሕፃናትና ወላጆች የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ተችሏል።

በመድኃኒት አቅርቦት በኩል ሕይወት አድን መድኃኒት አቅርቦት በ2013 ዓ.ም.(92%)፣ በ2014 ዓ.ም.(85%)፣ በ2015 ዓ.ም.(92%) መሆኑን ያሳያል። አስፈላጊ ወይም ኢሴንሻል መድኃኒት አቅርቦት ደግሞ በ2013 ዓ.ም(86%)፣ በ2014ዓ.ም(89%)፣ በ2015 ዓ.ም (90%) በመቶ አቅርቦት እንዲኖር ተደርጓል።

በሀገራችን እንዲሁም በከተማችን ያለውን ከፍተኛ የዐይን ሕክምና አገልግሎት ፍላጎት ጥያቄ ለመመለስ በዳግማዊ ሚኒልክ ሪፈራል ሆስፒታል የዐይን ሕክምና ማዕከል ለመመሥረት አዲስ ግንባታ ተከናውኗል። ማዕከሉ በዘመናዊ መልኩ ተቋቁሞ ግብአቶች ተሟልተውለት ከመስከረም 2015 ዓ.ም. ጀምሮ ሥራ እንዲጀምር ተደርጓል። የአገልግሎት ማስፋፍያ ከተደረገለት ጊዜ ጀምሮ የተመላላሽና አስተኝቶ ሕክምና ክፍልን በ4 እጥፍ፣ የኦፕሬሽን አገልግሎት መስጫ ክፍልን በ2 እጥፍ አሳድጓል። በያዝነው 2015 ዓ.ም. በአጠቃላይ ለ72,991 ታካሚዎች አገልግሎት መስጠት ተችሏል።

የኩላሊት ሕክምና ተገልጋዮች ከኩላሊት እጥበት ጋር በተያያዘ ይገጥማቸው የነበረውን ወረፋና እንግልት ለመቀነስ ከ2014 ዓ.ም. ነሐሴ ወር ጀምሮ በዳግማዊ ምኒልክ ሪፈራል ሆስፒታል ከአጋር ድርጅት ጋር በመተባበር(Public Private Partnership) የኩላሊት እጥበት ማዕከልን በተደራጀ መንገድ ማቋቋም ተችሏል። በዚህም ተጨማሪ 30 ማሽኖችን በመጨመር ባለፈው አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ለ108 ታካሚዎች 31,000 ጊዜ የኩላሊት እጥበት አገልግሎት ተሰጥቷል። የከተማ አስተዳደሩ ዐቅማቸው ለማይችሉ የኩላሊት ታካሚዎች ከ40 ሚሊዮን ብር በላይ ክፍያ በመፈፀም ነጻ የኩላሊት እጥበት አገልግሎት እንዲያገኙ ተደርጓል።

በጤናው ዘርፍ የተጀመሩና በሂደት ላይ ያሉ የግንባታ ሥራዎችን በተመለከተ የኅብረተሰቡን የጤና አገልግሎት ጥያቄ ይበልጥ ለማርካትና ተደራሽነትን በይበልጥ ለማስፋፋት በኮልፌ፣ በንፋስ ስልክ እና በቦሌ ክፍለ ከተማዎች ውስጥ ሦስት አጠቃላይ ሆስፒታሎች በግንባታ ላይ ይገኛሉ። እነዚህም ሆስፒታሎች እያንዳንዳቸው ከ450 በላይ የአስተኝቶ ሕክምና አልጋ የሚኖራቸው ሲሆን ዘመኑን በዋጁ እጅግ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች እንዲገነቡና እንዲደራጁ ተደርገው ወደ አገልግሎት የሚገቡ ይሆናሉ።

ነባር ሆስፒታሎችንም ከማስፋፋት አንጻር በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ ሥር የሚገኘው የዘውዲቱ መታሰቢያ ሆስፒታል ማስፋፊያ ሕንጻ ግንባታ Basement+G+8 ሲሆን ይህም 1.6 ቢሊዮን ብር በጀት ተይዞለታል። በአሁኑ ጊዜ ግንባታው ተጀምሮ በሂደት ላይ ይገኛል። ግንባታው ሲጠናቀቅ አገልግሎት ከማስፋፋትና ጥራትን ከማሻሻል አንጻር ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንደሚያደርግም ይጠበቃል። በጥሩነሽ ቤጂንግ ሆስፒታል ድንገተኛ አደጋዎችን እና ተያያዥ የጤና እክሎችን(Trauma Center) በተቀላጠፈ መንገድ የሕክምና አገልግሎት መስጠት ያስችል ዘንድ G+6 (ባለ2 ቤዝመንት) ሕንጻ ግንባታ 50% ደርሷል። ሲጠናቀቅም በአዲስ አበባ እና በዙሪያዋ የሚፈጠሩ ድንገተኛ አደጋዎችን በአፋጣኝና በጥራት አገልግሎት ለመስጠት ያስችላል።



ገጽ 64
የኢትዮጵያ
ኢኮኖሚ ልብ



ገጽ 68
ትምህርት



ገጽ 70
አዲስ ስፖርት

# የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ልብ

**ዮርዳኖስ ፍቅሩ**

ኅብረብሔራዊነቷ ትንሿ ኢትዮጵያ የሚል ስያሜን የአጎናጸፋት አዲስ አበባ የሀገራችን የኢኮኖሚ ማዕከልም ናት። በከተማይቱ የሚሰበሰበው ከፍተኛ ገቢ፣ ግዙፍ የገበያ እንቅስቃሴ፣ የትራንስፖርት ትስስሩና ቱሪዝም ወዘተ... የአዲስ አበባን የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ማእከልነት አጉልተው ያሳያሉ።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከተማዋ ለሀገራችን የሀገር ውስጥ ምርት ዕድገት የምታደርገው አበርክቶ የላቀ መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ ይህን ሚናዋን የበለጠ ማጎልበት የሚያስችሉ በርካታ የልማት ሥራዎችን ሠርቷል፤ እየሠራም ይገኛል። በከተማችን የተጀመሩና በተወሰነላቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ አምረው የተጠናቀቁ ትላልቅ ፕሮጀክቶች የከተማ አስተዳደሩ ብሎም የመላው አመራርና ሠራተኛ ጉልህ የትጋት ማሳያ ናቸው። ማኅበራዊ ፍትሕን ለማስፈን፣ በሕዝቦች መካከል የቆየውን የመደጋገፍ ዕሴት ለማጽናት የተሠሩና ዛሬም የቀጠሉ ሰው ተኮር የልማት ሥራዎችም የከተማ አስተዳደሩና የለውጡ ዘመን መገለጫዎች ናቸው ማለት ይቻላል። ሌሎችም በከተማዋ የተከናወኑ ዘርፈ ብዙ ተግባራት አዲስ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከተማዋ ለሀገራችን የሀገር ውስጥ ምርት ዕድገት የምታደርገው አበርክቶ የላቀ መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ ይህን ሚናዋን የበለጠ ማጎልበት የሚያስችሉ በርካታ የልማት ሥራዎችን ሠርቷል፤ እየሠራም ይገኛል።

**በ2015 በጀት ዓመት የአዲስ አበባ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች**

- ✓ 2000 ፀረ ሰላም ኃይሎች በሕግ ተጠያቂ ተደርገዋል
- ✓ 21 ወረዳዎች ስማርት ሆነዋል
- ✓ 112 ሚሊዮን 754 ሺህ ተማሪዎች ቅበላ ተደርጓል
- ✓ 28 የጤና ፕሮጀክቶች ሲጠናቀቁ 3 ሆስፒታሎች እተገነቡ ነው
- ✓ 39 ቢሊዮን ብር ከውጪ ሀገር ቱሪስቶች ገቢ ተገኝቷል
- ✓ 416 ሺህ 999 የሥራ ዕድል ተፈጥሯል
- ✓ 415 ሺህ 923 ዜጎች የምግብ ዋስትና ተጠቃሚ ሆነዋል
- ✓ 172 የቅዳሜና እሑድ ገበያዎች በተመጣጣኝ ዋጋ ምርቶችን ለነዋሪው አቅርበዋል
- ✓ 4 ሚሊዮን ዳቦ በቀን የማምረት ዐቅም ተፈጥሯል

አበባን በማስዋብ፣ ኢኮኖሚዋን በማንቃት፣ በዓለም መድረኮች እንድትታይ በማድረግ ረገድ ትልቅ ሚናን ተጫውተዋል።

የከተማዋ ከንቲባ ክብርት አዳነች አቤቤ ከዘመን መጽሔት ጋር በነበራቸው ቆይታ እንዳብራሩት፣ የመዲናይቱን የኢኮኖሚ ዐቅም ለማጎልበት የማምረት አቅሟን ማሳደግ የሚያስችሉ በርካታ ሥራዎች ተከናውነዋል። መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ወደ ባለሀብትነት እንዲያድጉ ተደርጓል። ትላልቅ የሥራ ዕድል የፈጠሩና ኢኮኖሚውን የሚያሳልጡ የማምረቻና የመሸጫ ሥፍራዎችንም በኢንደስትሪ ፓርክ ደረጃ መገንባት ተችሏል። መልከ ብዙ ሚና ያላቸው ሌሎች ሜጋ ፕሮጀክቶችም በመገንባት ላይ ይገኛሉ።

የአዲስ አበባን ኢኮነሞሚያዊ እንቅስቃሴ በተመለከተ ከዘመን መጽሔት ጋር ቆይታ ደረጉት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ክብርት ወ/ሮ አዳነች አቤቤ የከተማ አስተዳደሩ ያልተስተካከለ የግብይት ሥርዓት ያመጣውን ሰው ሠራሽ ችግር ለመቅረፍ፣ ምርት ወደ አዲስ አበባ እንዲገባ በማድረግ ትልቅ ሥራ ሠርቶ ትልቅ የሚባል ውጤት ተገኝቶበታል። በተጨማሪም ታክስ የማይደረጉና ሌላው ነጋዴ ከሚሸጥበት ዋጋ አንጻር ከ20 እስከ 30 ከመቶ የዋጋ ልዩነት ያላቸው 179 የእሑድ ገበያዎችን በመክፈት እሑድና ቅዳሜ ሕዝቡ በተመጣጣኝ ዋጋ ለኑሮ አስፈላጊ የሆኑ የፍጆታ ሸቀጦችን እንዲሸምት እየተደረገ እንደሚገኝም አንሥተዋል።

በንግድ ዘርፍ፣ ከተማ አስተዳሩ በቴክኖሎጂ የታገዘ ዘመናዊ የንግድ አሠራር በመዘርጋ በከተማዋ ዘመናዊ፤ ፍትሐዊና በውድድር ላይ የተመሠረተ የንግድ ሥርዓት የማስፈን ተልዕኮ ይዞ እየተንቀሳቀሰ ሲሆን፣ በመካከለኛ ዘመኑ ዘመናዊ፣ ተደራሽና ቀልጣፋ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት አሠራርን ማሻሻል፣ የንግዱንና የሸማቹን ኅብረተሰብ ዐቅም ማሳደግ፣ በግል ባለሃብቱና በመንግሥት አጋርነት ዘመናዊ የገበያ ማዕከላት እንዲገነቡ መደረጉንም ከከተማ አስተዳደሩ የተገኘ ሪፖርት ያመለክታል።

በየዘርፉ በርካታ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎችን ስታደርግ የቆየችው መዲናችን አዲስ አበባ ገቢዋ እመርታዊ ለውጥ ማሳየቱን ከንቲባ አዳነች አቤቤ ተናግረዋል። እንደ እርሳቸው ገለጻ በ2010 ዓ.ም የከተማዋ ዓመታዊ ገቢ 30 ቢሊዮን የነበረ ሲሆን፣ በ2015 ዓ.ም የ79 ቢሊዮን ብር ጭማሪ አሳይቶ 109 ቢሊዮን ብር መሰብሰብ ተችሏል። በቀጣዩ 2016 ዓ.ም በጀት ዓመት ደግሞ 140 ቢሊዮን ብር በመሰብሰብ ከ80 ቢሊዮን ብር በላይ የሚሆነውን ለካፒታል ፕሮጀክት ለማዋል ታስቧል። የበጀት ብክነትና አስተዳደራዊ ወጪዎችን እየቀነሰ በጀትን ለዘላቂ ልማት ለማዋል አስተዳደሩ ጠንክሮ እነደሚሠራ ነው ክብርት ከንቲባዋ የገለጹት።

ከነፍስ ወከፍ ገቢ አንጻር ደግሞ በሪፖርቱ እንደተገለጸው፣ የከተማዋ አመታዊ ጠቅላላ የምርትና አገልግሎቶች ቋሚ ዋጋ ግምት ለጠቅላላ ነዋሪዎች ተካፍሎ የሚገኝ አማካይ ዓመታዊ ገቢ ወይም ነፍስ ወከፍ ገቢ በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት ብር 149ሺ 801፣ በ2015 ወደ ብር 178ሺ 18 ብር አድጓል።

ለኢንተርፕራይዞች እና ለአምራች ኢንዱስትሪዎች የተቀናጀና ውጤታማ ድጋፍ በማድረግ የምርት ጥራት እንዲያረጋግጡና ምርትና ምርታማነታቸውን ማሳደግ እንዲችሉ በተሠራው ሥራ፣ በሦስት ዓመታት ወደ ውጪ ገበያ ምርቶቻቸውን የሚልኩ ኢንተርፕራይዞች ቁጥር መጨመሩም በሪፖርቱ ተመላክቷል።

ክብርት ከንቲባዋም፣ ከተማሪዎች ምገባና ሌሎችም ሰው ተኮር ሥራዎች ጋር ተያይዞ የተሠሩ ሥራዎችን አስመልክቶ እንደገለጹት፣ የሰው ተኮር ሥራዎች አንደኛው ዓላማ መላው የከተማዋ ነዋሪ ከከተማዋ በሚገኘው ገቢ ተጠቃሚ መሆን አለበት የሚለው ሲሆን፣ በዚህም አዲስ አበባን ሰው ተርቦ የማያድርባት ከተማ ማድረግ የተቻለበት ትልቅ ስኬት

## ድጎማን በተመለከተ

- ✓ 1 ነጥብ 9 ቢሊዮን ብር ለሕዝብ ትራንስፖርት
- ✓ 2 ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር ለተማሪዎች ምገባና የትምህርት ቁሳቁስ
- ✓ 1 ነጥብ 4 ቢሊዮን ብር ለሰብል ምርቶች
- ✓ 2 ነጥብ 6 ቢሊዮን ብር ለመንግሥት ሠራተኞች መኖሪያና ካፍቴሪያ
- ✓ 300 ሚሊዮን ብር ዐቅም ለአነሳቸው ዜጎች ሕክምና
- ✓ 300 ሚሊዮን ብር ለሸገር ዳቦ
- ✓ በድምሩ 9 ቢሊዮን ብር የሚደርስ ድጎማ ተደርጓል።
- ✓ 120 ሺህ 167 ቶን የሰብልና የእንስሳት ምርት በከተማ ግብርና ተመርቷል።
- ✓ 97 ነጥብ 82 ቢሊዮን ብር ገቢ ተሰበስቧል።
- ✓ ለ2 ሺህ 877 ባለሃብቶች አዲስ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ተሰጥቷል።
- ✓ 5 ሺህ 256 የመንገድ፣ የውሃ፣ የጤና፣ የትምህርት፣ የሼዶች እና የስፖርት ማዘውተሪያ ፕሮጀክቶች ተጠናቀው ተመርቀዋል።



መሆኑን አስምረውበታል።


በአለፉት ሦስት ዓመታት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ባህልን ለማጎልበት ከተከናወኑ ተግባራት በተፈጠረ ግንዛቤ እና የኅብረተሰብ ንቅናቄ ሥራዎች ምክንያት፤ በቤት እድሳት፣ በማዕድ ማጋራት፣ በደም ልገሳ፣ በመንገድ ትራፊክ አገልግሎት፣ በችግኝ ተከላ፣ በአካባቢ ጽዳት ወዘተ.... በመሳሰሉ ተግባራት ላይ የከተማችን ነዋሪዎች ተሳትፏቸው እያደገ መምጣቱ እንዲሁም በየደረጃው (ከማዕከል እስከ ወረዳ ድረስ) በበጎ ፈቃድ አገልግሎት ላይ ተሳትፎ ለአደረጉ አካላት የሚሰጡ ዕውቅናና ሽልማቶች ይበልጥ የኅብረተሰቡን የበጎ ፈቃደኝነት ባህል እንዲጎለብት የሚያበረክቱት አስተዋፅኦ ከፍተኛ እንደሆነ በዕቅድ አፈጻጸሙ ተመላክቷል።

ቀልጣፋና ጥራቱን የጠበቀ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሥርዓት በመዘርጋት ረገድ በተለይ በአለፉት ሦስት ዓመታት የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት አቅርቦትን ለማሳደግ በተሠራው ሥራ ዕድገት ተመዝግቧል። የመንገድ የትራፊክ ፍሰት እና ደኅንነትን በማሻሻል፣ የትራፊክ አደጋዎችን ከመቀነስ አንጻር የእግረኞች እንቅስቃሴ በሚበዙባቸው አካባቢዎች የአደጋ ተጋላጭነትን ለመቀነስ በአለፉት 3 ዓመታት ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ ቦታዎችን በጥናት በመለየት የቦላርድና ብረት አጥር ሥራዎችን የማስፋፋት ሥራ ተከናውኗል። ይህም የሚከሠቱ የትራፊክ አደጋዎች እየቀነሱ እንዲሄዱ አስችሏል።

ከአዲስ አበባ ፈጣን ዕድገት ጋር እያደገ የመጣው የነዋሪዎች የመኖሪያ ቤት ጥያቄ ጋር ተመጣጣኝ ምላሽ ለመስጠትና የቤት አቅርቦት ለማሟላት በተለያዩ የቤት አማራጮች ማለትም በኅብረት ሥራ ማኅበር፣ በግለሰቦች፣ በመንግሥት እና የግል ዘርፍ አጋርነት እንዲሁም በሪል ስቴት መኖሪያ ቤቶችን ለመገንባት ከተማ አስተዳደሩ ከፍተኛ ጥረት እያደረገ ይገኛል። በኅብረት ሥራ ማኅበራት የሚገነቡ ቤቶችን በተመለከተ የ2005 ዓ.ም 40/60 እና 20/80 ፕሮግራም ተመዝጋቢዎችን በ57 ማኅበራት እንዲደራጁ በማድረግ የግንባታ ቅድመ ዝግጅት ሥራ ተጠናቋል።

ከተማ አስተዳደሩ ዘመናዊ የመሬት አስተዳደር ሥርዓትን ቀጣይነት ባለው መልኩ ለመገንባት ይዞት በነበረው ዕቅድ መሠረት፣ የመሬት አስተዳደር ሥርዓቱ በከተማ ደረጃ የሚመራበት ከካዳስተርና የአድራሻ ሥርዓት ከግንባታው ጋር የተናበበ ወጥ የሆነ የሕግ ማሕቀፍ እንዲዘጋጅ፣ እንዲጸድቅና እንዲተገበር በማድረግ በከተማው ወሰን ውስጥ የሚገኙ ቁራሽ መሬቶች እና የጋራ መኖሪያ ቤቶች በሰነድ እና በመስክ አረጋግጦ መመዝገብ ችሏል።

ሌላው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከተከናወኑ ተግባራት መካከል ከተማዋን በዓለም አቀፍ መድረኮች እንድትታይ ያስቻሉ ሥራዎችን መሥራቱና ይህም ውጤት ማስገኘቱ ነው። አስተዳደሩ ከከተማ ገጽታ ግንባታ አንጻር ከውጭ እና ከሀገር ውስጥ ግንኙነት ሥራዎችን ለማሳደግ ከ14 ዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር ግንኙነት ለመፍጠር ዕቅዶ ዕቅዱን ሙሉ በሙሉ አሳክቶ ከ14 ተቋማት ጋር ግንኙነት መፍጠር ተችሏል። እንዲሁም ከ4 አዲስ የእኅት ከተማ ግንኙነት ለመመሥረት ታቅዶ ከ4 ከተሞች ጋር አዲስ የእኅት ከተማ (Sister City) ግንኙነት መመሥረት ችሏል። ከ16 አዲስና ነባር እኅት ከተሞች ጋር ያለውን ግንኙነት ለማጠናከር ዕቅዶም ከ9 የእኅት ከተሞች ጋር ጠንካራ ግንኙነት በማድረግ



## በሂደት ላይ ካሉ ፕሮጀክቶች

- ✓ ዓድዋ ሙዚየም 86 በመቶ
- ✓ የትራንስፖርት ተቋማት ቢሮ 61 ነጥብ 5 በመቶ
- ✓ የአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ 71 ነጥብ 2 በመቶ
- ✓ የየካ 2 መኪና ማቆሚያ 48 ነጥብ 2 በመቶ
- ✓ አዲስ አፍሪካ ኤግዚቢሽን ማዕከል 80 በመቶ
- ✓ አቃቂ ዓለም አቀፍ ስታዲየም 80 በመቶ ደረጃ ላይ ደርሰዋል።
- ✓ 186 ነጥብ 52 ሚሊዮን ሜትር ኪዩብንጹሕ ውሃ ተመርቷል።
- ✓ 130 ሺህ ቤቶችን ሥራ በማጠናቀቅ ባለዕድለኞች እንዲገቡበት ተደርጓል።
- ✓ 5000 ተገጣጣሚ ቤቶች ሥራ 30 በመቶ ተጠናቋል።
- ✓ 6 ሺህ 415 ቤቶች ተገንብተው ለዐቅመ ደካማ ነዋሪዎች ተሰጥተዋል።

የተለያዩ ሥራዎችን በጋራ ከውኗል።

በዚህም ከእሥራኤል ካምፓኒ በደንበኞች አገልግሎት (Customer Service) ዙሪያ ነጻ የቴክኖሎጂ አማራጭ አቅርቦ በከተማዋ ተቋማት ላይ ተግባራዊ እንዲሆን ስምምነት ላይ ተደርሷል። በተጨማሪም የአዲስ አበባ ከተማ ከፉጂያን ክፍለ ሀገር (ቻይና) ጋር አዲስ የእኅት ከተማ ጉድኝት ለመፍጠር የሚያስችል አጠቃላይ ቅድመ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ከተማ አስተዳደሩን በመወከል፣ በቻይና ቤጂንግ ከተማ የሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ቆንጽላ ጽ/ቤት የስምምነት ሰነድ እንዲፈርም ተደርጓል።

በተጨማሪም፣ በከተማዋ የMilan Urban Food Policy Pact አባል እንድትሆን በማድረግና በዓለም አቀፍ ደረጃ የትምህርት ቤት ምገባ መርሐ ግብርን በስፋት በማስተዋወቅ በብራዚል ሪዮ ዴጄኔሪዮ ከተማ በተካሄደው የ2022 Milan Urban Policy Pact Awards ውድድር ከ133 ከተሞች መካካል አዲስ አበባ አሸናፊ ሆናለች።

ጉዟችን ሩቅ መዳረሻችን ብልጽግና ነው ያሉት የከተማዋ ከንቲባ ክብርት አዳነች አቤቤ፣ በከተማችን የመጡ ለውጦች፣ መሥራትና ተግዳሮቶችን ማለፍ እንደምንችል ማሳያ እንጂ በራሳቸው በቂ ውጤት ናቸው ብለን ሳንረካ ያለድካም ለኢትዮጵያ ብልጽግና እንሠራለን ብለዋል!



በዓለም አቀፍ ደረጃ የትምህርት ቤት ምገባ መርሐ ግብርን በስፋት በማስተዋወቅ የ2022 Milan Urban Policy Pact Awards አዲስ አበባ አሸናፊ ሆናለች

- ✓ 130 ሄክታር አዳዲስ አረንጓዴ ቦታዎች የማልማትና ማስዋብ ሥራ ተሠርቷል።
- ✓ 110 የአንበሳና 200 የሸገር ዘመናዊ አውቶቡሶች ተገዝተው ወደ ሥራ ገብተዋል።
- ✓ 90 ሄክታር በሕገ ወጥነት የተያዘ መሬት ወደ መሬት ባንክ እነዲገባ ተደርጓል።
- ✓ ለ3 ሺህ 451 አርሶ አደሮች የመኖሪየና የእርሻ ቦታ ማረጋገጫ ተሰጥቷል።
- ✓ 16 ሺህ እናቶች በትምህርት ቤቶችና በማኅበረሰብ ምገባ የሥራ ዕድል ተፈጥሮላቸዋል።
- ✓ 3 ቢሊዮን ብር የሚደርስ ሀብት ከበጎ ፈቃደኞች ተሰባስቦ በዝቅተኛ ኑሮ ለሚኖሩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ተደጎሟል።
- ✓ 7 ነጥብ 3 ቢሊዮን ብር የሚገመት የበጎ ፈቃድ ሥራ ተከናውኗል።
- ✓ 632 ሚሊዮን 126 ሺህ ብር ለዓባይ ግድብ አስተዋፅኦ ድጋፍ ተደርጓል።
- ✓ 126 ሚሊዮን ብር በኮንሶና ቦረና በድርቅ ለተጎዱ ወገኖች ድጋፍ ተደርጓል።



# ትምህርት

ትምህርት ለአንድ አገር ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ዕድገት ቁልፍ መሣሪያ ነው። ይህ አጠቃላይ እውነታ እንደተጠበቀ ሆኖ ትምህርት በአንድ ሀገር ሁለንተናዊ ለውጥ ለማምጣት የአለውም ፋይዳ በርካታ ነው። ዓለም አንድ መንደር በሆነችበት በዚህ ዘመን በሀገራት መካከል ያለው ውድድር በቴክኖሎጂ ዐቅም ላይ የተመሠረተ መሆኑ የታወቀነው። ቴክኖሎጂን ለመፍጠርም ሆነ ለመጠቀም ደግሞ ዋናው ጉዳይ ትምህርት ነው።

ስለሆነም በሀገራት መካከል የሚካሄደው ውድድር በዕውቀት ላይ የሚመሠረት መሆኑ አይቀርም። የሰው ሀብትን ለማልማት ዋነኛው መሣሪያ ትምህርት በመሆኑ አዲስ አበባ ለዘርፉ ልዩ ትኩረት ሰጥታ እየሠራች ትገኛለች።

የትምህርት ዘርፉ ዋና ትኩረት የትምህርት ተሳትፎና ፍትሐዊነት በማሳደግ በዕውቀትና በሥነ-ምግባር የታነፀ ትውልድን ማፍራት ነው። ‹‹የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያዉ ሦስት ዓመት (2013-2015 ዓ.ም.) የልማት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት›› ላይ እንደተገለጸው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የትምህርት ሽፋንን በተመለከተ ከ2013-2015 ዓ.ም. በቅድመ አንደኛ ትምህርት 266,559 ተማሪዎች ለመቀበል ዐቅዶ 299,732 ወይም የዕቅዱን (112%) ማከናወን ችሏል። ይህ ስኬት የተገኘው ከተማ አስተዳደሩ በአመቻቸው የምገባ ሥርዓት ምክንያት ቤት ይውሉ የነበሩ በርካታ ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት በመግባታቸው ነው።

ከቅድመ አንደኛ በመቀጠል ያለውን ስንመለከት ደግሞ ከ2013- 2015 ዓ.ም. በአንደኛ ደረጃ ትምህርት 548,323 ተማሪዎች ለመቀበል ታቅዶ 607,369 (95.93%) ማከናወን ተችሏል። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት (9-12ኛ) ቅበላ በተመለከተ ሲታይ ከ2013-2015 ዓ.ም. 222,166 ተማሪዎች ለመቀበል ታቅዶ 226,549 (101.9%) ማከናወን ተችሏል።

በቅድመ አንደኛ ትምህርት 266,559 ተማሪዎች ለመቀበል ዐቅዶ 299,732 ወይም የዕቅዱን (112%) ማከናወን ችሏል።



ዜጎች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው እንዲማሩ በተፈጠረው ምቹ ሁኔታ፣ በ2014 ዓ.ም. 16,890 ተማሪዎች በአፋን ኦሮሞ ትምህርት የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ለመቀበል ታቅዶ 16,890 (100%)፤ በ2015 ዓ.ም. 30,583 ተማሪዎች ለመቀበል ታቅዶ 18,556 (60.6%) መቀበል ተችሏል። እንዲሁም በ2014 ዓ.ም. 34,184 ተማሪዎች በአፋን ኦሮሞ ትምህርት የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ለመቀበል ታቅዶ 34,184 (100%)፣ በ2015 ዓ.ም. 52,142 ተማሪዎች ለመቀበል ታቅዶ 42,692 (81.88%) መቀበል ተችሏል። ከዚህ በተጨማሪ በ2014 ዓ.ም. 12,769 ተማሪዎች በአፋን ኦሮሞ ትምህርት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ለመቀበል ታቅዶ 12,769 (100%)፣ በ2015ዓ.ም 20,729 ለመቀበል ታቅዶ 16,041 (77.4%) መቀበል ተችሏል።

ከትምህርት ቅበላና ተሳትፎ ጎን ለጎን የከተማዋን ሴቶች የትምህርት ተሳትፎ ለማሳደግ በርካታ ሥራዎች ተሠርተዋል። በቅድመ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ወንዶች በተወሰነ ልዩነት የሚበልጡ ሲሆን በአንደኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ግን ሴቶች የተሻለ ብልጫ አላቸው። በልዩ ፍላጎት ከ2013- 2015 ዓ.ም. 31,950 ተማሪዎች ለመቀበል ታቅዶ 37,198 (116.4%) ተማሪዎች የትምህርት ዕድል አግኝተዋል። በልዩ ፍላጎት በአፋን ኦሮሞ 500 ተማሪዎች ለመቀበል ታቅዶ 459 (91.8%) መቀበል ተችሏል።

የትምህርት ጥራትን ማሻሻል በተመለከተ ደግሞ ከ2013- 2015 ዓ.ም. የተማሪ መጽሐፍ ጥምርታ ምጥጥን በሁለተኛ ደረጃ (በዲጂታል) 1፡1 ለማድረስ ታቅዶ 1፡1 (100%) ማድረስ ተችሏል።

የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት የመምህራን ተማሪ ጥምርታ በተመለከተ ከ2013- 2015 ዓ.ም. 1፡35 ታቅዶ 1፡21፤ መጀመሪያ ደረጃ ትምህርት የመምህራን ተማሪ ጥምርታ 1፡20 ታቅዶ 1፡19፤ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የመምህራን ተማሪ ጥምርታ 1፡18 ታቅዶ 1፡19 ማድረስ ተችሏል።

ከ2013- 2015 ዓ.ም. በቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት የተማሪ የመማሪያ ክፍል ጥምርታ 1፡35 ታቅዶ 1፡39፤ በመጀመሪያ ደረጃ 1፡55 ታቅዶ 1፡45፤ በሁለተኛ ደረጃ 1፡40 ታቅዶ 1፡49 ደርሷል።

በቅድመ አንደኛ ደረጃ እና በ1ኛ ደረጃ ትምህርት መጠነ ማቋረጥ የቀነሰ ሲሆን በተለይ በ1ኛ ደረጃ በከፍተኛ ሁኔታ ቀንሷል። ይህም ለቅድመ 1ኛ እና 1ኛ ደረጃ የተሰጠው የምገባ ድጋፍ ውጤታማ እንደሆነ ማሳያ ነው።

የትምህርት መጠነ መድገምን መቀነስ በተመለከተ በሁለት የዕቅድ ዓመታት (ከ2013- 2014 ዓ.ም.) በመጀመሪያ ደረጃ (1-8) ትምህርት ተማሪዎች መጠነ መድገም በ2012 ዓ.ም. ከነበረበት 3.8% በ2014 ዓ.ም ወደ 3.12% ታቅዶ 1.6% (195%) ዝቅ ማድረግ የተቻለ ሲሆን ከ5 ዓመት ዕቅድ አንጻር ሲታይ ከ100% በላይ መሆኑን ያሳያል። በሁለተኛ ደረጃ በ2012 ዓ.ም. ከነበረው 9.7% በ2014 ዓ.ም ወደ 4% ለማድረስ ታቅዶ 2.42% (165%) ዝቅ ማድረግ የተቻለ ሲሆን ከ5 ዓመት ዕቅድ አንጻር ሲታይ ከ100% በላይ ሆኗል።

የትምህርት መጠነ ማለፍ በተመለከተ በሁለት የዕቅድ ዓመታት (ከ2013- 2014 ዓ.ም.) በ8ኛ ክፍል ትምህርት ተማሪዎች መጠነ ማለፍ በ2012 ዓ.ም. ከነበረበት 50.5% በ2014 ዓ.ም. ወደ 58.24% ታቅዶ 64% (110%) ማከናወን ተችሏል።

በዜጎች ተኮር ልማት ከተማ አስተዳደሩ በአመቻቸው የምገባ ሥርዓት እና የመማሪያ ቁሳቁስ መሟላት ምክንያት፣ ቤት ይውሉ የነበሩ በርካታ ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት በመግባታቸው የተማሪ ቅበላ ከ100% በላይ አድጓል። የተማሪ ወላጆች ኢኮኖሚያዊ ጫና ከማቃለል ባሻገር የተማሪ ውጤት ማሳደግ እና የቅድመ አንደኛ ደረጃ እንዲሁም የአንደኛ ደረጃ አቋራጭ ተማሪ ቁጥር መቀነስ ተችሏል። ዕድሜው ለትምህርት የደረሰን ዜጋ ሁሉ ከቅድመ 1ኛ እስከ 2ኛ ደረጃ በተቀመጠው የቅርበት፣ የቅበላና ተሳትፎ ስታንዳርድ መሠረት ምቹና አካታች በሆነ ትምህርት ቤት በፍትሐዊነት ማዳረስ በመቻሉ የልዩ ፍላጎት ተማሪዎችን ቅበላም ማሳደግ ተችሏል።

በቢሮው ትኩረት ከተሰጠባቸው መስኮች መካከልም ውስጣዊ ብቃትን ማሟላት፣ ፍትሐዊነትን ማረጋገጥ፣ የትምህርት ጥራትን ማስጠበቅ እና የትምህርት ሥርዓት ዐቅምን መገንባት ቢሆንም የትምህርት ፍትሐዊነትን የማረጋገጥ ተግባር ቅድሚያ ትኩረት አግኝቶ እየተሠራበት ይገኛል። የትምህርት አሰጣጡን በማዘመን እና በዕውቀትና በሥነ ምግባር የታነጸ ትውልድ ለማፍራት የከተማ አስተዳደሩ እየሠራቸው ያሉ ሥራዎች እጅግ አበረታች ውጤት ተገኝቶበታል።



# አዲስ ስፖርት

የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎችን በየአከባቢው በማስፋፋት እአምሮው የበለጸገ ጤናው የተጠበቀ ዜጋን ማፍራት ሀገራት የሚጋሩት ዓለም አቀፍ ግብ ነው። የኢትዮጵያ ስፖርት ፖሊሲ ማንኛውም ማኅበረሰብ በሚኖርበት፣ በሚማርበት እና በሚሠራበት አከባቢ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ በማድረግ ጤናማ እና አምራች ዜጋ እንዲሆን መሥራት እንዳለበት በግልፅ ያስቀምጣል። ይህን ታላቅ ሀገራዊ ፖሊሲ ለማሳካትና ስፖርትን ባህል ለማድረግ ከሚያስፈልጉ መሠረታዊ ነገሮች መካከል ዋነኛው የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራ ነው።

አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ እና የአፍሪካ መዲና እንዲሁም የዲፕሎማሲ ማዕከል እንደመሆኗ መጠን ለዜጎቿ በቂ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራ ለረጅም ጊዜ አልነበራትም። በተለይም የከተማዋ ነዋሪ ቁጥር በየጊዜው እየጨመረ መምጣቱና የቆዳ ስፋቷ ውስንነት በከተማዋ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎችን እንደ ልብ ያለመገኘት ችግር እጥፍ ድርብ አድርጎታል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ከተማዋ ያለባትን ይህን ትልቅ ችግር ለመፍታት የከተማዋን ስታንዳርድ /ደረጃ/ የሚመጥኑ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎችን የማዘጋጀት ትልቅ ሐላፊነት ተሰጥቶት እየሠራ ይገኛል። በአዲስ አበባ ከተማ በአለፉት አራት ዓመታት ከ500 በላይ የሚሆኑ የእግር ኳስ፣ የቅርጫት ኳስ፣ የእጅ ኳስ ፣የመረብ ኳስ፣ የሕፃናት መጫዎቻዎች እና ቤተመጻሕፍትን ጨምሮ 17 ዓይነት አገልግሎቶችን የሚሰጡ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎች ተገንብተው አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ።

አቶ ብርሃኑ ባዩ በአዲስ አበባ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ የማዕከላትና የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎች ልማትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ናቸው። ቢሯቸው ከተሰጡት ሐላፊነቶች ዋነኞቹ የስፖርት ማዘወተሪያ ሥፍራዎችን መገንባትና አዳጊ ስፖርተኞችን ማፍራት መሆኑን ይናገራሉ። ተተኪ ስፖርተኞችን ለማፍራት የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎች ስለሚያስፈልጉ ሁለቱ ጉዳዮች ተያያዥ ናቸው የሚሉት ዳይሬክተሩ፤ የስፖርት ማዘወተሪያ ሥፍራ ትውልድን ከማነጽና አልባሌ ቦታ እንዳይውሉ ከማድረግ አንጻር ጉልህ አስተዋፅኦ እንዳለው ይገልጻሉ። ቢሯቸውም ሆነ የከተማ አስተዳደሩ ለእነዚህ ጉዳዮች ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ መሆኑን ሲያስረዱም፣ እንደ ቢሮ የዓሥር እና የአምስት ዓመት ዕቅድ አለን። ከእነዚህ ዕቅዶቻችን በመነሣት በየዓመቱ ዝርዝር ዕቅዶችን በማዘጋጀት ከመሬት አስተዳደር፣ ከዲዛይንና ግንባታ እና ከፋይናንስ እንዲሁም ከፕላን ኮሚሽን ጋር በጋራ በመሥራት ውጤት ለማምጣት እየተንቀሳቀሱ መሆኑን ገልጸዋል። በየመንገዱ ይጫወቱ የነበሩ ልጆች ጥርጊያ ሜዳዎች ተሠርተውላቸው የሚገለገሉበትን ሁኔታ መፍጠር መቻሉ ትልቅ ውጤት ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል ይላሉ።

"በጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ አነሣሽነት የተጀመሩ ፕሮጀክቶች አሉ። የመደመር መጻሕፍት ተሸጠው ለልጆች መጫወቻና ለወጣቶች መዋያ የሚሆኑ የስፖርት ማዘውተሪያ ቦታዎች ተገንብተው አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ። ይሄ የሚያሳየው ከላይ እስከታች ያለው አመራር ለስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎች ልማት ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን ነው።" ብለዋል። ኢያይዘውም የባለሀብቱና የኅብረተሰቡ ተሳትፎም ወሳኝ እንደነበር ጠቅሰዋል።

በአዲስ አባባ የሚገኙ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎችን በ2012 ዓ.ም ከነበሩበት 840 በ2015 ወደ 945 ለማሳደግ ግብ ተቀመጦ የነበረ ሲሆን፣ ባለፉት ሦስት ዓመታት የኅብረተሰቡንና የግል ባለሀብቱን ተሳትፎ በማሳደግ በተሠራው ሥራ ወደ 1098 ከፍ በማድረግ የዕቅዱን አፈጻጸም 116 በመቶ በማድረስ ለኅብረተሰቡ ተደራሽ ማድረግ ተችሏል። እነዚህ ማዘወተሪያ ሥፍራዎችም ጥርጊያ ሜዳዎች ፣ጅምናዚየሞች፣ መዋኛ ገንዳዎች ፣ ስቴዲየሞችና ፣ 3በ1 ፣ 2በ1፣ ሜዳ ቴኒስ ሲሆኑ ተገንብተው አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ። የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎች በከተማ ደረጃ ሁሉም ዜጎች በአካል እና በአእምሮ ጎልብተው ጤናማ እና አምራች እንዲሆኑ በማኅበረሰብ አቀፍ ስፖርት እንዲሳተፉ የስፖርት ሥልጠናዎችና ውድድሮች በአግባቡ እንዲካሄዱ በማድረግ ለስፖርት መስፋፋት ከፍተኛ ሚና እየተጫወቱ ይገኛል።

በ2013 በጀት ዓመት ቢሮው ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጋር በጋራ በመሆን 51 የስፖርት መዘውተሪያ ሥፍራዎችን ግንባታቸውን አጠናቆ ለተጠቃሚዎች ክፍት አድርጓል። ከእነዚህ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎች መካከል 45ቱ





ግንባታቸው በ2013 ዓ.ም. የተጀመሩና የከተማ አስተዳደሩ ከፍተኛ አመራር ባደረገው ክትትልና ድጋፍ በአጭር ጊዜ ውስጥ የተጠናቀቁ ናቸው። ግንባታቸዉ በ2013ዓ.ም ተጀምሮ በአጭር ጊዜ ከተጠናቀቁ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎች መካከል የአፍንጮ በር ሁለገብ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራ አንዱ ሲሆን ግንባታው በሦስት ወር ከ15 ቀን የተጠናቀቀ እና የቅርጫት ኳስ፣ የቮሊቦልና የእጅ ኳስ ስፖርት መጫወቻ 3 በ1 ሜዳ፣ የእግር ኳስ ሜዳ እና የቤት ውስጥ ጨዋታዎችን ማጫወት የሚችል አዳራሽ እንዲሁም ካፍቴሪያ ያለው የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራ ነው። ለግንባታውም 14 ሚሊዮን ብር ከተማ አስተዳደሩ ወጭ አድርጎበታል። የፈረንሳይ ጨፌ ሜዳ ሁለገብ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራ ሌላዉ በከተማ አስተዳደሩ በ3 ወር 15 ቀን ግንባታው የተጠናቀቀ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራ ነው። ደረጃውን የጠበቀ የእግር ኳስ ሜዳ፣ 3 በ 1 ሜዳ፣ የእግር ኳስ ሜዳ እንዲሁም የቤት ውስጥ ስፖርቶች ማወዳደሪያ አዳራሽና የሻወር ቤቶችን አካቶ የተገነባ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራ ነው። ለግንባታውም 25 ሚሊዮን ብር ከተማ አስተዳደሩ ፈሰስ አድርጎበታል።

የራስ ኃይሉ ዘመናዊ የውሀ ገንዳ ግንባታው በ2005 ዓ.ም. የተጀመረና በችግር ምክንያት የዘገየ ነበር። የነበረበትን የተለያዩ ችግሮች የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስፖርት ኮሚሽን ከከተማ አስተዳደሩ ጋር በጋራ በመሆን በመለየትና በመፍታት በ2013 ዓ.ም. ግንባታው ተጠናቋል። ለግንባታው በአጠቃላይ አንድ መቶ ዓሥር ሚሊዮን ብር ወጭ ሆኖበታል። የሕፃናት እና የዐዋቂዎች መዋኛ ገንዳን አካቶ የተገነባ ዘመናዊ የውሃ መዋኛ ገንዳ ነው።

በ2015 ዓ.ም. በጀት ዓመት ብቻ ከ24 በላይ የማዘውተርያ ሥፍራዎችን በመገንባት ለአገልግሎት ክፍት እንዲሆን የማድረግ ሥራ በመሠራቱ ስፓርቱ መነቃቃትን አግኝቷል። ቢሮው የከተማዋን ነዋሪ ማኅበረሰብ ቁጥር ያማከለና የከተማዋን ስታንዳርድ /ደረጃ/ የሚመጥን የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራ ለማዘጋጀት ያደረገው ዘርፈ ብዙ እንቅስቃሴ በስኬት እንዲጠናቀቅ የመደመር ትውልድ መጽሐፍ ምርቃት የአንበሳውን ድርሻ ይዟል።

በ2015 ዓ.ም. በጀት ዓመት በሦስት ወራት ውስጥ ግንባታቸው የተጠናቀቁ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎች ሁሉም በሚባል ደረጃ ስታንዳርዶችን የጠበቁ እና ወቅቱን የሚዋጁ ሆነው ተሠርተዋል። 12 የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎች በመደመር ትውልድ የመጽሐፍ ሽያጭ የተገነቡ ሲሆን ቀሪዎቹ 12 ከተማ አስተዳደሩ በመደበው በጀት ግንባታቸው በአጭር ጊዜ ተጠናቆ አገልግሎት መስጠት የጀመሩ ናቸው። ማዘውተሪያዎቹ የቅርጫት ኳስ፣ የመረብ ኳስና የእጅ ኳስ ስፖርት መጫዎቻ፣ 3 በ1 ሜዳ፣ የእግር ኳስ ሜዳ እና የቤት ውስጥ ጫዋታዎችን ማጫወት እንዲችሉ ተደርገው የተገነቡ እና አዳራሽ እንዲሁም ካፍቴሪያ አላቸው።

የማዘውተሪያ ሥፍራዎች ሀገር አቀፍ ስታንዳርድ እንዲያሟሉ ለማድረግ በተሠራውም ሥራ 10 ማዘውተሪያ ሥፍራዎች ደረጃ (ስታንዳርድ) እንዲያሟሉ የተያዘው ዕቅድ ግቡን መቷል። የአበበ ቢቂላ ስቴድየም እና የራስ ኃይሉ መዋኛ ገንዳ ዓለም አቀፍ ደረጃ (ስታንዳርድ) ያሟሉ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎች እንዲሆኑ የማድረግ ተግባር ተከናውኗል። የአቃቂ ቃሊቲ ኢንተርናሽናል ስታዲየም ግንባታ ቀሪ ሥራዎችን የመለየት ሥራ ከመሥራት ጎን ለጎን የCAF እና FIFA ስታንዳርድ እንዲያሟላ ከኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ጋር በመነጋገር ለስታዲየሙ ማስፋፊያ የተጠየቀው ቦታ ተፈቅዶ ግንባታው በመካሄድ ላይ ይገኛል።

በአዲስ አበባ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ የማዕከላትና የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎች ልማትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ብርሃኑ ባዩ ለዘመን መጽሔት እንደተናገሩት፣ በሌሎች ሀገሮች ተሞክሮ እንደታየው የስፖርት ማዘወተሪያ ሥፍራዎች በመንግሥት ብቻ ተገንብተው ተደራሽ ማድረግ አይቻልም። ባለሀብቶች የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎችን ማልማት እንዲችሉ አንድ ደምብ አዘጋጅተን ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትሕ ቢሮ አቅርበን እየታየ ይገኛል። ደምቡ ሲጸድቅ እስከዛሬ ባለሀብቱ ጥያቄ እያቀረበ የሕግ ማሕቀፍ ባለመኖሩ ምክንያት ሳይስተናገድ የቀረበት ሁኔታ ተቀይሮ የግል ዘርፉ የስፖርት ማዘወተሪያ ሥፍራዎች ግንባታ ላይ መሠማራት ይችላል። በአለፉት ጥቂት ዓመታት የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎችን ለማስፋፋት የተሰጠው ከፍተኛ ትኩረት በዚህ የሕግ ማሕቀፍ ሲደገፍ በአዲስ አባባ ከተማ የፊነጠቀው የስፖርት ማዘወተሪያ ቦታዎች ትንሣኤ ወደላቀ ደረጃ እንዲሸጋገር አመቺ ሁኔታ ይፈጠራል።

ስለኢትዮጵያ

ኢትዮጵያ እያሸነፈች ትሻገራለች!